# ርዕስ አንቀፅ

## ረቂቅ ሕጉን መተቸት በራሱ ያስከስስ ይሆን?

በሀገራችን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተረቀቁ ወደ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እየተላኩ ያሉ ሕጎች በአብዛኛው በጀርባቸው ያዘሉት የገዥውን ሃይል ህልውና ለማስከበር በሚያስችል መልኩ የተቃኙ ይመስላሉ:: ለገዢው ኢሕአዴግ የስልጣን ጉዞ አቀበት ይሆናሉ ተብለው የተገመቱ ሃይሎች በአብዛኛው የሰንሰለት የልጓም ሸምቀቆ እየተበጀላቸው ይገኛሉ:: በሂደትም የሰንሰለት ልጓም ተብለው የተገለፁት ሕጎች በአብዛኛው ሕዝብ የስልጣን ባለቤት እንዳይሆንና የሕዝብ ይሁንታ ያገኘ የፖለቲካ ስልጣን እንዳይዝ ለማድረግ ጉልበት ያላቸው መሆናቸው በዲሞክራሲያዊ ሂደት ላይ አደጋ ጋርጠዋል:: ምርጫ 97ን ተከትሎ በተከታታይ የወጡ የፕሬስ፣የመያዶች፣የፓርቲ፣ የባንክ … ወዘተ ሕጎችን የተመለከተ አንድምታቸው ከእንግዲህ «በስልጣን ቀልድ የለም» አይነት ይመስላል:: በዚህም እይታ የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ሁኔታ ከነበረው ወደ አልነበረው የውስብስብ ገፅታው እያመራ ነው ሊያስብል ይችላል:: ሁኔታው የኋልዮሽ ተጉዞን አስቀያሚውን የቀድሞ የሀገራችንን ታሪክ ልንከልሰው ነው እንዴ!? የሚያስብል አግራሞት አዘል የስጋት ጥያቄ ብዙዎች እንዲጠይቁ አስገድዷቿል::

የሚወጡ ሕጎች በውስጣቸው እጅግ ከፍተኛ ቅጣትና ገደቦች አካተው ተግባራዊ ሆነዋል:: በርካታቹም ከአስተማሪነትና የህዝብን ሰላምና ደህንነት ከመጠበቅ ይልቅ በመብቶች ላይ ከፍተኛ ገደቦችን የማስቀመጥ ባሕሪ ይታይባቸዋል:: ለዚህ መከራከሪያ ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎችና ዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ቃል ኪዳኖች አፅንኦት በመስጠት ትልቅ ከለላ የሰጧቸው መብቶች እምብዛም በማያሳምኑ እና ቢያንስ «የበቀርን» (exceptions) አግባ በማያሟሉ መከራከሪያዎች ገደብ እንዲጣልባቸው ሆነው የፀደቁ ህጎች ማስረጃዎች ናቸው:: እነዚህ የሚያስረዱት ማንኛውንም ዓይነት ሂደቶችን ለመመከተ የህግ ድጋፍ ለመያዝ ነው:: ይህ ደግሞ እያንዳንዷ አተነፋፈስህን በመንግስት ፍላጎት እና ይሁንታ እንዲሆንና የህዝብ ልዕልና ጎልቶ እንዳይወጣ ወጥመድ የማነፅ ስራ እንደሆነ አብዛኞቹ የፖለቲካ ሰዎች የገለፁት እና እየገለፁት የሚገኝ ነው:: ይህንን የእራሱ የኢህአዴግ ልሳኖች በራሳቸው መንገድ ገልፀውታል:: ለዚህ እርምጃው ይረዳው ዘንድ ሰሞኑን ዲፕሎማቶች ምክር ይሠጡበት ዘንድ መንግስት ያዘጋጀው የፀረ-ሽብርተኝነት ረቂቅ ህግ አንዱ መገለጫ ነው::

ለአሜሪካና ለአውሮፓ ዲፕሎማቶች ተበትኗል የተባለው የህግ ረቂቅም የሀገሪትዋን ህገ መንግስት የሠብአዊ መብት ድንጋጌዎች፣ የማስረጃ አቀራረብ ሂደቶችን መሠረታዊ መርህዎችና የፍትህ ስርዓቱን የስራ ልምድ ፍፁም ሊቀይር የተነሳ ይመስላል:: መቼም በሀገራች አንድ ህግ ተረቆ ከወጣ መፅደቁ አይቀሬ በመሆኑ ምናልባት ሰሚ ካለ ተስፋ በማይቆርጠው የብዕር ቀለማችን የበኩላችንን ምክር ለመለገሽ የተወሰኑ ነጥቦችን እናንሳ:: እዚህ ጋር በቅድሚያ ረቂቅ

ህጉ ከመፅደቁ በፊት ረቂቁ ላይ አስተያየት መስጠት የሚያስጠያቅና ሽብርተኛ የሚያስብል ከሆነ ከወዲሁ «አውቀን በድፍረት ሳናውቅ በስህተት ለሰራነው ሀጢያት» እንደተለመደው ይቅርታን ከወዲሁ ተማፅነናል፡፡

የፀረ-ሽብርተኝነት ረቂቅ ውስጥ እንደ ጀምስ ቦንድ ፊልም በአሸባሪነት የተጠረጠረው ሰው መያዝም ሆነ ለረጅም ወራት ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ፖሊስ ተጠርጣሪን በቁጥጥር ስር ማዋል ይቻለዋል፡፡ በሰሚ ሰሚ ያገኘውንም ሆነ በሌላ መንገድ የተገኙ ማስረጃዎችን አስፈፃሚው አካል ለፍርድ ቤት ሲያቀርብ ፍርድ ቤቱ እንዲቀበል ማድረግ፤የተጠረጠሩ ሰዎች የስልክ፣ የኢንተርኔት . . . የግንኙነት መስመሮቻቸውን መጥለፍ፣ መኖሪያ ቤታቸውን በሚስጥር መመርመር ይቻላል፡፡ ሽብርተኛ የተባሉ ድርጅቶችን ወይም ቡድኖችን ዓላማ ወይም ተግባር ያበረታታ፣ የፃፈ፣ ያተመ፣ ያሳየ፣ ያሰማ በተባባሪነት ተቆጥሮ ለዓመታት ለእስር ይዳረጋል፡፡ የሽብር ተግባር እፈፅማለሁ ብሎ የዛተም በፀረ-ሽብርተኛ ረቂቅ ህጉ ውስጥ እጅግ ከፍተኛ ቅጣት ተቀምጦለታል፡፡ አሸባሪ ነህ አይደለህም በሚለው የክርክር ሂደት ውሰጥ የማስረዳት ሸክም (burden of proof) ከከሳሽ ወደ ተከሳሽ የተሸጋገረበት ሁኔታ በረቂቁ ላይ ታይቷል፡፡ ተጠርጣሪው በማያውቅበት ሁኔታ (በሚስጥር) የራሴ ብሎ በግል ባስቀመጣቸው ወሰኖች ውስጥ አልፎ አስፈፃሚው አካል ምርመራ እንዲያደርግ ረቂቁ ሌላ ፍቃድ ይሰጠዋል፡፡

በቁንፅል ከላይ የገለፅናቸው የረቂቁ ክፍሎች በአብዛኛው ከመሰረታዊ የህግ መሰረቶች አንፃር በእጅጉ ላዕላይ ችግር ያለባቸው ናቸው፡፡ በአንድ ወቅት የእንግሊዝ ጠ/ሚኒስተር የነበሩት ቶኒ ብሊየር ለአገራቸው ፓርላማ ካቀረቡት እና ፓርላማውም የቀረበው አይነት ረቂቅ ህግ በመቃብራችን ላይ ካልሆነ በጭራሽ አይደረግም ብሎ ድጋፍ ከነፈገው ረቂቅ ህግ ጋር የኢትዮጵያው ረቂቅ መጠነኛ ጎረቤትነት ይታይበታል፡፡ ነገር ግን መሠረታዊ የሆነ የፍትህ ስርዓት በመጋፋቱ እረገድ ከቶኒ ብሊየር ረቂቅ ይልቅ በመንግስት የተረቀቀው እጅግ የባሰ ነው፡፡ በዚህ ረቂቅ በአሉባልታ የመጠርጠርና ተጠርጣሪው ካለ አንዳች የዕስር ማዘዣ በቁጥጥር ስር እንዲውል የማስደረግ እና የማድረግ መብት አስፈፃሚ የመንግስት አካል አለው፡፡ ይህ በሁለት መደቦች ተይዞ የነበረው ስልጣን የሽብርተኝነት ጉዳይ ላይ ሙሉ በሙሉ ለአስፈፃሚው አካል አምላክን ፈርቶ በትክክለኛው መንገድ ካልተጓዘ በቀር ተጠርጣሪውን እንደፈለገው ቢያደርገው የሚጠየቅበት መንገድ የለም፡፡ ስለዚህ የበደል መንገድ ይከፍታል፡፡ በተለይ መሰረታዊ የማስረጃ አቀራረብ ላይ በትልቁ የተሰመረበት፤በሰሚ ሰሚ (በአሉባልታ) የተገኘ ማስረጃ (ከተውሰኑ ልዩ/«በቀር»/ ድንጋጌዎች መኖር በስተቀር) በፍርድ ቤት ተቀባይነት የሌለው ቢሆንም በአሁኑ ረቂቅ በተቃራኒው ተቀምጧል፡፡ እዚህ ጋር አንድ አስገራሚ ነገር እድናስታውስ ያረገን የኢትዮጵያ የማስረጃ ሕግ ተረቆ ቁጭ ብሎ አቧራ እየጠጣ ባለበት፣ እልፍ አንቀፆች ፀድቀው ተፈፃሚ ሆነዋል፡፡ ምናባትም የጸረ-ሽብርተኝነት ረቂቅ ሕግ የማስረጃ ረቂቁን ቀድሞ እንደሚፀድቅ ለመገመት አይከብድም፡፡ ግን ለምን እንዲህ ሆነ? በአሉባልታ የተገኘ ማስረጃ የአንድን ሰው አሸባሪነት የሚያረጋግጥበት አካሄድ ሕገ መንግስታዊ ካለመሆኑም በላይ በአገሪቱ ካለው ደካማ የፍትህ ስርዓት ጋር ተደምሮ የዜጎችን ችግር እንዳያባብሰው ትልቅ ስጋት አለን፡፡

አንድ ሰው ወንጀል አልፈፀምኩም ብሎ ቢል ወንጀለኝነቱን የማስረዳት ሸክም የተጣለው በአቃቤ ሕግ ላይ ቢሆንም በአሁኑ ረቂቅ ግን መሰረታዊ የሕገ መንግስት መስፈርትን ሳይጠብቅ በተፃራሪ ተጠቅሷል፡፡ አቃቤ ህግ ከግለሰብ የተሻለ ማስረጃ የመሰብሰብና የማስረዳት ህጋዊ ዕውቅና ያለው ስለመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግም ሆነ በማስረጃ አቃራረብ መርሆች በግልጽ  የተቀመጠ ነው፡፡ እንዲህ አይነቱ ሕግ አንድ በወንጀል ተጠርጣሪ የፍርድ ውሳኔ ተሰጥቶት ወንጀለኛነቱ እስከሚረጋገጥበት ጊዜ ድረስ ከተጠረጠረበት ወንጀል ነፃ ሆኖ የመገመት መብቱን የሚገፍ ነው፡፡ በዚህ ረቂቅ-ሕግ አንድ ተጠርጣሪ የሽብር ድርጊት መፈፀሙን ለፖሊስ በሰጠው ቃል ያመነ ከሆነና አቃ ሕግ ተጠርጣሪው ከወንጀሉ መፈፀም ጋር በተያያዘ ግንኙነት እዳለው ከጥርጣሬ በላይ ለፍርድ ቤቱ ካሳየ የአቃቤ ሕጉን ማስረጃ ውድቅ የማድረግ ሸክም ወደ ተከሳሹ ይዞራል፡፡ ፖሊስ በአንድ ተጠርጣሪ ላይ አካላዊ ጉዳትና ስቃይ በማድረሱ ተጠርጣሪው የተጠረጠረበትን ወንጀል መፈፀሙን ቢያምን ፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ ደግሞ ትክክለኛውን እውነታ ቢያስቀምጥ እጣ ፈንታው በል እራስህ ተወጣው ሊሆን ነው ማለት ነው? በማስገደድ/በሃይል የተገኘ ማስረጃ በይፋ በሕግ ደረጃ ተቀባይነት ሊኖረው ነው ማለት ነው? በተጠርጣሪ አፀድ፣መኖሪያ ቤት፣ . . . ሽበርተኛ ሊያስብለው የሚችል ቁስ በአንድ ቡድን ወይም ግለሰብ ቢቀመጥበትና እርሱም እንዲያ ስለመሆኑ እንጂ ስለ አቃቤ ሕግ ውንጀላ የሚያውቀው አለመኖሩን በመግለፅ ውንጀላውን ውድቅ ቢያደርግ፣ ከሳሹ ወንጀሉ ስለመፈፀሙ ማስረዳት ሲገባው ተጠርጣሪውን በል ወንጀሉን አለመፈፀምህን ከእኔ ቀድመህ በማስረጃህ ተወጣው ልንለው ነው? እነዚህ ጥያቄዎች ረቂቅ ሕጉ ሕግ ከመሆኑ አስቀድሞ በፀሞና ተጢነው የመፍትሄ ነጥቦች ሊሰጣቸው የሚገቡ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የረቂቁን ሁለንተና ስናየው ሰላምና መረጋጋትን ከመፍጠር ይልቅ ውጥረትን የማንገስ ባህሪ የተጫጨነው ነው፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ ምን ያህል የአሸባሪዎች ኢላማ ተደቅኖባታል? የሚል ጥያቄ ለጊዜው እናቆየውና አሸባሪዎች አደጋ ከመጋረጣቸው አስቀድሞ ምን እናደርጋለን የሚለው ቀድሞ መታሰቡ ተገቢ ነው፡፡ በሀገር ውስጥ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ (አይዲዮሎጂ) ልዩነቶቻቸውን ማስታረቅ ተስኗቸው ጎራ ለይተው ለሚጋጩ፣ አሸባሪና ተሸባሪ ሆነው በሁለት ጎራ ራሳቸውን ፈርጀው ከመንቀሳቀስ፣ በምክንያታዊ የፖለቲካ ሰበዝ የራሳቸውን እሳቤ አጉልቶ በመምዘዝ በሰላማዊው መንገድ ልዩነታቸውን መፍታትና ሆደ ሰፊነትን መፍጠር ታላቅ መፍትሄ ነው፡፡ አሳሪና ታሳሪ ሳያስፈልግ ለሁሉም የምትሆን ሀገር ከገነባን መክሰስ ሳይስፈልገን መፍትሄ መፍጠር ይቻለናል፡፡ ህገ መንግስቱን እስከመርሳት የሚያደርሱ ህጎችን መቆለል ሳያስፈልግ ፖለቲከኞቻችን መከባበር በመሀላቸው ሳያጡ ይህችን ሀገር ወደፊት ፈቀቅ ሊያደርጓት ይቻላቸዋል፡፡ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ የፖለቲካ ጥፋቶችና የአስተዳደር ክስተቶች ውስጥ እየገቡ የሚፈጠር መኮራረፍ የአሸባሪነት መዝገብ ውስጥ እየተመዘገቡ ከመጡ ያሉን ቀውሶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ የሚያደርጉ እንጂ የመፍትሄ ቀንዲሎች እንድንሆን የሚያስችልን አይደለም፡፡ የመተሳሰብ እና የመግባባት ቅርጫት ያስፈልገናል፡፡ ይህ ቅርጫት የእብሪት፤ የአምባገነንነት እና የጥላቻን ነቀርሳ የምንጥልበት ይሆን ዘንድ ይጠቅመናል፡፡ ከዚህ ውጭ

ለሀገራችን - የሁላችንም ሀገር የሆነቸውን ኢትዮጵያን - ስጋት ለሆነ፣ የሽብር ጦሩን ለሰበቀ ጠላት የጋራ ክንድ ይረዳ ዘንድ ሌላ ቅርጫት ያስፈልጋል፡፡ ዞሮ ዞሮ ኢላማው ኢትዮጵያን ወደፊት አንድ እርምጃ እንድትራመድ መስማማቱ ላይ ነው፡፡ ይህ ከሆነ የጋራ ጠላታችን የሆነውን ሽብርን የመዋጋትና የማስቀረት መፍትሄው በእጃችን ላይ ይሆናል፡፡ ለጋራ መፍትሄ በጋራ እንስራ! የመፈራረጅ ፖለቲካ ይቁም፡፡ ህጎቻችን መፍትሄ እንጂ የፖለቲካ ምስቅልቅሎሽ የሚፈጥሩ አይሁኑ፡፡ ሁላችንም ስለራሳችን ሳይሆን ስለሀገር ህልውና መፍትሄ እናስብ፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ነገሮችን አወሳስቦ ከመቋጠርና ከማጦዝ እንቆጠብ - ኩራታችን ወደፊት መጓዛችን እንጂ የኋልዮሽ መስፈንጠራችን አይደለምና!

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር**

# Verbatim

## *ማን ምን አለ?*

« **….** የሰው ልጅ አቋም ባለበት የረጋ (Static) አይደለም፡፡ የሰው ልጅ አስተሳሰቡም ሆነ አቋሙ አንዴ የተተከለ አይደለም፡፡ ያም ከሆነ ችግር አለበት ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ሕወሓትም ኦህዴድም ከነበሩት ጋር ለመስራት ግንኙነት እየፈጠርን ነው፡፡ … ግንኙነት ስንፈጥር መሰረታዊ ቁም ነገሩ በእነዚህ መርህዎች ያምናሉ ወይ ነው እንጂ ያለፈውን ታሪክማ ሁሉም የየራሱ ታሪክ አለው፡፡ …»

***(ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ፣** በመጋቢት 6 ቀን 2001 በወጣው ሪፖርተር ጋዜጣ ላይ ባደረጉት ቃለ ምልልስ ከቀድሞ የህውሓት ባለስጣናት ጋር ለመስራት መወሰናቸው ለምን እንደሆነ ተጠይቀው ሲያስረዱ ከተናገሩት ተወሰደ፡፡)*

« … እኔ በጥቅሉ ለኦሮሞ ህዝብ ወይም በኦሮሞ ህዝብ ቁመት ስልጣን ለመጋራት ይሄ መንግስት ዝግጁ አይመስለኝም፡፡ … ያ እስካልተደረገ ድረስ ብዙ የሚደረጉ ግርግሮች ከግርግር ያለፈ ውጤት ያመጣሉ የሚል እምነት የለኝም፡፡ የኦሮሞ ህዝብ መሰረታዊ ጉዳይ መብቱን የመጎናፀፍ ጥያቄ ነው፡፡ . . . »

***(ዶ/ር መራራ ጉዲና፣** ለአውራምባ ታይምስ በጥቅምት 04 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጡት ቃለ ምልልስ ላይ በመንግስትና በኦነግ መደራደር ዙሪያ ተጠይቀው ከሰጡት ምላሽ የተወሰደ፡፡)*

« … በእርግጥ እከሌ ብዬ በሞዴልነት የምይዘው ሰው የለም። ግን በአንፃራዊነት ቀልቤን የምትስበው የበርማዋ (ምየንማር) የሰብአዊ መብት ተሟጋችና ሰላማዊ ታጋይ ኦንግ ሳን ሱኪይ ነች። እስረኛም ስለሆነች ነው መሰለኝ የመንፈስ ጥናካሬዋን አደንቅላታለሁ … »

*(ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ፣ ለአውራምባ ታይምስ በሞዴልነት የሚጠቅሱት ሰው ካሉት ተብለው ተጠይቀው ምላሽ ከሰጡት የተወሰደው።)*

« … በአገራችን የትምህርት ጥራት፣ብቃትና ውጤታማነት እንዳይኖር የፈረደው ገዢው ፓርቲ ራሱ ነው። የሞያው ነፃነት በፖሊካ ጣልቃ ገብነት ተክቶ ትምህርትና ተቋማትን ለፖለቲካ መሳሪያነት እየተጠቀመበት ይገኛል። ታዲያ ራሱ ገድሎ ራሱ ሙሾ ቢያወርድ እንዴት መፍትሄ ሊገኝ ይችላል … »

*(አቶ ገብሩ አስራት፣ የቀድሞ ትግራይ ክልል ርዕሰ መስተዳደር የነበሩ፣ በአሁኑ ወቅት የአረና ትራይ ሊቀመንበር እንዲሁም የ«መድረክ» አባል፤ «የትምህርት ዘርፉን ገድሎ ማልቀሱ ይቁም» በሚል ርዕስ በመጋቢት 5 ቀን 2001 ዓ.ም በአዲስ ነገር ጋዜጣ ላይ ካሰፈሩት ፅሁፍ የተወሰደ።)*

# ዜናዎች

## ወ/ሪት ብርቱካን ነገ ፍርድ ቤት ይቀርባሉ

ከታሰሩ ሁለት ወር ከአስራስምንት ቀን የሆናቸው የአንድነት ለዴሞክራሲ እና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ሊቀመንበር ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ የካቲት 27 ቀን 2001 ዓ.ም በህግ ጠበቃቸው በኩል የፌደራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽንን መክሰሳቸው ይታወሳል። ሊቀመንበርዋ በክሳቸው ላይ የሰብዓዊ መብታቸው እየተጣሰ መሆኑን፤ ማረሚያ ቤቱ ከእናታቸው እና ከልጃቸው በስተቀር በሌሎች ሰዎች እንዳይጎበኙ ማድረጉን ነገር ግን ከዘመዶቻቸው፤ ከጓደኞቻቸው ከሃይማኖት አባታቸው፤ ከህግ አማካሪያቸው እና ሃኪማቸው ጋር የመገናኘት መብታቸው በሕግ መከበሩን በክስ ማመልከቻቸው ላይ ዘርዝረዋል። ከዚህም ባለፈ ወ/ሪት ብርቱካን በቁጥጥር ስር

ከዋሉበት ጊዜ አንስቶ ለብቻ መታሰራቸው ተገቢ አለመሆኑንም በክስ ማመልከቻቸው ላይ ተካትቷል።

ባለፈው ሳምንት ማክሰኞ የሊቀመንበሯ የክስ አቤቱታ በፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር በኩል በፌደራል አንደኛ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ለአምስተኛ ፍታብሔር ችሎት ለዳኛ ሀቢብ ማሀመድ ቀርቦላቸው ነበር። ነገር ግን ዳኛው ከወ/ሪት ብርቱካን ጋር የግል ትውውቅ ስላለኝ ጉደዩን መመልከት አልችልም በማለታቸው ክሱ ወደ ሬጅስትራር መመለሱ ይታወሳል። በዚህም መሠረት የፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር ክሱ ወደሌላ ችሎት እንዲዛወር አድርጓል።

በዚህም መሠረት ባለፈው ሐሙስ የወ/ሪት ብርቱካን የክስ ሒደት ዘጠነኛ የፍትሐብሔር ችሎት ጉዳዩን እንዲመለከተው የሬጅስትራር ጽ/ቤቱ መዝገቡን ልኳል።

የወ/ሪት ብርቱካን ክስ በፍርድ ቤቱ ሬጅስትራል የተሳካለት የመጀመሪያ ደረጃ የልደታ ምድብ ዘጠነኛ የፍትሐብሔር ችሎት ለነገ መጋቢት 9 ቀን 2001 ዓ.ም ቀጠሮ ሰጥቷል። በዚህም መሠረት ከሳሽ እና ተከሳሽ ነገ ልደታ በሚገኘው የአንደኛ ደረጀ የፍታብሔር ልደታ ምድብ ዘጠነኛ ችሎት ተገኝተው ከሳሽ ያቀረቡትን አቤቱታ በመመልከት ማረሚያ ቤቱን ያስከስሰዋል አያስከስሰውም የሚለውን ውሳኔ ያደምጣሉ ተብሎ ይጠበቃል።

# የታላቁ ኢትዮጵያዊ ልጅ የመጀመሪያዋ ኢትዮ-አሜሪካዊ ዳኛ ሆና ተሾመች

«ታላቁ የሙዚቃ ሰው» ተብለው በኢትዮጵያውያም ሆነ በዓለም የሚታወሱት ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ ዳግመኛ ስማቸው ተዘክሯል። የእኝህ ታላቅ የሙዚቃ ሰው ልጅ የሆነችው ኒና አሸናፊ ሪቻርድሰን በፍሎሪዳ የመጀመሪያዋ ኢትዮ አሜሪካዊ ዳኛ ሆና ተሾመች።

ኢትዮ - አሜሪካዊቷ ኒና በኢትዮጵያ ተወልዳ በልጅነትዋ ከአባትዋ ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ ጋር ወደ ዩናይትድ ስቴት በመጓዝ ኑሮዋን በፍሎሪዳ አድርጋ ቆይታለች። ዳኛ ኒና ባለትዳርና የሁለት ልጆች እናት ስትሆን ባለቤትዋ ሪቻርድሰን ቀደም ሲል በፍሎሪዳ ስቴት የሕግ አውጪ ምክር ቤት አባል ነበር። ኒና በፍሎሪዳ የመጀመሪያዋ ኢትዮ- አሜሪካዊት የጠበቆች ማህበር አባልም ለመሆን ችላለች። የማህበሩ አመራር አባልም ለመሆን ችላለች። አሁን ደግሞ በአንድ ግዛት ደረጃ ዳኛ ሆና ተሹማለች።

«በአገር የፍርድ ቤት ደረጃ ዳኛ ሆኖ መመረጥ ትልቅ ነገር ነው ዋናው ነገር ይንን አስጠብቆ የመሄድ ጉዳይ ነው። የሥራ ሽክም እና ኃላፊነቱ ከባድ ነው። ነገር ግን የተሰጠኝን እድል በትጋት እወጣለሁ» ስትል ዳኛ ኒና ለፍሎሪዳ ታይምስ ተናግራለች።

የኒና አባት ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ የኢትዮጵያ ባሕላዊ ሙዚቃ አቀናባሪ በመባል በተለያዩ ቦታዎች ክብር ያገኙ ሲሆን ከንጉሰ ነገስት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ብሄራዊ ሽልማት

የተበረከተላቸው ኢትዮጵያዊም ናቸው:: ፕ/ር አሸናፊ ቅዱስ ያሬድ የሙዚቃ ትምህርት ቤትን አቋቋመው በዳይሬክተርነት መርተዋል:: በአሜሪካ በሚገኙ ታላላቅ የሙዚቃ ዩንቨርሲቲዎችም ውስጥ አስተምረዋል:: ከዚህም ባለፈ በስራዎቻቸው የተለያዩ የክብር ሽልማቶችን ለማግኘት ችለዋል::

ልጃቸውም በፍሎሪዳ የሳቸውን ስም ዳግመኛ እንዲጠራ እያደረገች ትገኛለች:: በ60 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ በሕግ ባለሙያ ልጃቸው ኒና አሸናፊ ዳግም ስማቸው በምድረ አሜሪካ እንዲጠራ ሆነዋል:: የመጀመሪያዋ ኢትዮ - አሜሪካዊት ዳኛ በመሆን ኒና አሸናፊ በኢትዮጵያኖች ዘንድ በአብነት የምትጠቀስ ለመሆን በቅታለች::

# ቢኒያም መሀመድ ወደ ኢትዮጵያ

በአሜሪካ የእስረኞች ማቆያ፣ በጓንታናሞ ከሰባት ዓመት የእስር ቆይታ በኃላ በቅርቡ እንግሊዝ ሀገር የገባው ቢንያም ሞሐመድ ለመጀመሪያ ጊዜ «ሜይል» ለተባ ጋዜጣ በሰጠው ቃለ ምልልስ በሞሮኮ በደረሰበትን የስቃይ ምርመራ የእንግሊዝ ትብብር እንደነበረበት ማስታወቁ ይታወሳል:: በቃለ ምልልሱም ኤም.አይ.5 (የእንግሊዝ ወታደራዊ የመረጃ ተቋም - Military Intelligence Section 5) ለአሜሪካው ሲ.አይ.ኤ. የጥያቄ ዝርዝሮችንና በለንደን የሚኖሩ ሰዎችንና ቦታዎችን የሚያሳዩ ፎቶግራፎችን መስጠቱን የገለጸው ቢንያም «እንግሊዞች የስቃይ ምርመራ እያደረጉብኝ ከነበሩት ሰዎች ጋር መተባበራቸውን ስገነዘብ እጅግ ባዶነት ተሰምቶኛ ነበር::» ብሏል::

ይሁንና የእንግሊዙ ቴሌግራፍ ባለፈው ሣምንት እንደዘገበው ቢንያም ከእንግሊዝ ሀገር መባረር (deport) እንደሚገባው ኮንዘርቫቲቭ ፓርቲው እየገለጸ ነው:: እ.ኤ.አ. በ 1994 እንግሊዝ በመግባት ጥገኝነት ጠይቆ በ 2000 የመኖሪያ ፍቃድ የተሰጠው ቢንያም ለሰባት ዓመት ከሃገር ውጭ በታሰረበት ወቅት የመኖሪያ ፈቃዱ ጊዜው አልፏል ተብሏል:: ቢንያም አሁን በእንግሊዝ እንዲቆይ ጊዜያዊ ፈቃድ ቢሰጠውም በእንግሊዝ ፓርላማ ውስጥ የውጭ ጉዳይ «ሻዶው» ሚኒስትር የሆኑት ዴቪድ ሊንግተን «[ቢንያም] ደረሰብኝ ከሚለው ስቃይ በተናጠል የስደተኝነት ጉዳዩን በተመለከተ ሊነሱ የሚገባቸው ወሳኝ ጥያቄዎች አሉ::» ይላሉ:: «እነኚህ የስቃይ ውንጀላዎች በሚመለከታቸው አካላት በተገቢው ሁኔታ ምርመራ ሊካሄድባቸው እንደሚገባ አምናለሁ:: ነገር ግን በቋሚነት ስለመቆየቱና አለመቆየቱ ጉዳይም አጠያያቂ ነገር አለ::» በማለት ዴቪድ ሊንግተን መናገራቸውን ቴሌግራፍ ዘግቧል::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኢትዮጵያ መንግሥት በመቀየሩ ምክንያት ከኢትዮጵያዊያን የሚቀርቡ የጥገኝነት ጥያቄ ማመልከቻዎች አብዛኛዎቹ ውድቅ የተደረጉ መሆኑን የሚገልጹት ሊንግተን «በእንግሊዝ እንዲቆይ የሚያስችለው ጠንካራ ምክንያት ካለው ሚኒስትሮች በይፋ ለመከራከር ሊዘጋጁበት የሚገባ ጉዳይ ይሆናል::» ብለዋል:: «የቢንያም ሞሐመድ የጤና

ሁኔታን እና ያቀረባቸውን ውንጀላዎች ክብደት ከግምት በማስገባት መንግሥት በአፋጣኝ ወደ የስደተኛነት ጉዳዩ ለምን ሊያመራ እንዳልቻለ ሊገባኝ ይችላል፤ ነገር ግን አሁንም ተንጠልጥለው የቀሩ ጠንካራ ጥቄዎች እንዳሉ አስባለሁ።» ይላሉ ሊንግተን።

በአሁኑ ሰዓት በእንግሊዝ ምዕራብ ዶርሴት የሚገኘው ቢንያም የእንግሊዝ መንግሥት አሳልፎ እንደሰጠውና በደረሰበት ስቃይ ተባባሪ እንደነበር እየወነጀለ ቢሆንም ከየትም ሀገር ይልቅ በእንግሊዝ መኖር እንደሚፈልግ ተናግሯል። «መኖሪያዬ (ቤቴ) ብዬ ልጠራት የምችለው ብቸኛዋ ቦታ ናት» ብሏል ቢንያም - እንግሊዝን።

# የኮካኮላ ምርት መቋረጥን ተከትሎ የለስላሳ መጠጦች እጥረት አጋጠመ

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአቅርቦት ቅሬታዎች በተጠቃሚ ሕብረተሰብ ሲቀርቡበት የነበረው የኮካ ኮላ፣ ስፐራይት፣ ፋንታ ኦሬንጅና ፋንታ አናናስ ለስላሳ መጠጦች አምራች ኢስት አፍሪካን ቦትሊንግ በሀገሪቱ በደረሰው የውጭ ምንዛሬ እጥረት ሳቢያ ባለፈው ሳምንት ሀሙስ ምርቱን ለማቆም ተገዷል። ከዚህ ቀደም ምርቶቹን በመደበኛ ጊዜና በበቂ ቁጥር ለደንበኞቹ ማቅረብ ባለመቻሉ ለተነሱት ቅሬታዎች ፋብሪካው የጥሬ እቃዎች እጥረት እንደገጠመው መግለፁ ይታወሳል።

በኢትዮጵያ የገቢ እና የወጪ ንግድ አለመመጣጠን ምክንያት የተከሰተው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እጥረት የቶርኪ ክዳን፣ ውሁድ ንጥረ ነገሮችንና የተለያዩ መለዋወጫዎችን ከውጭ ሀገር እያስመጣ የለስላሳ መጠጦችን የሚያመርተውን ኢስት አፍሪካን ቦትሊንግ የማምረት እንቅስቃሴውን ለማቆም የመጀመሪያው ቢሆንም በሀገር ውስጥ ብቸኛ ተፎካካሪው ሞሃ የለስላሳ መጠጦች ፋብሪካም ተከታይ ሊሆን እንደሚችል እየተነገረ ነው። ፔፕሲ ኮላ፣ ሰቨንአፕ፣ ሚሪንዳና ሚሪንዳ ቶኒክ የሚያመርተው ሞሃ እስካሁን ድረስ ማምረቱን ባያቆምም በምርቶቹ ላይ ከፍተኛ የአቅርቦት እጥረት እየታየ ነው። ጥሬ እቃዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የሚያስችለውን «ሌተር ኦፍ ክሬዲት» አስቀድሞ በመክፈቱ የኢስት አፍሪካን ቦትሊንግን እጣ አሁን ተካፋይ ባይሆንም የውጭ ምንዛሬ እጥረቱ በዚሁ ከቀጠለ ሞሃም በቀጣይ ወራቶች ከባድ ጊዜ ሊገጥመው እንደሚችል ተገምቷል።

ኢስት አፍሪካን ቦትሊንግ ከሀሙስ ጀምሮ ማምረት ያቆመ ቢሆንም እስከ እሁድ ድረስ በጥቂት የከተማችን መደብሮች፣ ካፍቴሪያዎችና ሆቴሎች የተወሰኑት ምርቶቹ ሲሸጡ መዋላቸው ታውቋል። በተለይ የኮካ ኮላ ለስላሳ መጠጥ ቋሚ ተጠቃሚ የሆኑ ደንበኞች እንደገለፁት ከአቅርቦት እጥረት ምክንያት ከመበደኛ ዋጋው ጨምረው መግዛታቸው ሳያንስ ጭራሹኑ መጥፋቱ አሳስቧቸዋል። ፋብሪካው ምርቱን በማቆሙ ምክንያት የዓመት ፈቃድ

በመስጠት ሰራተኞቹን ለማሰናበት ተገዷል፤ ሆኖም የግዴታ የዓመት ፈቃድ እንዲወስዱ የተደረጉት ሰራተኞች የሙሉ ደሞዝ ክፍያም እንደማይቀርባቸው ታውቋል::

የውጭ ምንዛሬ እጥረት ተፅዕኖ በለስላሳ መጠጦች ላይ መታየቱ ይጉላ እንጂ የጥሬ እቃ ግብዓቶችን ከውጭ ሀገር የሚያስመጡ ማንኛቸውም የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ተጠቂ እንደሚሆኑ ጥርጥር የለውም:: የኢስት አፍሪካን ቦትሊንግ የዳይሬክተሮች ቦርድ ከመደበኛ አጀንዳው የ2008 የስራ ሂደቶችን መገምገም በተጨማሪ የተከሰተውን ችግር በተመለከተም ለመወያየት ዛሬ መጋቢት 8 ፕሮግራም መያዙ ታውቋል::

## መጣጥፎች

# «ሰሞነ ፍስሐ፣ ሰሞነ ህማማት፣ እና ሰሞነ ፍዳ»

አቤ ቶኪቻው
abeto2007@yahoo.com

እንዴት ሰነበቱ ወዳጄ!? ግራ ቀኙ፣ቀዬው፣ሀገሩ ሁሉ አማን ውሎ አድሯል? አማን መሆን ደግ ነው:: ታድያ አማን መሆን እንደው ከመሬት የሚታፈስ ነገር አይደለም:: ትህትና ያስፈልገዋል:: ፀሎት ያስፈልገዋል:: ስለሆነም ቀጣይነት ላለው የአማን ውሎ አዳር ራስዎን በትህትናና በፀሎት ይገንቡ:: (የፆሙ ነገር ግዴታ ስለሆነ ምክር አያስፈልገውም ብዬ ነው::)

ባለፈው ሳምንት ወዳጆቼ ከደረሱኝ ጨዋታዎች ውስጥ «ሰቃይ» የነበረችው ለዛሬ ርዕስ የተደረገችው ነች - «ሰሞነ ፍስሐ፣ ሰሞነ ህማማት፣ እና ሰሞነ ፍዳ»:: ይህ ለአንድ ሙሉ ወር የተሰጠው ክፍልፋይ ስያሜ ነው:: እንሚከተለው ይብራራል:-

ደሞዝዎን ከተቀበሉ በኋላ ያሉት ተከታታይ አስር ቀናት «ሰሞነ ፍስሐ» ናቸው:: ከአስረኛው ቀን እስከ ሃያ ድረስ «ሰሞነ ህማማት» እንዲሁም ከሃያኛው ቀን እስከ ሚቀጥለው ደሞዝ ድረስ ደግሞ «ሰሞነ ፍዳ» ናቸው:: ታድያ እንደየ ሰዉ ጥንቃቄ ይወሰናል:: አልበላም አልጠጣም ታምሜያለሁኝ ብለው ሃኪም ቤት ሳይሔዱ ጥቅልል ብለው ከከረሙ ሰሞነ ፍስሐዎ ረዘም ሊል ይችላል:: (ወጪ አላወጡማ!) የአንዳንዱ ሰው «ሰሞነ ፍስሐ» ከሳምንት በላይ ላይዘል የማለ ነው የሚመስለው:: ደሞዝ ከተቀበለ ከሳምንት በኋላ «ሰሞነ ህማማቱ»ን ይቀበላል:: ለዛውም

«ሰሞነ ህማማት» ላይ ነኝ ለማለት ቢያንስ አበዳሪ መኖር አለበት:: አበዳሪ ከሌለ ወዲያው «ሰሞነ ፍዳ» ውስጥ መግባት ግድ ይላል::

ወዳጄ እርስዎ አሁን የትኛው ሰሞን ላይ ይገኛሉ? ለሁሉም እንኳን አደረስዎ እንባባል እንጂ! እርግጥ ዘንድሮ «ሰሞነ ፍስሐ» ቁጥጥር እንደሚበዛባት ፍቅረኛ አንድ'ፍታ ብቅ ብላ እልም ስትል በህልሜ ነው በእውኔ ያየኋት ታስብላለች:: እና «ሰሞነ ፍስሐ» ላይ ባይሆኑ አይገርመኝም:: እንደ እኔ «ሰሞነ ፍስሐ» የበዛላቸው ወዳጆች በዙሪያዎ ካሉዎትና ከነርሱ አበዳሪነት የተነሳ «ሰሞነ ህማማት» ውስጥ ከኖሩም ተመስገን ነው:: ምንም ምንም በሌለበት «ሰሞነ ፍዳ» ከመኖር ይሻላል::

እኔ የምለው ገንዘቡን እንዲህ በረከት የነሳው ምንድነው? ግሽበቱ ለሽበት ሲዳርገን ሰዎቹም እያዩ ዝም አሉ ማለት ነው? እንደ አንዳንዶች ሃሜት ከሆነ «ሰዎቻችን «በሰሞነ ፍስሐ» ውስጥ ብቻ መኖር ከጀመሩ በርካታ ጊዜ ስለሆናቸው የእኛ «ሰሞነ ህማማት» አያማቸውም የእኛ «ሰሞነ ፍዳ» አይጨንቃቸውም:: ስለዚህ ግሽበቱም ሽበቱም የሚታወቀው ለእኛው ነው» ሲሉ ይደመጣል:: ውይ ይሔስ ጡር መናገር ነው:: ምነው በየ«ህዝባዊ ውይይቱ» ሆነ በየመግለጫው «የኑሮ ውድነቱን ለመቆጣጠር የሚያስችል የተለያየ «ፓኬጅ» እየነደፉልን መሆኑን ነግረውን አይደለም እንዴ? ከዚህ በላይ ምን ያድርጉልን:: የዋጋ ግሽበቱ እኛን እንደ ተርብ ሲነድፈን እነርሱ በጎን ስትራቴጂ ባይነድፉልን ኖሮ አልቆልን አልነበር እንዴ? ተዉ ጎበዝ ጡር አንናገር:: ምንም እንኳን ኑሮው ከእለት እለት የባሰ ቢሆንብንም «ፓኬጅ» ካለች የከፋ ነገር አይገጥመንም::

በድሮ ጊዜ «ሰሞነ ፍስሐ»ን የምናሳልፈው ባንኮኒ ተደግፈን ቀዝቃዛ ቢራ በቀኝ እጃችን፣ የሞቀ ገላ በግራ እጃችን ጨብጠን ነበር:: ዛሬ ግን ይንን ማድረግ «ህማማት»ን ማፋጠን ይሆንብናል እያልን መጨበጡንም ሆነ መጨለጡን ለእነርሱ ትተን (ልብ አድርጉልኝ ስም አልጠቀስኩም) እኛ በጥንቃቄ እየኖርን ነው:: (ችግሩ ጥንቃቄውም የትም አያደርስም::) ሰሞኑን ታድያ የፍስሐ ሰሞኔን እንደ ዋዛ የተቀበልኩበት ሰሞን ነበርና እንደ ድሮው ባንኮኒ ባልደገፍ እንኳን እግር ኳስ ልደግፍ ብዬ በስንት ጊዜዬ የእንግሊዝ ፕሪምየር ሊግ ጨዋታ ለማየት «ዲኤስ ቲቪ» ቤት ታድሜ ነበር:: የእንግሊዝ እግር ኳስ እንደ አምና ካቻምናው ሁሉ ዘንድሮም ብዙ ተመልካች፣ ዘንድሮም ብዙ ደጋፊ አለው:: አንድ ወዳጄ «ይሄ ሁሉ የአግር ኳስ ደጋፊ አረጋውያንን እና ወላጅ አልባ ህፃናትን ቢደግፍ ምን ያህል አመርቂ ውጤት ባስመዘግብን ነበር?» ያለው እውነት ሳይሆን አይቀርም:: ሰዉ ቀላል ይደግፋል እንዴ!? እውነት ግን እኮ በተለይ የወላጅ አልባ ህፃናት ነገር ለአበበች ጎበና ብቻ የሚተው ጉዳይ አይደለም:: (በነገራችን ላይ አበበች ጎበና ከአፍሪካ ምርጥ ሶስት ሴቶች መሀከል አንዷ መሆኗን በመስማቴ የተሰማኝን ደስታ ለመግለፅ

እወዳለሁኝ።) በተለይ ልማታዊ ባለሃብቶቻችን በዚህ ጉዳይ ላይ በመሳተፍ ትጋት እንዲያሳዩ እመክራለሁኝ።

«መስጠት በቁመና ሳሉ በምድር
ተመሬት ሳይገቡ ሳይሆኑ  አፈር»

የሚለውን የየኔ ብጤ ግጥም በማስታወስ የተቸገሩትን መደገፍ ተገቢ ነው። (ወይስ ልማታዊ ባለሃብቶቻችን የየኔ ብጤው ግጥም አይመለከታቸውም?)

እኔ የምለው!? የእኛ ሀገሩ እግር ካ፞ስ ጉዳይ በቃ እንዲህ ጓዳ ጓዳውን ሆኖ ሊቀር ነው እንዴ? እንዴት በሀገሩ አንድ እንካ፞ን «አንተም ተው አንተም ተው» የሚል ሽማግሌ ይጠፋል? ባለፈው ሰሞን እኒያ «መንግሰትን ከተቃዋሚዎች 'ያስታረቁ ሽማግሌዎች' አዲሱን እና የቀድሞውን ፌዴሬሽን ሊያስማሙ ነው» የሚል ዘገባ ሰምተን ነበር። ወድያው ግን «ሽማግሌዎቻችን» እንካ፞ንስ ሌላ ሊያስታርቁ ይቅርና አስታረቅን ያሉት «ሻ፞ ብትን!» ሲል ድምፃቸው አጠፋብን። ዘይገርም ነገር አትሉልኝም?

ስለዚህ እግር ካ፞ሳችን በገንዘብ አበዳሪ ሳይሆን በአስታራቂ ሽማግሌ እጦት «ሰሞነ ፍዳ» ውስጥ ለመኖር ተገዷል። ገንዘቡንማ እግዜር ይስጣቸውና ከ«ሰሞነ ፍስሐ» ውጪ ሌላ የማያውቁት እኒያ የታደሉ ባለሃብት ለአንዱ ግማሽ ሚሊዮን ለሌላው ግማሽ ሚሊዮን  እየሰፈሩ በመስጠት ቀጥ አድርገው ይዘዋቸዋል። የሰውየው ቸሮታ ለእኛዎቹ ብቻ ሳይሆን ሙሉ ምስራቅ አፍሪካ በየአመቱ ለሚያለፋው «ቅሪላ» ስፖንሰር እስከ መሆን የዘለቀ ነው።

ካነሳናቸው አይቀር እኒህ ባለሃብት አለም ሁሉ በኪሳራ ተውጦ ግማሹ «በሰሞነ ህማማት» ግማሹ «በሰሞነ ፍዳ» ውስጥ በሚዳክርበት  በዚህ ጊዜ «የአለም ሃብታሞችን አርባ ሶስተኛ ደረጃን ተቆናጠጡ» የሚል ዜማ (ዜና ማለቴ ነው) በቅርቡ ሰምተናል። በዚህም «ይሁን እሰይ! ምንም እንካ፞ን እኛ ድህነት እየቆነጠጠን ብንሆንም ከመሀከላችን አንድ ደህና ሰው ይህን ደረጃ መቆናጠጡ ለሀገሪቱ ኩራት ነው» እያልን «ሴሌብሬት» እያደረግን ባለበት ወቅት አንድ ወዳጄ «አለም ሁሉ ወደ ድህነት በማምራቱ እኔም በሰፈሬ አርባ ሶስተኛ ደረጃን አላጣም» ሲል የባለ ሃብቱን ደረጃ ለማጣጣል ሞክሯል። እኔና ወዳጆቼ ግን የዚህን ሰው ማጣጣያ እንዳልሰማን በመቁጠር ደስታችንን ባጧጧፍንበት ወቅት ሌላው ወዳጃችንም ከኢንተርኔት አገኘሁኝ ባለው መረጃ «ሰውየው ዜግነታቸውም ሆነ የመኖሪያ አድራሻቸው የተመዘገበው ሳኡዲ አረቢያ በሚል ስለሆነ ፈንጠዝያው በሀገራቸው ቢሆን አይሻልም» ሲል ደስታችን ላይ ውሃ ሊበርዝ ቢሞክርም ከአፍታ ምክር በኋላ «ቢያንስ የምናውቃቸው ሰው በመሆናቸው በስኬታቸው ኩራት ይሰማናል» አልነው። («ኩራት አይሆን እራት» ብሎ መተረት የአገሪቱን መልካም ገፅታ የሚያጎድፍ

ከመሆኑም በላይ በልማታችን ላይ መሳለቅ ስለሚሆን ጋዜጣዊ መግለጫ ያስወጣናል።) እውነት ግን አልገረማችሁም? ሰውየው ከዘጠና ሰባተኛ ወደ አርባ ሶስተኛ በአንድ ጊዜ ይሔንን ሁሉ እድገት ማስመዝገብ መታደል ነው። በዚህ አይነት የሀገራችን ኢኮኖሚ አስራ አንድ ነጥብ ሁለት በመቶ ብቻ ሳይሆን መቶ አንድ ነጥብ ሁለት በመቶም ቢያድግ ሲያንሰው ነው።

<u>በመጨረሻም፡-</u> አንድ ወዳጄ «ፀሀዩ መንግስታችንን «The Vitamin D Government» ብንለውስ አይሆንም ወይ?» ያሉኝ በበኩሌ ተስማምቶኝ ነበር፤ግን ሰዎችን ሳማክር «Vitamin D» የጠዋት ፀሀይ ብቻ ስለሆነ ከ«ሰሞነ ፍስሐ» እስከ «ሰሞነ ፍዳ» ቀጥ አድርጎ የያዘንን መንግስታችንን ውለታ ማኮሰስ ይሆንብናል። ለምን የጠዋት ፀሀይ ብቻ? የተሲያቱን ፀሀይ ማን ሊሆን ነው? የማታውንስ? የሚል አስተያየት ሰጥተዋል።

ለዛሬ እንዲህ ይብቃን ወዳጄ። «ሰሞነ ፍስሐ»ዎን ያብዛልዎ!

አማን ያሰንብተን!

# የይቅርታ አዋጁ ሲፈተሽ

**በወንድይራድ ደብረጽዮን**

ከሕግ ልዩ ባህሪያት ማህል አንዱ ጥቅል ይዘት ያለው መሆኑ ነው። ሕግ ለአንድ ሰው አይወጣም። እንዲህ አይነቱ መርህ ጠቀሜታው ለተወሰኑ ፍላጎቶች እና አላማዎች ብቻ ህግ እያወጣን መልካም የህዝብን የአኗኗር ብሂል ሳንካ እንዳንፈጥርበት ዋስትና ይሆን ዘንድ አለማዊውንም መንፈሳዊውን ሂወት አጣቅሰው የህግ መቀመሪያዎች «አንድ ህግ አጠቃላይ ይዘት መያዝ አለበት። የሚለውን መርህ አስቀምጠዋል!! ከዚህ መርህ ውጭ የሆኑ ህጎች ተፈጻሚነታቸው እና ጉዟቸው ደካማ ይሆናል» ግለሰቦችን እና «ጥቂት ፍላጎቶችን » እያለምን ህጎችን የምናረቅ ከሆነ ዞሮ ዞሮ ለእያንዳንዱ ህዝብ እና ቡድን መተዳደሪያ የሚሆን ህግ ማውጣት ስለሚጠበቅብን ብዙ ግዚያችንን ሌላ ስራዎችን ትተን ህግ ስንጽፍ እና ስናጸድቅ መኖራችን ሊሆን ይችላል። በመርህ ደረጃ በእንደዚህ ዓይነት መንፈስ የሚወጡ ህጎችም በመርህ ቢሆኑ የህግን ፍልስፍና መሠረት አድርገው የተጻነሱ ባለመሆናቸው «ህግ» ብለን ልንጠራቸውም የሚያስችል ወኔው ያጥረናል።

ከዚህ ባለፈ ሆነው አጠቃላይ ማህበረሰቡን ወይም በተወሰነ መልኩ የገዘፈ ማንነት ያላቸው የማህበረሰብ ቡድኖችን ለማስተዳደር የወጡ ህጎች ከሆኑ ግን የቱንም ያህል ጠንካራ ይሁኑ ልፍስፍስ የራሳቸውን ህግ ሟሟላት ከሚጠበቅበት መሠረታዊ መርሆች ማህል ዋንኛው በማሟላታቸው እንደ ህግ ተቆጥረው አወዛጋቢ ገጽታቸው ደግሞ ለውይይት ቀርቦ የክርክር አንዱ አካል ሆኖ ይቀጥላል:: ከህገ መንግሥቱ አንስቶ እስከ አንድ አነስተኛ መመሪያ ድረስ ያሉ የህግ ድክመቶች እያነሱ መከራከር እና መወዛገብ ብሎም ወደ ህግ ተርጓሚው ዘንድ ቀርቦም ክርክሩ እልባት እንዲያገኝ መሟገት ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ገጽታዎች ማህል አንዱ ነው:: አንድ መደብ ዘለን ስንራመድ ወይም የወጣው ህግ በአግባቡ በአስፈጻሚ አካል እና ህጉ በተፈጸመበት ወገን በኩል ክርክር ቢነሳ እና ክርክሩ ተጠናክሮ ቢቀጥል ዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መሠረቱ ጠንካራ የሚያደርግ እና ሀሳብን የመግለጽ መብት የአፈጻጸም ደረጃውን ወደ ጥሩ ምዕራፍ መሸጋገሩን በአስረጂነት ልናስቀምጠው የምንችለው ነው:: ይህ በሚሆንበት ወቅት ሀሳብን የመግለጽ ነፃነት ከመብትነት ባሻገር የማህበረሰቡ ሱስ ሆኗል ብሎም ለመደምደም የሚያስችል አጋጣሚ ነው::

ከላይ በመንደርደሪያነት የቀረቡት እሳቢዎች በተለያየ መንገድ ከወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ መታሰር ጋር በተያያዘ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ሲነሱ ተስተውለዋል:: የወ/ሪት ብርቱካን መታሰር ምክንያት ተደርጎ እየተገለጸ ያለው «ይቅርታ አልጠየኩም» ብለዋል የሚል እንደሆነም እየተገለጸ ይገኛል:: መንግሥትም ሆነ የወ/ሪት ብርቱካን መታሰር የሚቃመው ወገኖች የየራሳቸውን መከራከሪያ እያቀረቡ ይገኛሉ:: ሁለት የመከራከሪያ መስመሮችን ያሰመሩት መንግሥት እና የመንግሥት እርምጃ የሚቃወሙ አካላት የራሳቸውን መከራከሪያ አቅርበዋል:: መከራከሪያዎቹን መዝኖ ወደ አንድ ጭብጥ ለመድረስ ግን ወ/ሪት ብርቱካን ቃሌ ብለው ያስተላለፉትን መልዕክት፣የይቅርታ ሥነ - ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 395/1996 የይቅርታ አጠያየቅ ሂደቶች እና የቅንጅት ይቅርታ አጠያየቅ ገጽታቸው፣በቅንጅት አመራሮች ከእስር አፈታት ሂደት ውስጥ የሽማግሌዎች ሚናን እና የመሳሰሉትን በማጤን አጠቃላይ የውዝግብ መነሻ እና መዳረሻው ብንመረምር የተሻለ ነው::

በአዋጅ ቁጥር 395/1996 መሰረት የይቅርታ ዓላማው «የሕዝብን ደህንነትና ጥቅም ለማስከበር» እንደሆነ በአንቀጽ 11 ላይ ይደነግጋል:: ይህ ማለት አንድ ሰው «ይቅርታ ይደረግልኝ ተጸጽቻለሁ» ብሎ «ድንጋይ ተሸክሞ ስለጠየቀ» ብቻ ሳይሆን የይቅርታ ጠያቂ ይቅርታ ቢደረግለት ለህዝብ ደህንነትና ጥቅም ለማስከበር የሚኖረው አስተዋጽኦ ምንድን ነው? ለሚለው በቅድሚያ ምላሽ ሊሠጠው ይገባል:: የይቅርታ ዓላማ ይህ ከሆነ ይቅርታ ለይቅርታ ጠያቂው ይሰጠዋል የሚለውን የሥር - ሥርዓት ጥያቄ ከወ/ት ብርቱካን የይቅርታ ጥያቄ ሂደት ጋር በመገናኘት እንመልከት::

የይቅርታ ጥያቄ ማለት በአዋጁ መሠረት አንድ ፍርድ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን ወይም የቅጣቱ አፈጻጸምና ዓይነት በቀላል ሁኔታ እንዲፈጸም የሚቀርብ ጥያቄ እንደሆነ ያስቀምጣል:: እንዲህ አይነቱን ይቅርታ የሚሰጡት በቦርዱ አቅራቢነት የሪፐብሊኳ ርዕሰ ብሄር

(ፕሬዝዳንቱ) ናቸው:: በቅድመ ሁኔታ ይቅርታ ተደርጎላቸው ቅድመ ሁኔታውን ያላሟሉትን ወይም የጣሱትን በተመለከተ ከቦርድ የሚቀርብለትን የውሳኔ ሐሳብ መሠረት በማድረግ ይቅርታውን ለመሰረዝ ይችላል:: በዚህም መሠረት ይቅርታ ሰጭውም ሆነ ነሺው በፕሬዝዳንቱ መልካም ፈቃድ ላይ የተመረኮዘ እንደሆነ ተቀምጧል::

ከዚህ ሁኔታ ለመረዳት የሚቻለው በይቅርታ ሂደት ውስጥ ሁለት ወገኖች እንዳሉ ነው:: ይቅርታ ጠያቂና ይቅርታ ሰጭ ማለት ነው:: ምናልባት ይቅርታ ጠያቂን የሚወክል በህጉ መሠረት በተደነገገው መልኩ ሦስተኛ ወገን ካልተደመረ በቀር በይቅርታ ጠያቂና በይቅርታ ፈቃጅ መሐል የሚኖር ጉልህ ፍላጎት ያለው አካል የለም:: ስለዚህ በቅንጅት አመራሮች እና በመንግሥት ማህል ሆነው ከእስር ቤት ወደ ቤተመንግሥት ከቤተመንግሥት ወደ እስር ቤት ሲመላለሱ የነበሩት ሽማግሌዎች የነበራው ሚና ምን ነበር ? የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነው::

ስለ ይቅርታው ጥያቄ አቀራረብ የይቅርታ አዋጁ በአንቀጽ 12 ላይ በዝርዝር ያስቀምጠዋል በዚሁ አንቀጽ አንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) እንደሚከተለው ይነበባል::

1. «በወንጀል ጉዳይ ላይ በፍርድ ቤት ተከሶ የመጨረሻ ፍርድ የተፈረደበት ማንኛውም ሰው የተወሰነው ፍርድ በህግ ይቅርታ የሚያስከለክል ካልሆነ በቀር <u>የይቅርታ ጥያቄውን ራሱ ወይም በባለቤቱ፣በቅርብ ዘመዶቹ፣ወኪሉ ወይም ጠበቃው አማካኝነት ማቅረብ ይችላል</u>»
2. «ከዚህ በላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ <u>የፍትህ ሚ/ር ለፌደራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ይቅርታ ሊደረግላቸው የሚገባቸውን ሰዎች በመምረጥ በበኩላው የይቅርታ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ</u>:: መስሪያ ቤቶች የይቅርታ ጥያቄ ለማቅረብ የወሰኑ እንደሆነ የይቅርታ ጠያቂው ደብዳቤ ቅጂ ይቅርታ ለተጠየቀለት ሰው እንዲደርሰው ማድረግ ይኖርባቸዋል» ይላል:: የተሰመረባቸውን ሀረጎች ስናይ ይቅርታ የሚጠይቀው (የሚጠየቅለት) ፍርደኛ የይቅርታውን ጥያቄ አቀራረብ በምን መልኩ እንደሚሆን ያሳየናል:: ከዚህም ባለፈ ይቅርታውን የሚያገኘው ሰው ሙሉ ፍላጎት እንዳለው ይገልጻል:: በማንኛውም መንገድ በአዋጁ መሠረት በሌላ ወገን ይቅርታ ቢጠየቅለትም እንኳን ይቅርታው የሚፈጸምበት «ፍርደኛ ሰው» ይሁንታውን ለይቅርታው እንዲሰጥ የሚፈቅድ ሥነ - ሥርዓት በዓዋጁ ተስቷል::

ከእነዚህ እውነታዎች አንጻር ሽማግሌዎች ይቅርታ ለአንድ ሰውም ሆነ ይቅርታ ጠያቂዎች ለፕሬዝዳንቱም ሆነ ለቦርዱ ይቅርታ ለመጠየቅ ህጋዊ ሰውነት እንዳልተላበሱ ለመረዳት ይቻለል ብሎ መከራከሪያ ማቅረብ ይቻላል:: ምክንያቱም በህጉ መሠረት አንድ ፍርደኛ ይቅርታ እንዲያገኝ የመጠበቅ ህጋዊ መብት የተሰጣቸው ይቅርታው ይገባኛል የሚል ፍርደኛ ወይም ባለቤቱ፣በቅርብ ዘመዶቹ ወኪሉ ወይም ጠበቃው እንደሆነ እና ከላይ ያለው እንዳለ ሆኖ በፍትህ ሚ/ር የፌደራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን አማካይነት እንደሆነ በአዋጁ ተቀምጧል:: የአገር ሽማግሌ ፍርደኛን በይቅርታ እንዲፈታ የሚያደርግበት የሕግ አግባብ የለም:: (ወይም

በሌላ አገላለጽ ሽማግሌዎች ፍርደኞችን ወክለው ይቅርታ የመጠየቅ ፈቃድ በአዋጁ አልተሰጣቸውም) ከህግም ማእቀፍ ውጭ ሆነን ከሆነ ግን የሚቻልበት የባህል እና የልምድ አካሄዶች ተግባራዊ አድርገን «ይቅር ለእግዚአብሄር» ማስባባል የሽማግሌዎች አይነተኛ ሚና ነው፡፡

በ395/1996 ዓ.ም የይቅርታው ሥነ - ሥርዓት አዋጁ መሠረት የአንድ ይቅርታ የሥነ - ሥርዓት መሟላት ያለበት መቼ ይቅርታ መጠየቅ እንደሚቻል በተቀመጠው ነው፡፡ በአዋጁ ትርጓሜ ላይ «ይቅርታ ጠያቂን» ይቅርታ የተጠየቀበት ፍርድ ለሚመለከተው ሰው ሲሆን ግብረ አበሮቹንም እንደሚያካትት ይገልጻል፡፡ «የይቅርታ ጥያቄ» ማለት አንድ ፍርድ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን ወይም በቅጣቱ አፈጻጸምና አይነት በቀላል ሁኔታ እንዲፈጸም የሚቀርብ ጥያቄ ነው ሲል ይተረጉመዋል፡፡

በተጨማሪ በአዋጁ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀፅ አንድ ዳግም የይቅርታ ጥያቄውን «ፍርዱ ከሰጠ በኋላ በማንኛውም ጊዜ» ማቅረብ እንደሚቻል ይደነግጋል፡፡ ከዚህ የአዋጁ ድንጋጌዎች የምንረዳው ይቅርታ የሚጠይቀው አካል ፍርደኛ መሆኑን እና የይቅርታ ጥቄውንም ፍርድ ከተላለፈበት በኋላ አንድ ፍርድ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን ወይም የቅጣቱ አፈፃፀምና ዓይነት በቀላል ሁኔታ እንዲፈፀምለት ነው፡፡ ከእነዚህ ሁሉ ግን መሠረታዊ የሆነው ይቅርታ ጠያቂው የይቅርታ ጥያቄውን የሚያቀረበው ፍርዱ አልቆ ፍርድ ቤት የጣለበትን ቅጣት በእሱ ላይ ተፈፃሚ እንዳይሆንበት ነው፡፡ ወደ ቅንጅት አመራሮች ስንመጣ ይቅርታ ጠየቁበት የሚባለው ሰነድ ከእስረኞቹ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተላከው ጉዳዩን የያዘው በከፍተኛ ፍርድ ቤት የ2ኛ ወንጀል ችሎት ውሳኔ ሳይሰጥ እና ተከሳሾቹም ፍርደኛ ሳይሆኑ ነው፡፡በሌላ አገላለፅ "ይቅርታ ጠያቂ" የሚያያስብላቸውን ሰርተፍኬት ሳያገኙ ነው፡፡ የቅንጅት አመራሮች ከእስር ቤት ወደ ጠቅላይ ሚንስትሩ «በሽማግሌዎች» አማካኝነት የላኩት ሰነድ የተፃፈው በሰኔ 15/1999 ሲሆን ፍርድ ቤቱ የቅጣት ውሳኔን የተላለፈው (ፍርደኞች የሆኑበት ቀን) ሐምሌ 9/1999 ነበር፡፡ (በመካከላቸው የአንድ ወር ልዩነት አለ) ይህ ማለት ይቅርታ ሰጪውም ሆነ ይቅርታ ጠያቂው ጉዳዩ ለይቅርታ አቅመ አዳም ወይም ሄዋን ሳይደርስ ነው ይቅርታ ሰጪ እና ይቅርታ ተቀባይ የሆኑት ማለት ነው፡፡

ከላይ አዋጁን ተንተርሰን ስለይቅርታ ጥያቄ አቀራረብ መቼ መቅረብ እንደሚችል ተመልክተን በመቀጠል የይቅርታ ጥያቄው ማመልከቻ መያዝ ያለበት ዝርዝር ነገሮችን ከቅንጅት አመራሮች የይቅርታ ሰነድ ጋር እያወዳደርን እንመላከት፡፡ በይቅርታ አሠጣጥ ስነ-ስርዓት ላይ የይቅርታ ጥያቂን በተመለከተ የተለያዩ መረጃዎች ማካተት እንዳለበት አዋጁ በአንቀፅ 13 ላይ ያስቀምጣል፡፡

በዚህ አንቀፅ መሠረት የይቅርታ ጉዳዮችን አስፈፃሚ የሆነው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሪፐብሊክ በፍትህ ሚኒስትር የይቅርታ ቦርድ ፅ/ቤት ሶስት የተለያዩ ቅፆችን አዘጋጅቷል፡፡

ቅፅ አንድ «የይቅርታ ጠየቂ ማመልከቻ» ሲሆን ወደ ስድስት ገፅ የሚጠጋ የይቅርታ ጠያቂውን ዝርዝር መረጃ በራሱ ወይም በአዋጁ መሰረት ለይቅርታ ጠያቂው ይቅርታውን ሲጠይቅ የሚያስፈልጉት መጠይቆች ያካተተ ነው፡፡

ቅፅ ሁለት ደግሞ «የይቅርታን ጥያቄ በመደገፍ የተሰጠ መስክርነት» የሚሞላበት የምስክርነት ቃል የሚሰጥበት ሰነድ ነው፡፡ ይህ ቅፅ አራት ገፅ ሲኖሩት ወደ ዘጠን የሚጠጉ ይቅርታ ጠያቂው ይቅርታ እንዲሰጥ የሚፈልጉ የተፈጥሮ ሰው፣ማህበር ወይም ተቋም ምክንያታቸውን የሚተነትኑበት ነው፡፡

ቅፅ ሶስት ደግሞ በይቅርታ ሂደቱ ላይ የማረሚያ ቤቱ አስተያየት የሚሞላበት ነው፡፡

እነዚህ በቅፅ በቅፅ ተከፋፍለው የተቀመጡት የይቅርታ መጠየቂያ ሰነዶች በአዋጁ አንቀፅ 13 ላይ በተለይ (shall) በማለት መካተት አለባቸው ብሎ የዘረዘራቸው የይቅርታ ጠያቂው መረጃዎች ሳይካተቱ እንዳይቀሩ በማመን ይመስላል፡፡ ቦርዱ እንደመመሪያ የቀረፃቸው የሚል ግንዛቤ አለ፡፡ የቅንጅት አመራሮች ግን ወደ ጠቅላይ ሚንስትሩ የላኩት ሰነድ እነዚህ በቦርዱ የተዘጋጀውን ሶስት ቅፆችን መሠረት ያደረገ እንዳልነበር ግልፅ ነው፡፡ በወቅቱ ይቅርታ ጠይቀውበታል ተብሎ በመንግስት ሚዲያዎች የተመለከትነውና በጋዜጦች ታትሞ ያየነው በግማሽ ገፅ ላይ ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተፃፈ ደብዳቤ ነበርና ከሁኔታው የምንረዳው የይቅርታ ጉዳይ በአዋጁ መሠረት እንዳልተፈጸመ ነው፡፡

ስለዚህ ወ/ት ብርቱካን ቃሌ ብለው በፃፉት የመከራከሪያ ሀሳባቸው ላይ ስለሂደቱ ያነሱት የመከራከሪያ ሀሳብ ላይ ከህግ የቴክኒክ መመዘኛ አንፃር ተጨባጭ እውነታዎች ያነሳል፡፡ በግልፅ ሀሳባቸውን የመግለፅ መብታቸውን በተወሰነ ደረጃ ተጠቅመዋል፡፡ በተለይ የይቅርታ አዋጁን መሠረት አድርገን ከተወያየን መንግስት ይቅርታን ሠጥቻለሁ ሊያስብል የሚችል የሥነ-ሥርዓት ሂደት አንስቶ ለመከራከር የሚያስችል እውነታዎችን አንስቶ ለመከራከር ማስረጃዎች ለማቅረብ እንብዛም የሚያስችል አይመስለኝም፡፡

## <u>ይቅርታን ስለመሰረዝ እና የወ/ት ብርቱካን ይቅርታ ቀሪ መሆን</u>

የይቅርታው ሂደት የይቅርታ ሥነ-ሥርዓቱን አዋጅ 395/1996 መሠረት አድርገን የቱንም ያህል ህጉን ጠብቆ ባይሄድም ይቅርታው ይቅርታ እንደሆነ ተቀብለን በማየት ይቅርታው በአዋጁ እንዴት ሊሠረዝ እንደሚችል እና የወ/ት ብርቱካን "ይቅርታ" ቀሪ መሆን እንመልከት፡፡

በአዋጁ አንቀፅ 16 መሰረት ይቅርታ ሊሰረዝባቸው የሚችሉበት አግባቦች ተቀምጠዋል፡፡ በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ሁለት ላይ «ይቅርታ ውሳኔ ለይቅርታ ተባዩ ከደረሰና ተቀባይነት ካገኘ በኋላ <u>የይቅርታ ውሳኔ በማጭበርበር ወይም በማታለል የተገኘ መሆኑ ስለተረጋገጠ</u> የይቅርታ ውሳኔው ዋጋ አይኖረውም» ይላል፡፡ ንዑስ አንቀፅ ሶስት ደግሞ በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ይቅርታ ቅድመ ሁኔታው መጣሱ ስለተረጋገጠ የይቅርታ ውሳኔው ዋጋ

አይኖረውም ይላል:: ከእነዚህ የህግ አግባብ ውጪ ሲሆን ይቅር ተባይ የይቅርታ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ወደነበረው ቦታ እንዲመለስ በቦርዱ መብት ያገኛል::

በአንቀፅ 16 ንዑስ አንቀፅ 2 ላይ «የይቅርታ ውሳኔ በማጭበርበር ወይም በማታለል የተገኘ መሆኑ ስለተረጋገጠ የይቅርታ ውሳኔው ዋጋ አይኖረውም..» የሚል ነጥብ አለ:: ከመንግስትም በኩል የወ/ት ብርቱካን ይቅርታ መነሳት ተጭበርብሮ ወይም በማታለል የተሰጠ ስለሆነ አንስተነዋል የሚል መከራከሪያ ይቀርባል:: ለመሆኑ በአዋጁ መሰረት ተጭበረበረ ወይም ማታለል ተፈፀመ ልንል የሚያስችለን ምንድን ነው? ለዚህ ምላሹ ይቅርታ የተሰጠው ሰው በህግ ይቅርታ የማያሰጠው ሆኖ ሳለ ይቅርታ ሲያገኝ (አንቀፅ 12) ይቅርታ ጠያቂው በአዋጁ አንቀፅ 13 መሠረት ለይቅርታ ጥያቄው ማመልከቻ ያቀረበበት ቅፅ ላይ ሀሰተኛ መረጃ ካስቀመጠ እንደሚሆን ግልፅ ነው:: ከዚህ አንፃር ወ/ሪት ብርቱካን ያጭበረበሩት ምንድን ነው? መንግስት ይቅርታ ጠይቀዋል ያላቸውን ሰነድ መፈራረማቸውን ቃሌ ብለው ባስነበቡት ቃላቸው አስምረውበት ተናገረዋል::ይቅርታ ጥያቄ ማመልከቻቸውን ለመንግስት ሲያቀርቡ በአዋጁ አንቀፅ 13 መሠረት ያስቀመጡ ባለመሆናቸው ከማመለከቻ ጋር በተያያዘ ተጭበርብሯል ብለን የምናነሳው ነጥብ ያለ አይመስለኝም:: ተጭበርበሯል ብለን ካልን የተጭበረበረው ነጥብ በዚህ ጉዳይ ላይ ህጉ ሊያስረዳን አይቻለውም:: ምናልባት ይህንን ማስረዳት የሚችለው መከራከሪያውን ያነሳው አካል ብቻ ነው:: በሂደት ውስጥ በይቅርታ ጠያቂው ሊጭበረበር የሚችለው ስለ ይቅርታ የፈረመው ሰነድ ውስጥ ሐሰተኛ ነገር ከሞላ እና ይቅርታ ሊሰጠው ሳይገባ ይቅርታ ከተሰጠው ነው::

ከዚህም ስናልፍ ማጭበርበር እና ማታለል መፈጸሙን ምስክርነት የሚሠጠው ማን ነው? ማጭበርበር እና ማታለል መፈፀሙን መወሰን ሥልጣን ያለው አስፈጻሚው አካል ነው:: ወይስ ፍርድ ተርጓሚው? ማጭበርበር እና ማታለል ላይ የመዳኘት ሥልጣን ያለው የወንጀል ፍርድ ቤት ነው? ወይስ አስፈጻሚው? ይቅርታውን በማጭበርበር መገኘቱን በፍርድ ቤት ለዳኝነት አረጋግጠን ነው መጭበርበሩን የምናስወስነው? ወይስ ቦርዱ «ተጭበርብሯል» ብሎ በቀጥታ እርምጃ ይወስዳል? እነዚህ በራሳቸው ምላሽ የሚያስፈልጋቸው ናቸው::

# የማይነበብ

ያው እንደነገርኳችሁ ባቅላባ እወዳለሁ:: እናም በቀደም ውል ሲልብኝ አንድ ጓደኛዬን ደውዬ ፒያሳ ተቃጠርኩት:: እንደናንተ ባልሆንም የማንበብም (የወሬም) ሱስ ስላለብኝ የቀኑን ጋዜጦች ከጓደኛዬ ጋር ሆኜ ሳገላብጥ የአገራችን ቁጥር አንድ ባለሀብት በዓለም ደረጃ የሀብታምነት ደረጃቸው ወደ ላይ መመንጠቁን ተረዳሁ:: ነገር ግን እኚህ የተከበሩ ሰው የሀብት

መጠናቸው ጨምሮ ሳይሆን ሌሎች ይበልጧቸው የነበሩ የዓለም ቱጃሮች ሀብታቸው አሽቆልቁሎ መሆኑን ያነበበው ጓደኛዬ ድንገት ቀና ብሎ ለግንባታ ሲባል በሰማያዊ (ከፊሉ ነጣ ባለ ቀለም ተቀይሯል) የቆርቆሮ አጥር ተከልሎ የኖረውን ቦታ ተመለከተና ፈገግ አለ:: «የሀብታቸው መጠን እነደዚህ ግንባታ ባለበት ቆሟል» አለኝ እንደመጣለት የሚያወራው፣ የበላበትን ወንጭፍ ሰባሪ ጓዴ::

እኔ ግን ያንን የፒያሳ ሰማያዊ አጥር ግቢ ስመለከት ሁሌም የሚያሳስበኝ የዚያ እንደሰገነት የተተከለው የዕቃ ማውጫና ማውረጃ የክሬኑ ጉዳይ ነው:: (ለኮንስትራክሽን ሙያ ቅርበት ስለሌለኝ ቀጥተኛ መጠሪያውን አላውቀውም::) እዚያ ቦታ ላይ ተተክሎ ለረጅም ጊዜ በመቆየቱ (መቼም ብረት ነውና) ቢዝግና ቢወድቅስ? የሴጣን ጆሮ ይደፈንና በቦታው የሚገኙ ታክሲዎች፣ተሳፋሪዎች፣ተራ አስከባሪዎች፣የአዲስ አበባ መስተዳደር ሠራተኞች፣የባህል አዳራሹ ቲዓትር ተመልካቾች እና የመሳሰሉት እንደወጡ ቀሩ ሊባልም አይደል!? ግንባታው እንኳ ቢዘገይ (የዓለም ኢኮኖሚ እስኪረጋጋ) የሆነ ፀረ-ዝገት ነገር ቢቀባ መልካም ነው:: ማለቴ ለአጥሩ የሚደረግለት የቀለም እንክብካቤ ለክሬኑም ቢደርሰው ብዬ ነው::

መቼም «አታንብቡ እየተባላችሁ ለምን ታነባላችሁ?» እያልኩኝ መጨቃጨቁ ስለመረረኝ እንደማታነቡት አድርጌ ወጌን ልገንባ:: «የታክሲ ሾፌሮች እና የትራፊክ ፖሊሶች ፍቅር ምን ያህል ነው?» በሚል ርዕስ ጉዳይ መጽሐፍ፣ ፊልም፣ ... ፣ እንዲሁም ዜና ሁሉ የሚሰራ ሰው እጅጉን አትራፊ እንደሚሆን አትጠራጠሩ:: ይህን ለማረጋገጥ ደግሞ ጋቢና ተቀምጦ ለታክሲ ሾፌሩ ስለ ትራፊክ ፖሊስ አንስቶ «ማኖ» ማስነካት በቂ ነው:: ከዚያማ እስከዛሬ የደረሰበትን የትራፊክ ቅጣት ብሶት በተለያዩ አስቂኝ የወግ ዘዴዎች አብሶ ይዘከዝክላችኋል:: ሆኖም እንደዚያ በዘለፋና በወቀሳ አጅቦ ለትራፊክ ፖሊሶች ያለውን ጥላቻ ሲዘከዝክላችሁ የነበረው ሾፌር በድንገት አንድ ትራፊክ ፖሊስ ፊሽካውን አሰምቶ «ጥግ ይዘህ ቁም» ሲለውና አጠገቡ መጥቶ ሰላምታ በመስጠት መንጃ ፈቃድ ሲጠይቀው «አቤት ጌታዬ ... ምን አጠፋሁ» በማለት የክብርና የፍቅር ፈገግታውን ያሳያል - ጥፋቱን ያውቀዋላ:: ብቻ ፍቅራቸው ያስገርማል:: በቀደም እንደለመደብኝ ጋቢና ቁጭ ብዬ አንድ የታክሲ ሾፌር የትራፊክ ፖሊስን እያማልኝ ሳለ በአጋጣሚ መስቀለኛ መንገድ ላይ  የመኪና ታርጋዎች የያዘ የትራፊክ ፖሊስ አየና «እይ እስኪ፣ «ቆርቆሮ ያሌው» እንኳን እንዲህ አይሸቅልም'ኮ» ሲለኝ ልቤ እስኪፈነዳ ነበር የሳኩት:: የዚያን ዕለት ብዙ ነገሮች ሰምቼ የነበረ ቢሆንም ከዚህ በላይ ካልኩኝ ወገንተኛ ያስብለኛል::

የሆነው ሆኖ በሠራተኛ ቅጥር ጉዳይ ላይ ሁሌም የሚያሳስኝ ነገር አለ:: በመንግሥት መስሪያ ቤቶች ዘንድ ብሔር፣ፆታ፣ከዚህ ቀደም የተሳተፉባቸው ማህበራት ካሉ ይጥቀሱ፣እና የመሳሰሉት መስፈርቶችን እመለከታለሁ:: በእርግጥ የፆታ ነገር ሕገ መንግሥቱም ለሴቶቻችን የድጋፍ እርምጃ /affirmative measures/ ይወስድላቸው ዘንድ ያዛል:: ሰሞኑን ግን አስቂኝ መስፈርት ያዘለ የሥራ ማስታወቂያ ተመልክቼ ሊያስቀኝ ሲገባ አስገርሞኛል:: ከሥራ ማስታወቂያው በስተመጨረሻ «አመልካቾች ከጫት ሱስ የፀዱ መሆን አለባቸው» ይላል:: ይህንን ማስታወቂያ ያወጣው የመንግሥት መስሪያ ቤት አይደለም፣ የግል ፕሬስ ድርጅት ነው::

እስኪ አስቡት አንድ ተቀጣሪ በሥራ ሰዓቱ ጫት ካልቃመና የሚጠበቅበትን ካከናወነ ከሥራ ሰዓቱ ውጪ ግን በተጠመደበት በየትኛውም ሱስ ቢዘፈቅ ለቀጣሪው ምኑ ነው!? (ጫት መቃምን እያበረታታሁ እንዳልሆነ ይታወቅልኝ::) ደግሞስ መንግሥት ጠቀሜታውን አክብሮ ቴምብር የሰየመለትን፣አምራቾቹንና ነጋዴዎቹን የሸለመለትን የኢኮኖሚያችን ዋልታ የመሆን አቅም ያለውን ጫት ባበረታታስ ምን ይገርማል:: ሆነም ቀረ በዚህ የስራ ማስታወቂያ ለማይቅሙ ሰዎች በተዘዋዋሪ የድጋፍ እርምጃ እየተወሰደላቸው ነው:: ያም ሆኖ ግን ጥቂት ጥያቄዎች አሉኝ:- አንድ አመልካች የጫት ሱሰኛ ስለመሆኑ በምን ይረጋገጣል? ሱስ ምን ማለት ነው? ከጫት ሱስ የፀዳ ሲባልስ-ምን ያህል የፀዳ? ወይስ የአምራምባ ታይምስ ጋዜጣ አምደኛ አቤ ቶክቻው ባለፈው ሳምንት እንዳለው፣ የሥራ ማስታወቂያው «ስክሪን ሴቨር» ነውን?

«ሱሴ» የሚለው የአብነት አጎናፍር ሙዚቃ አይመቻችሁም? መልሱን አልፈልግም:: ለማንኛውም መልካም ሳምንት ሱሶቼ::

# ተቃዋሚ ታዳጊም (Rescuer) ሊሆን መቻሉም ሲታይ!

***ከመርዓዊ ሚጌሶ***

በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ተቃዋሚነት የዲሞክራሲው የዕድገት መሳሪያ ነው:: ተቃዋሚ በመሰረቱ ስህተት ፈላጊ ሳይሆን (ስህተት ፈላጊ ባለጋራ ነው) ከትክክለኛ መርህ አንፃር መኬድ ያለበት በዚህኛው አግባብ እንጂ በያዝከው አግባብ አይደለም! በማለት በአማራጭ መንገድ በህቅ የሚሞግትና የሚፋለም ነው:: የተቃዋሚውም ሆነ የገዥው ፓርቲ ዓላማ ከሀገር ጥቅም አንፃር ከሚሰራ ዓላማ አኳያ መነሳት ያለበት መሆኑ አያከራክርም:: ስለሆነም ለሀገሩ ጥቅም የሚያመጣው አግባብ ይኸ እንጂ ያኛው አይደለም፣በመባባል እስከመተማመን ደረጃ መድረስ አለባቸው እንጂ አንዱ ሌላውን የመወንጀል ዓላማን ሥራዬ ብለው ሊተጉበት አይገባም::

የአገሩን የሰውና የተፈጥሮ ሀብት ያለእድልዎ ሥራ ላይ ሊያውል ለሚችል አስተሳሰብ እቅድ አለኝ በሚል መጀመር ከገዢም ሆነ ከተቃዋሚ ፓርቲ የሚጠበቅ መሆኑ የታወቀ ነገር ነው:: በዚህ ሂደትም ገዥው ፓርቲ በተቃዋሚው ይበጃል፣ የተባለውን ሀሳብ አሳማኝነት

እንዳለው በቅንነት ካስተዋለ በዚያ አቅጣጫ አካሄዱን ማስተካከል አለበት፤ተቃዋሚውም ፓርቲ እንደዚሁ ይህ አቋምህ ጥሩ ነው! የራሴን ባንተ ልተካው እስማማለሁ ማለት መቻል አለበት:: ለዚህ ታዲያ የህሊና ንፅህና ቀናነት ያስፈልጋል:: ሀሳቡን ማንም ያምጣው መመዘኛው ከእኔ ይልቅ ባንተ አካሄድ አገር ይጠቀማል ወይ? የሚለው ነው መሆን ያለበት:: (ይሄ የታወቀ ነው:: መንገር አያስፈልገኝም አትበሉ:: ተደጋግሞ መናገሩ ይበጃልና ምክሩን ደጋግማችሁ ስሙት::) ይህንን ሳስተውል አንድ ነገር ትውስ አለኝ:: የሶርያው የጦር ዓለቃ የንዕማን ነገር ነው:: ንዕማንን አንዳንዶቻችን እናውቀዋለን:: ብዙ ወታደራዊ ድሎች የነበሩት ቢሆንም ይህ የሶርያ የመከላከያ ሹም ግን ለምፃም ነበረ:: ለምፁ የሚፈጥርበት አለመመቸት ስለነበረው የፈውስ ጥማት ነበረው::ታዲያ እንደመለኮታዊ አጋጣሚ በዚህ ሰው ቤት አንዲት እስራኤራዊት ምርኮኛ የቤት ሰራተኛ ነበረች:: ይች ሴት የለምፅ ደዌ ስለሚፈወስበት ሁኔታ እውቀት ነበራትና ለእመቤትዋ ምን ትላታለች፤ «ጌታዬ እኮ ወደ እስራኤል ቢሄድ ከለምፁ የሚነፃበት ነቢይ አለ፣ ስለምን ወደዚያ አይጓዝም? ስትል ተቆርቋሪነቷን ጭምር ስትገልጽ፣ ሚስት ይህንኑ ለባል ትነግርና ንዕማን ወደ ነብዩ ኤልሣ ይሄዳል፣ ከለምፁ ደዌም ይፈውሳል:: (ፈውሱን ተቀበለ ሚንስትር ንዕማን ማለት ይሄ ነው::)

የዚህ ታሪክ መልዕክት ምንድን ነው? ንዕማን የመፍትሄ ሀሳቡ ከአንዲት የተናቀች ምርኮኛ ባለጋራ ወይም ተቃዋሚ የመጣ ስለሆነ ለዚህ ትኩረት የለኝም ብሎ አለመናቁ ነው:: ከዚህ የምንማረው ተቃዋሚም ሆነ ገዥ ፓርቲ ሀሳቡን ከጥቅም አንፃር እንጂ ከሀርቫርድና ኦክስፎርድ አንፃር ሳያዩ ጠቃሚ ሃሳብ ነው ወይ? በሀሳቡ ሌላ የተጠቀመ ሕዝብ አለወይ? ይሞከር ወይ? ማለት ይኖርብናል እንጂ ሃሳብን ከሰውየው ማንነት ጋር ልናይይዝ አይገባም:: መመቻቸትና መደላደል ለነሳን ችግር (ደዌ) /ዋናውም ደዌ ድህነት ነው/ መፍትሄ ካለ ዘለን እንጠቀም እንጂ ሀሳቡ በሱ ከቀረበ አልቀበልም አንበለው:: በመሰረቱም ቢሆን እኛ ተቃዋሚውንም ገዢውንም ፓርቲ የምንመለከት የህዝብ አካል የሆንን ክፍሎች በጭፍን ተቃዋሚውን ወይንም ገዢውን እንደግፋለን በማለት ሳይሆን እየተመለከትን ያለነው ማናቸው ትክክለኛ ሀሳብ ያቀረቡት? የሚለውን እንደምንመረምር አትዘንጉት:: እንዳይመስላችሁ፤ መመዘኛው ይሄ እንጂ ሌላ አይደለም - በከተማም በገጠርም ያለን ህዝቦች:: ከእናንተ የምንፈልገው ትክክለኛ ሀሳብና እውቀትን ሥራ ላይ ማዋልን ስለሆነ በዚህ መንፈስ የመስራት ግዴታ እንዳለባችሁ፤ሊጠፋችሁ አይገባም::

ሌላው የተቃዋሚና የገዥው ፓርቲ የእርስ በእርስ ችግር አንዱ ሌላውን ይጠላኛል ብሎ የማሰብ ነገር ነው:: ይህን ሀሳብ በመያዝም ስለእኔ መልካም የማይናገር ስለሆነ አልቀበለውም የሚል ነገርም ያለብን ይመስላል:: እንዲህ ያለው ነገር ግን በወካዩ ህዝብ ከተሰጠ ሀላፊነት (manadate) ውጭ ነው:: ይህን ጉዳይ ሳስተውል መንፈሴ ወደ ንጉስ አክአብ ወስዶኛል:: እርግጥ ንጉሱ ዲሞክራሲያዊ ፕሬዚዳንት ስላልነበር ከዚህ ጉዳይ ጋር አይሄድም ሊባል

ይችላል:: በበኩሌ እንዳየሁት ግን የሱ ቢያንስ አንድ አካሄድ ለዲሞክራሲ አስተዳደርም የሚጠቅም መልዕክት የሰጠ ነው:: ስለሆነም ይህንን ነገር ቀጥዬ ባጭሩ ልተርክ ወይም ለመተረክ ልሞክር::

በአንድ ወቅት ንጉሱ ከሶሪያ ጋር ጠበኛ ነበርና የሶሪያን ንጉስ ከወታደሩ ጋር ሊገጥም ፈለገና የይሁዳን ንጉስ ኢዩሳፍጥን ተባበረኝ ሲል ደለለው:: የይሁዳ ንጉስ ግን ምሪት (Direction) ሳይቀበል ለሰልፍ ስለማይወጣ ነቢይ ይጠይቅ ዘንድ አክአብን ጠየቀ:: አክአብም ይስማማና ጉዳዩ ለ400 የቤተመንግስት ነቢያት ውሳኔ ያቀርባል:: የቤተመንግስቱ ነቢያትም እግዚአብሄር ሶርያን በእጅ አሳልፎ ይሰጣልና ውጣ! አሉት:: ኢዩሳፍጥ ግን የለም ሌላ ትክክለኛ ነቢይ ይፈልግ! በማለት 400ውን ነቢያት ተብዬዎች በጄ አልል አለ:: ኋላም ሚኪያስ የተባለ ነቢይ እንዳለ፣ይህ ነቢይ ግን ዘወትር ለንጉስ አክአብ መልካም እንደማይናገርና አክአብም ይህንን ነቢይ እንደሚጠላው በግልፅ ለንጉሱ እዩሳፍጥ ገለፀ:: ኢዩሳፍጥ ግን ይህንን ተቃውሞ በመገዳደር፣ንጉስ እንዲህ አይበል፣የተባለው ነቢይ ይምጣ! ብሎ የአክአብን ተቃውሞ አፈረሰ::

ነቢዩም ቀርቦ በመጨረሻ አክአብን እንዲህ አለው:- ወደዚህ ጦርነት አትውጣ፣ጦሩ በሰላም ወደቤቱ ይመለስ ብሎሀል እግዚአብሄር! ሲል ቢገልፅለት ንጉስ አክአብ ይህን እውነተኛ ነብይ ባለጋራዬ ነህ ሲል ነቢዩን አሰረ:: ማ? አክአብ ነዋ! ከጦርነቱ እስክመለስ ድረስ የመከራ እንጀራ ይብላ፣የመከራም ውሃ ይጠጣ አለ:: ነቢዩም በበኩሉ አንተ ከተመለስክ እኔ ነቢይ አይደለሁም! አለው:: አክአብም መለኮታዊ ምክር ንቆ ወደሰልፍ በመግባቱ በአሳፋሪ ሁኔታ ሞተ:: /lgnominious death ይሉታል ይሄን::/

ከዚህ የሚቀሰመው አንዱ ትምህትር በተቃዋሚነት የምናየው ሰው ታዳጊ ሊሆነን መቻሉንና ለሆዳቸው ያደሩ አጭበርባሪዎች ሊሸነግሉን መቻላቸውንም ነው::

ነቢዩ ሚክያስ ንጉሱን አክአብን የመታደግ ተልእኮ እንደነበረው አክአብ ስላልተገነዘበ በማይገባ ዘመቻ ሊወድቅ እንደተገደደ ሁሉ ለህዝብና ለአገር ጥቅም የሚሰሩ መሆናቸውን የሚታይላቸውን ተቃዋሚዎች ባንጠላ ተገቢ ይመስለናል:: በአንፃሩ ቃላቸውን አስተባብረው ወደማይገባ ጠበኝነትና ጦረኝነት ከሚገፋፉ አስመሳዬች ግራ ቀኙ ሊጠነቀቁ ይገባል:: ይሄ መፅሀፍ ቅዱሳዊ እውነት መመሪያ አይሆነንም ማለት የዋህነት መሆኑን በማሰብ የበኩሌን የዛሬ ተልዕኮ እዘጋለሁ:: ደህና ቆዩን::

# አውራአምባ - በህንድ

**ከተስፋ ተገኝ**

በአማራ ክፍል በደቡብ ጎንደር ዞን ወረታ- ወልደያ መስመር ወደ ቀኝ ገባ ብሎ አውራ አምባ መንደር ትገኛለች፡፡ አውራ አምባ ለመድረስ ከክልሉ ርዕሰ ከተማ ባህርዳር ተነስቶ በመኪና 4 ሰዓት ገደማ ያስኬዳል፡፡ የአውራ አምባ ማህበረሰብ ምን ዓይነት ዕምነት አመለካከትና ሃሳብ እንዳላቸው በብዙሃን መገናኛ በተደጋጋሚ ቀርቧል፡፡

በዚህ ጽሑፍ የቀረበው በአገራችን ያሉትን የአውራ አምባ ማህበረሰብ አስመልክቶ ሳይሆን ሕንድ አገር ያሉትን «ኦራቭል ፋውንዴሽን» (የህንድ አውራምባ) ማህበረሰብ በተመለከተ ነው፡፡ ኦራቭል ፋውንዴሽን በህንድ አገር ከታሚልናዱ ግዛት ርዕሰ ከተማ ከቸናይ በመኪና የ4 ሰዓት መንገድ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ አካባቢ የሚኖሩ ማህበረሰቦች እምነት፣አመለካከት ፣ሐሳብና ህልም ከአገራችን የአውራ አምባ ማህበረሰብ ጋር በእጅጉ ተመሳሳይ ነው፡፡

የኦራቭል ማህበረሰብ አስተሳሰብ መሥራች ኦሮቢንዶ ኦሻራም ተብሎ ይጠራል፡፡ የተወለደውም ህንድ ካልካታ በ 1864 ዓ.ም (ሁሉም የዘመን አቆጣጠር በኢትዮጵያ ነው) ነው፡፡ የተማረው ለንደንና ካምቢሪጅ ሲሆን በትምህርቱ ጎበዝ እንደነበረ ይነገርለታል፡፡ በኋላም ህንድ ተመልሶ በከፍተኛ የአስተዳደር ኃላፊነቶች ሰርቷል፡፡ የነበረውን የአስተዳደር ሥርዓት ስለሚቃወምና እንዲለወጥ ስለሚታገል ወደ እስር ቤትም ተወርውሮ የነበረ ሲሆን ከእስር ከተፈታ በኋላ የሕይወቱ አቅጣጫ ሙሉ በሙሉ ተቀየረ፡፡ በፖለቲካና በጋዜጠኝነት ሥራ ለጥቂት ጊዜ ሲሰራ የቆየውን በመተው ወደተለያዩ መንፈሳዊ ልምምዶች ሊመራ ወደሚችል በጥልቀት እራስን ወደማየት ተግባር ተጠመደ፡፡

በፓንዲቸሬ ግዛት ለአራት ዓመታት በፀጥታ እራሱን ሲመለከት ከቆየ በኋላ ከእናት (THE MOTHER) ጋር በመቀናጀት አንድ የፍልስፍና ወርሃዊ መጽሔት ያሳትሙ ጀመር፡፡ ኦሮቢንዶ በ1918 ዓ.ም ከውጫዊ ጉዳዮች እራሱን በማራቅ አብዛኛውን ጊዜ ውስጣዊ እሱነቱን በማየት ሥራ እያሳለፉ እስከ ሞተበት 1942 ዓ.ም ድረስ የተለያዩ የፍልስፍና ጽሁፎችን ጽፏል፡፡

የማህበረሰቡ አባለት የሚጠሯት እናት (MOTHER) እያሉ ነው፡፡ እናት የተወለደችው በፈረንሳይ – ፓሪስ በ 1870 ዓ.ም ነው፡፡ ከልጅነቷ ጀምሮም ለየት ያለ አመለካከት እንዲሁም ለሥነ ጽሑፍና ለፍልስፍና የተለየ ዝንባሌ የነበራት ሲሆን በተጨማሪም በስዕልና በሙዚቃ የጎላ ተሰጥኦ ነበራት፡፡ በ1906 ዓ.ም ኦሮቢንዶ ጋር ስትተዋወቅ አንድ ዓይነት ራዕይ ስለነበራቸው ለመግባባት ጊዜ አልወሰደባቸውም፡፡

በወቅቱ በአካባቢው ጦርነት ስለነበረ ከጥቂት ወራት በኋላ ወደ አገሯ ተመለሰች፡፡ ከዚያም ለተወሰነ ጊዜ ጃፓን አገር ከቆየች በኋላ በ1928 ዓ.ም ወደ ፓንዲቸሪ ግዛት ተመልሳ ቀሪውን ዕድሜዋን ኖረች፡፡

ኦሮቢንዶ ከውጫዊ ጉዳዮች በቋሚነት ራሱን ካራቀበት ከ 1918 ዓ.ም ጀምሮ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሥራዎችን ተረክባ ትንቀሳቀስ ነበር። ኦሮቢንዶ የሐሳቡ ጠንሳሽ ይሁን እንጂ በኦሪቬል ፋውንዴሽን ግቢ ውስጥ የተከናወኑ አብዛኞቹ ሥራዎች በእናት አማካኝነት የተሰሩ ናቸው።እናት በ 1950 ዓ.ም አጠቃላይ ሥራዋን ለተከታዮቿ አስረክባ ልክ እንደ ኦሮቢንዶ እራሷን አገለለች። የውስጣዊ መንፈሷን እና የሥራዋን ዕድገት አስመልክቶ «የእናት አጀንዳዎች» በሚል ርዕስ አሥራ ሦስት ቅጾች ታትመዋል። እናት በ96 ዓመቷ በ 1966 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታለች።

የዙምራ እና የኦራቪል ፋውንዴሽን መሥራቾች ህልም ማንም ሰው በዚህ ዓለም ሲኖር የብሄርተኛነት ስሜት የእኔ ነው የሚል የግል የይገባኛል ጥያቄ ሊያነሳ አይገባም። የሰው ልጅ በፈለገው አካባቢ፣በእኩልነት፣በሠላምና በፍቅር አብሮ ሊኖርበት የሚገባ የጋራ ሐብት ናት የሚል ራዕይ አላቸው።

ሕፃናት ውስጣዊ እነሱነታቸውን እንደያዙ በአንድነት ተሳስረው ማደግ አለባቸው። ሲማሩም ፈተናን ለማለፍ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ሳይሆን ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ተረድተው የተሻለ አዲስ ነገር ለመፍጠር መሆን ይኖርበታል» የሚል ሕልም አላቸው። ይህን አመለካከት የሚያራምዱ የማህበረሰብ አባላት የሚኖሩበት አካባቢ ኦሪቪል ተብሎ ይጠራል። ስያሜው የተወሰደው ሐሳቡን ካመነጨው ወይም ከመሥራቹ ኦሮቢንዶ ያሽራም ስም ነው። ቦታው በወቅቱ የተራቆተና ያገጠጠ ምድረበዳ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ማህበረሰቡ ዓይን የሚማርክና የማይጠገብ ቦታ አድርገውታል።

በዚህ ማህበረሰቡ በመረጠው ቦታ አንድ ሰው ከየትኛውም የዓለማችን ክፍል ይምጣ ወይም የየትኛውም አገር ዜግነት ይኑረው ምንም ዓይነት የሃይማኖት ወይም የፖለቲካ አመለካከት ይያዝ በዚህ አካባቢ በነፃነት የመኖር መብት አለው። ይህ ስብጥርም እውነተኛውን የሰው ልጅ አንድነት ይፍጥራል ተብሎ በማህበረሰቡ ይታመናል።

የዚህ አስተሳሰብ አራማጆች መኖሪያ የሆነው የኦሪቭል አካባቢ ፕላን በአራት ክፍሎች ተከፋፍሏል። ከአራቱ ክፍሎች መካከል እናትነትን የሚወክል አንድ ለየት ባለ ንድፍና በወርቅ ቅብ የተሠራ ጉልበት ያለው ሕንፃ አለ። ይህ ውስጡ የሚያምርና በጀርመን ባለሙያዎች የተሠራው ሕንፃ ቤተክርስቲያን ወይም መስጊድ አይደለም። ሆኖም ግን ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት በውስጡ ሆነው አምላካዊ ባህሪን በመላበስ የሰው ልጅን ሠላማዊ አንድነት ለማሳደግ በፀጥታ ራሳቸውን ወይም ውስጣዊ ማንነታቸውን በተመስጦ የሚያዩበት ቦታ ነው። ይህን ሕንፃ ማዕከል በማድረግ ቀሪው ቦታ በአራት ዞኖች ተከፋፍሏል። እነሱም የባህል ዞን ፣ዓለም አቀፍ ዞን ፣ኢንደስትሪ ዞን እና የመኖሪያ ዞን በመባል ይጠራሉ።

የባህል ዞን ሥነ - ውበት ፣ባሕል፣ስፖርት ... የሚካተቱበት ነው፡፡ ትምህርትና ጤና በዚሁ ዞን ሥር ቢሆንም የትምህርት አሰጣጣቸው ግን በራሳቸው ሥርዓተ ትምህርት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎች ወድቀዋል ወይም አልፈዋል ብሎ ጣጣ የለም፡፡ ተማሪዎቹ በትምህርት ጊዜያቸው ሁሉም ሊይዙት የሚገባውን ዕውቀት (ክህሎት) እንዲይዙ ይደረጋል፡፡ በዚያ መልክ ሁሉም ያልፋሉ፡፡ ተማሪዎችም ከነሱ ክልል ውጭ ባሉ ሌላ ትምህርት ቤት ሲሄዱ ያለውን ሁኔታ ምን እንደሚመስል የሕንዱ አውራ አምባ አባላት ተማሪዎች ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ወይም ዩንቨርሲቲ ሲገቡ ብቁ ተወዳዳሪና ውጤታማ ስለሆኑ ያላቸውን ሥርዓተ ትምህርት እንዲለውጡት የሚያስገድድ ሁኔታ እንዳላጋጠማቸው ይናገራሉ፡፡ ጤናንም አስመልክቶ በነሱ የጤና ተቋማት ታክሞ መዳን ያልቻለ ግለሰብ ሲያጋጥም ማህበሩ ወጪውን በመሸፈን ሌላ ጤና ተቋም ሄዶ እንዲታከም ይደረጋል፡፡

በዓለም አቀፍ ዞን የሚኖሩ ሰዎች ከተለያየ አገር የመጡ በመሆናቸው ማህበራዊ ኑሮን የሚያጠናክር ሕዝብ ለሕዝብ የሚያስተሳስር ሥራዎች የሚሠራበት ነው፡፡ ተሠርተው ከታዩት ሥራዎች ውስጥ ለአብነት ከ124 አገሮች በመጣ አፈር የተሠራ ስቴዲየም መሰል ክብ ነገር ይጠቀሳል፡፡ ይህ ቦታ አልፎ አልፎ የስብሰባ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ በዚህ ዞን የሰው ልጅ መተሳሰብን ፣ህብረትንና አንድነትን አስመልክቶ ለመሰባሰብና ለመመራመር የሚያስችል ዓለም አቀፍ የምርምር ተቋም ለመገንባት ዕቅድ እንዳለ ይነገራል፡፡

የኢንዱስትሪ ዞን ማህበረሰቡ የተሻለ ኑሮ የሚያኖረውን ገቢ ማግኘት የሚያስችለውን ሥራ መሥራት ነው፡፡ የገቢ ማስገኛ መንገድ ተብለው የተዘረዘሩት ደግሞ ከቀላል ግብርና ጀምሮ እስከ ትልቁ ኢንዱስትሪ ማንኛውንም ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎች ናቸው፡፡

በአሁኑ ወቅት የዚህ አመለካከት ተከታይ ቁጥር ከተለያዩ አገሮች የመጡ 1880 ቤተሰብ ያሉ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ ሁለት ኢትዮጵያዊያን ይገኛሉ፡፡ የመኖሪያ ዞን ለነዋሪዎች ማህበራዊ ኑሮና የዕለት ዕለት እንቅስቃሴ የማይገታ ሆኖ በመገንባት ትኩረት ያደረገ ነው፡፡
በሁሉም ነገር ዘመናዊ በሆነው መመገቢያ አዳራሽ ሲገባ ሁሉም ሰው ጫማውን አውልቆ ይገባል፡፡ የሚሰጠውም ምክንያት መመገቢያ ቦታ ስለሆነ ለንጽህና ሲባል መሆኑን ነው፡፡ ምግቡ ቡፌ ሲሆን እያንዳንዱ ሰው ተመግቦ ሲጨርስ የተመገበበትን ሳህን አጥቦ ያስቀምጣል፡፡ ምግብ የሚበስለው ከፀሐይ ብርሃን ከሚገኝ ኃይል ነው፡፡

በአንድ ጊዜ ለአንድ ሺህሰዎች ምግብ ለማብሰል የሚያስችል የፀሐይ ብርሃን ማመንጫ አላቸው፡፡ ዝናብና ደመና በሚሆን ወቅት እስከ 500 ሰዎች የሚመግብ ምግብ የማብሰል አቅሙ አለው፡፡

ከዚህ ማህበረሰብ መውጣት እንደ መግባቱ ሁሉ ቀላል ነው:: ነገር ግን ማንም ሰው ይዞት የሚወጣው ቁሳዊ ንብረት አይኖርም:: ሆኖም ወደፈለገው ቦታም ሆነ ሀገር የሚያደርስ የገንዘብ ድጎማ ይደረግለታል:: ማንም የኦሮቪል ፋውንዴሽን ማህበር አባል ለመሆን ደግሞ ፓስፖርት (የመኖሪያ ፍቃድ) በቀጥታ ከአካባቢው አስተዳደር ሊያገኝ ይችላል:: ይህ ማህበረሰብ ራሱን ችሎ እንደ ሀገር የሚታይበት ደረጃ ላይ ለመድረስ ከፈረንሳይ ድጋፍ የሚያገኝ ሲሆን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ የህንድ መንግሥት የቴክኒክ እና የገንዘብ ድጋፍ እያደረገለት ይገኛል:: የበለጠ መረጃ ለማግኘት የሚፈልግ ከአለ በሚከተለው አድራሻ

AUROVILLE FOUNDATION – AUROVILLE, TAMIL NADU,INDIA

ወይም ህንድ ኤምባሲ አቧሮ ኢንፎርሜሽን ሴክሽን ቢፅፍና ቢጠይቅ ሊያገኝ የሚችል መሆኑን በመጠቆም የኦርቪል ፋውንዴሽን ማህበረሰብን በአካል ምልከታ ለአደረገው ምንጩ መንገደኛው ብዕርተኛ አመሰግናለሁ::

# ሁለተኛው ቀዝቃዛ ጦርነት ውስጥ ገባን እንዴ?

***ሰሎሞን አበበ ቸኮል***

11ኛይቷ ሰዓት የምር ገባች መሰል የሰብዓዊ መብት ሪፖርት ከአሜሪካ ኮንግረስም ጋር አላተመው:: ልክ በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት የሩስያ ኮሚኒስት የሚያሳየው ሩስያ በቀዝቃዛኛ ጦርነት ያሳየችው እናንተ እንጂ እኛ አይደለንም የሰብዓዊ መብት አፍራሾች ማለትም መጣ:: ቀስ በቀስ እየፈጠጠ መውጣቱ ይሆን? ዝም ብላችሁ አስተውሉ እስቲ::

ቀዝቃዛው ጦርነት የሐሳቦች ጦርነት ነበር:: በሕዝብ አእምሮ ላይ የሚደረግ ጦርነት:: የፕሮፓጋንዳ ጦርነት:: በርግጥ ያኔ እስያንና አፍሪካን በመሳሰሉት ሌሎች ሀገሮች ላይ ነበር የሚደረገው:: ምዕራብያዊያን ተበልጠው ሶቭየት ከድል ወደድል ትሸጋገር ነበር:: ታዲያ ምዕራቡ የኮሚኒስቱን ምስራቅ በመብት ረገጣ ሲወነጅል ሩስያ ደግሞ ፈጣንና የበረታ ምላሽ ትሰጥ ነበር:: እዚህም ይሄው ነው የሚታየው::

ያን ጊዜ የአሜሪካ የውጭ ዕርዳታ ፕሮግራም ኮሚኒስቶችን ለመቆጣጠርም መሣሪያ ሆኖ ነበር:: ያም ሆኖ ይህ ኮሚኒስቶችን ለመዘርፈጥ ብቁ ሆኖ አልቆየም:: በአገራችን የተሞከረው የዕርዳታ ማቀብ ዕድሜ ለምስራቅ አፍሪካ ትኩሳት በእንዴት ያለ ወዳጅነት ተቀይሮ እንደቀጠለ የምናውቀው ነው::

ከሁሉም በላይ የውጭ ዕርዳታው ወዳጅነትን በገንዘብ መሸመት እንደሚቻል ለምዕራቡ ዓለም በጆሮአቸው ሹክ የሚል ነገር ፈጣሪ ነበር:: ሌላው የሚያስበውን ከመረዳት ይልቅ ገንዘብን አውጥቶ መወርወር የበለጠ ቀላል ነገር ነው:: ድሮም ዛሬም ይህ የሚደረገው ከድህነቱ የተነሳ ነው:: ድህነት ግን አስተማማኝና ዋስትናው በተረጋገጠ መሠረት ተጀምሮ ቀጣይነት ባለው ጥረት የሚረታ ነገር ነው:: በተለይ ለኢትዮጵያዊው እፎይ ብሎ የራሱን ሕይወት

እንዲኖር ቢደረግ ባለፉት 30 ዓመታት እንደቆየበት ሳይታመስ በተረጋጋ ሰላም ቢቆይ ከላይ ያለው በፖለቲካና በሥልጣን ጉዳይ ሳይጎነትለው ለአንድ ዐሥር ዓመት እንዲኖር ቢለቀው እንደ ፍጥርጥሩ መውጣት የሚችልበት አቅምና ማህበራዊ ጸጋ ነበረው:: ከምር ስለአገርና ስለወገን በሚያስብ ተቆርቋሪ ከለላ ስር ቢተው ቀድሞ ለሌላ ዓላማ ሲባል ሳይሆን ለራሱ ታስበው በተሠሩ ፖሊሲዎችና ሕጎች ከላይ ልባዊ ድጋፍና ልባዊ ከለላ ቢያደርጉለት ሳያውቅ ጥልቅ እንዲል በተደረገበት ግሎባላይዜሽን ውስጥ ቢሆን የራሱን ኑሮ ለመኖር ተፎካካሪ መሆኑን የግዱን ያውቅበት ነበር:: ቤቱና ጎረቤቱ ድረስ የሚዘልቅ --- አለመረጋጋት በአካል፣ በአእምሮ፣ በሥነ ልቦናና ... ባይደረስበት አሁንም በአስርም ሆነ በሃያ ዓመት ውስጥ መመንጠቅ መጀመርን ባላጣበት ነብር:: በሚሊዮናትና ቢሊዮናት ብር ርጥባን ሳይሆን ራሳችን በራሳችን በአጥንትም ቆፍረን ቢሆን ለራሳችን እናውቅበት ነበር - ቢለቁን::

ያን ጊዜ በቀዝቃዛው ጦርነት የየአገሮቹ ሰበብ ሆኖ ዕርዳታውም አንዱ መሳሪያ ሆኖ ነበር:: ግና ድህነት ለቲዮሬቲካል ኮሚዩኒዝምም ምርጥ መፈልፈያው እና ማራቢያውም፣ ለፕሮፓጋንዳ ማዛመቻም አገለገለ:: ያኔ እንዲያ እንደሆነው ድህነታችን ለአብዮታዊው ዘመቻ ማስፋፊያና ሥር መስኬጃ ሆነ::

ድህነት በቀዝቃዛው ጦርነት ሩሲያን ለመውጋትም እንደ ጦርሜዳ አገልግሏል:: ሃምሳም፣ ስልሳም ዓመት ሙሉ ሠራተኛውንና ብዙውን ሕዝብ ሥርዓት ባጣ አመራር ማቆየቱን በጭካኔና በግፍ ማኖሩን እንጂ ለድሃው ምንም አልተረፈም:: የሠራተኛው ክብርና ውርደት ነበር ከዚያን ያህል ዓመት በኋላም ለሶቭየት ሕብረት ሰዎች የተረፈው:: በኢትዮጵያም እነሆ ንጉሡ ነገሥታዊው መንግሥት ከተፈጸመ ወዲህ ኢትዮጵያን በእጃቸው ያቆዩ ሁለቱም አብዮታውያን የኢትዮጵያን ውርደትና ከዕለት ወደ ዕለት መውደቅን ነው ያተረፉት:: የፊቱ 17ቱን ዓመት በጦርነቶችም ነበር ያሳለፈው:: «የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም» ይል የነበረው ደርግ አሜሪካውያን ሞቱንም ውድቀቱንም ያስቡለት ስለነበር ያን ያህል ከጎኑ የቆሙለት አልነበሩም:: የዚህኛው ግን ፈጽሞ የተለየ ነው:: ራሱ የሚያመጣው ራሱ የሚያሮጠው መታወክ ካልሆነ ቢያንስ የፊቱን ያህል አልተወጠረም:: ሁሉን እየመዘገቡም ቢሆን አሜሪካውያንም ሆኑ ሌሎች ከጎኑ ሳይቆሙ የቀሩባቸው ጊዜያት አብረው ከቆሙበት ጋር ቢተያይ ከጀንያ ሙሉ ባቂላ አንዲት ጥቁር ራስ የመፈለግ ያህል ነው የሚሆነው::

እንዲሁም ዕድለኛ ሆኖ ለሃያ ፈሪ በሆነ ዘመኑ ከሰማንያ ሁለት ሚሊዮን ሕዝብ የአዲስ አበባን ሕዝብ ብዛት የሚያህለው ሰው እንኳ ኑሮውን ስንዝር ከፍ አላደረገም:: ቻይነቱን ያደለው ሕዝብ ሆኖ ግን ይኖራል:: ይህ ድህነቱ ታዲያ ከሁለቱም ወገን ጥሩ መሳሪያ እንደሆነ አለ::

የድህነት ጉዳይ በእርግጥም የነፃ - ዓለም ፕሮፓጋንዳ ነው:: በውቅ የተሠራ አውርዱልኝ ልብስ ያህል አንስቶ ጥልቅ ብድግ ነው:: በቀዝቃዛው ጦርነት በአፍሪካና በእስያ ዴሞክራሲ ሲጠሯት ብቻ የምትሰማ ጣፋጭ ቃል ነበረች፤ በኢትዮጵያም እንዲሁ ይቺ ዴሞክራሲ ከምላስ ላይ የተቋጠረች ቃል ብቻ ናት:: (እንዲያውስ ከምላስ እልፍ ያለችስ ብትሆን ይህ ዴሞክራሲ ዴሞክራሲ የሚባለው አገዛዝ ያኔ ሶሻሊዝም ሶሻሊዝም ተብሎ እንደተንቆላጠሰው ላለመሆኑ

እጃችንን ጠፍጥፎ የሚያሳምነን ይኖር ይሆን? ውስጡ ባዶ ሆኖ በሚሽጡ «ዜሮ ነው ኒውትሪቲቭ ቫሊው» የሆኑ ፈርኖዎች ውስጥ ዲሞክራሲም ቢሆን ወጥ (ሶሴጅ) አይሆንልንም፡፡ ይሁን ብለን ስናስበው ደግሞ «ሁሉ እኩል ነው፤ አንዳንዶች ደግሞ የበለጡ እኩል ናቸው፤ ይልቁንም አሊጋርኪዎቹ!» የሚያስብል ጨዋታ ተያዘ፡፡

በቀዝቃዛው ጦርነት ጊዜ የኮሙኒስት ፕሮፖጋንዳ በጥንቃቄ የተሰመረ መስመር ይከተል ነበር፡፡ ሲጀመር አካባቢ በነበረ «ኮሚንተርን» ታስቦ ተቀይሶ በዚያው መሠረት በብልጠት ይራመድ ነበር፡፡ ኮሙኒስቱ በሳይንስ ውስጥ ሳይቀር ፕሮፓጋንዳ ነበረው፡፡ በሕዝቡ ሥነልቦናም እንዲሁ ቦታውን በጽኑዕ መሠረት ተክሎ ነበር፡፡

መጀመሪያ የብዙኃኑን ሻምፒዮናነት፣ ጨቋኝ በሆኑ ጥቂቶች ላይ፣ በጨቋኝ ሥርዓት ላይ ያውጃል-ያሳምናል፡፡ ቀጥሎ በብሔር ጥያቄ ረገድ በያዘው ስታሊናዊ ርምጃ የሰባሰባቸውን አገሮችና ሩስያ ላይ የውጭ ኃይሎች እንደተነሱ ያስረዳል - ይሄው ኮምኒስታዊው የቀዝቃዛ ጦርነት የምሥራቃዊ ጎን አባወራ፡፡

እንግዲህ ይኸንንም በምሥራቅ አፍሪካው ብሎክ እንተርጉምና እንየው እስቲ፡- በትምህርቱ፣ በታሪክ፣ በሲቪክስ የሞላው ምንድን ነው፡፡ እስኪ ብሔር የሚለውን ቃል ለምንድን ነው በአዲስ ፍቺ የያዝነው? አዋቂ ነኝ ያለ ሁሉ «ብሔር - ብሔረሰብ» ሲል ምን እያለ እንደሆነ አውቆት ይሆን? እንዴት ነው በአንዲት ብሔር በአንድ ብሔር ውስጥ ሌላ ብሔር የሚኖረው? የቋንቋው ሊቃውንትን እንኳ እንዴት አድርገው እንደወሰዷቸው እንጃ፡፡ ይህ ጉዳይ ይህ ቃል እንዴት ሆኖ ለነሱም ሌላ ሆኖ ተያዘላቸው? - በዚህ ዓይነት እንግዲህ እግዚአ«ብሔር» ማለቱም ልክ አይደለም እንበል? «እግዚአ - ብሔሮች» ማለትን እየተጠየቅን አይደለም ይሉን ይሆን?

እንደነዚህ ያሉ ቅስቀሳዎች ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ ደግሞ ያኔ በሩስያ ዛሬ በኢትዮጵያ እናያለን፡፡ ኢሕአዴግ ሥልጣን ላይ ከወጣበት ጊዜ በኃላ ከምርጫው ማግሥት እንደ አዲስ እስከ 1998 መከር መግቢያ ድረስ በየገጠሩ ሁሉ የዘመተበትንና ውጤቶቹን አይተናል፡፡ በየቦታው በሃይማኖት እየተነሣ የደረሰውን ግጭት ሁሉ በማሰብ ምንኛ ውጤታማ እንደሆኑም ማሰብ እንችላለን፡፡ ከምዕራቡ ዓለም ጋር በምርጫው የተነሣ የገጠመውን ፊት መንሳት እንደመለሰ ሲታሰብ የቀዝቃዛው ጦርነት የፕሮፓጋንዳ አርሴናሎች ብዙ ጊዜ ውጤታማ እንደሆኑ ይታየናል፡፡ ምክንያቱም ያኔ በቀዝቃዛው ጦርነትም ሆነ አምሳያው ባደረግነው ያለንበት ያገራችን ዕጣ እነዚህ ፕሮፓጋንዳዎች የአይዲያሊዝም እና የለውጠኝነት ስሜት በወጣቱና በሌሎች ወሳኝ የኅብረተሰብ ኃይሎች ዘንድ ያሳድራሉና ነው፡፡ ይልቁንም «ተጨቁነህ-ተበድለህ» የሚባለው ባለጉዳዩን እስከመስዕዋት ድረስ ለማነሳሳት የበረቱ ናቸው፡፡

ይህን ያህል የኅብረተሰብ ሥነልቦና ላይ መጫወት ሁሉ በሁለቱም - ያኔ በቀዝቃዛው ጦርነት በነበረው የሩስያ ፕሮፓጋንዳና አሁን በምናመሳስለው - ዘንድ ይበረታል፡፡ እና ደግሞ ወዲያው በአንድ ሌሊት ግልብጥ ማድረግ በሚያስችል ሙሉ ሀይልና አቅም ነው የሚፈጸመው፡፡ ከምዕራባውያን በተለይም ከአሜሪካ በተወረሰ የውይይትና የተቃውሞ ትግልን

ለማድረግ እንኳ ሳይሞከር ነገሩ በላይ በላይ ተጥሎ ፣ውጤቱን በሚያስገርም ሁኔታ አጠገብህም ባለው ወንድምህ ሳይቀር ታየዋለህ፡፡

የቀዝቃዛው ጦርነት ኮሙኒዝም ለእርምጃ፣ ለመስዋዕትነት፣ ለጀብድ ጥሪ ያደርግ ነበር፡፡ አደጋ የገጠመው መስሎ በታየው ጊዜ ይህንንም ሁሉ ማስፈጸም ይችላል፡፡ በምዕራቡ ዓለም ላይ የጠነከረ ትችትና አያገባህም የማለት ያህል ምላሽ ይሰጣል፡፡

በአንፃሩ የምዕራባውያን አብነት መንደላቀቅ በጥምዝ ሽቦ በተቀሰሩ ምቹ ምንጣፎች ላይ መንፈላሰስን የመሰለው ነው፡፡ ፕሮፓጋንዳቸው ፊልምና ሲኒማ ነው፡፡ በሆሊውድ መዋኛ ገንዳ በላዝቬጋዝ ካዚኖ … እንዲህ ያለው ቅስቀሳ ከድሆቹ አገራትና ከተያዘው ዓላማ የራቀ ሆነው ነው የሚታዩት፡፡ ቢያንስ ዒላማዎቹ ምዕራባውያኑ እንደሚያስቡት ላይሆን ይችላል፡፡ ምን ምቹ ሕይወትነቱ ከልባቸው ቢገባ፣ የኑሮው ጣሪያ አድርገው ሊቆጥሩት ይችላሉ፡፡ «እኛም ኖርን እንላለን!» ብሎ እንዴት ብሎ በቶሎ እንደሚያገኘው የሚያልምበትን ያስብ ይሆናል፡፡ ብዙ ጊዜ ታዲያ ይህን በፊልም የሚያየውን ሕይወት እንዲኖር ያነን ሊያገኝ የሚችልበትን አቋራጭ በመፈለግ ባገኘው ዕድል የመጠቀም ስሜትን ፈጥሮ በማይሆንና ወደከፋ ዓለም በሚወስድ መንገድ ሊመርጥበት ይችላል፡፡ ካጋጠመው የፖለቲካ ሥልጣንና ጥቅም ላይ ያለአግባብ መፈናጠጥም ሊሆን ይችላል፡፡

በቀዝቃዛው ጦርነት ጊዜ ለሶቪየት ሩሲያ በማጥቃቱ ላይ ነበረች፡፡ በመምታቱ ፈጣን ነበረች፡፡ ሁሌ መናተፍ ነው፡፡ ሁሌ ቀድሞ መናገር ነው፡፡ ሁሌ ሌላኛው የማይፈልገውን ማወጅ በሥሩ ባሉትም ላይ ፈጣን ዕርምጃ፣ ፈጣን ምላሽ በላዩ ላይ ማዝነብ ነው፡፡ ዴሞክራሲያዊያኑ ደግሞ ራሳቸውን በራሳቸው እንዲገልጹ የሚተዉ ናቸው፡፡ ምዕራቡ በላዩ ላይ የጫነው የዲሞክራሲ ድንጋይ እንደ ዔሊ ያዘግማል፡፡

እንዲያውም ብዙ ጊዜ ከሩስያ ጋር በሰላም የመኖር ፍላጎት ያሳይ ነበር፡፡ አሜሪካውያን በእርግጥም ያን ይፈልጉ ነበር፡፡ ዛሬም ቢሆን እንደዚያው ነው፡፡ ነገር ግን ከምዕራባውያን ወገን ይጠየቅ የነበረው ሌላ ነበር፡፡

«እነሱ በሰላም እንዲኖሩ የምንመኘውና የምንፈቅደው እነሱ ለኛ በሰላም መኖርን ሲፈቅዱልን ነው፣» በማለት ነበር «ማይካንትሪ ኤንድ ማይፒፕል»፣ «ዘ ኢምፓርታንስ ኦፍ ሊቪንግ» የመሳሰሉትን መጻሕፍት የጻፉት ሊን ዩታንግ የተባሉት በጊዜያቸው ከተከበሩ ፈላስፋዎች አንዱ የጠየቁት፡፡ «ዘ ሰክሬት ኔም» ብለው ያቀረቡትን ማንበብ ይቻላል፡፡ እንዳለ በዚህ መጣጥፍ እየቀረበ ያለውን መመሳሰል አንባቢ እየተመለከተ ይገርመዋል፡፡

«እኛ እነሱን በሰላም እንዲኖሩ የምንመኘው እነሱ እኛን በሰላም እንድንኖር የፈቀዱለት ነው፡፡» ይልና አሜሪካውያን የነበራቸውን ፍላጎትና መርህ ሊገልጹ ይሞክራሉ፡፡ «እኛ ፍትሕን ነፃነትን፣ ዲሞክራሲን እና የሁሉም አገሮች እኩልነትን ይዘናል፣» ይላሉ፡፡

የአሜሪካውያን የጊዜው ኃያልነትም እነዚህን በንባባቸውም ለምድሪቱ «ቅዱስ ቅዱስ» የሚባሉ ሐሳቦች ይዘው መገኘታቸውም ነው፡፡ እነዚህን ወደ ሌላው አገር ይዞ እጅን የማስገባቱ ነገር በራሱ የሚጠየቅ ነገር እንደማይጠፋው ይታወቃል፡፡ አሁን የኢትዮጵያ ገዢ ኃይል

ከአሜሪካ ጋር ከሚይዘው የወረቀትና የፕሮፓንጋዳ ዘመቻ አንፃር የቀዝቃዛው ጦርነት የኮሚኒስቶች ወገን በኩል በነበረው ሐቅ ዛሬም ይሄው በራሳቸው ወገን እንዳለ የሚተረጎም መሆኑ ተይዞ ነው እየተመሳሰሉ የሚገኙት።

ምሳሌ በአገራችን ሊቃውንተ ትርጓሜ ዓይነት ዓይነት አለው። በዋነኝነት ሁለት ያደርጓቸዋል፦ ምሳሌ ዘኢይተርፍ እና ምሳሌ ዘይተርፍ።

በሚመሰልበት ነገር (ልብ በሉ! «በሚሆንበት» አይባልም) ቁጭ እንዳለ ከሆነ፣ ምሳሌ ዘኢይተርፍ (የማይተርፍ ምሳሌ - ልክክ ያለ)፤ በከፊል፣ በተወሰነ መልኩ ብቻ መስሎ ሲገኝ ደግሞ «ምሳሌ ዘይተርፍ» ወይም የሚተርፍ ምሳሌ ይሆናል። አሁን ለአሜሪካን ምሳሌ አላመጣንም። ኮሚኒስቶቹን ግን የኢሰብዓዊነት ፖለቲካ ጥያቄ በተነሳ ቁጥር ከኔ ወዲያ ለፍትሕ፣ለዲሞክራሲና ለሰውልጅ መብት የቆመ የለም ከሚሉት ጋር በእጅጉ የሚተያዩ ናቸው። የመብት ከበራና ዴሞክራሲ በቀደመችቱ ኢትዮጵያ ተነስቶ አያውቅም (ምናልባት ወደ ፊት አይነሳም) ለሚለውና እንዲያውም ራሷን አሜሪካን የሰውልጅን መብት በመጣስ የሚከስሰው መንግስት በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በኩል የነቢንያም መሀመድ የጓንታናሞ ጉዳይ እየተነሳ ጭምር «እኮ እነ ማናችሁ እናንተ፣ የኛን ሰብአዊ ጉዳይ እያነሳችሁ የምትከሱን?» ማለቱን ይዟል። ይህ የቀዝቃዛው ጦርነት የፕሮፖጋንዳ አርሴናል ነበረ።

(ምሳሌ ዘኢይተርፍ ወይስ ዘይተርፍ ? ... ይህ ለአስተዋይ ተመልካች ይተዋል።)

በእርግጥም ፍትሕ፣ ነፃነት፣ እኩልነት፣ዲሞክራሲና የመሳሰሉትን መብቶች ለኢትዮጵያውያን በማውረድ የኢትዮጵያውያን መተዳደሪያ ደንብ ላይ በመጻፍም ጭምር ከማን ነበረ - እንደኔ? በማለቱ ረገድ የቀዝቃዛውን ጦርነት ዘመን ሩስያ ሶቭየትም ፕሮፓጋንዳ መለያ ነበር። ግና ከዚያኛው ወገን ሆነው የተመለከቱ እንደነ ሊን ዶታንግ ያሉት ታዲያ «ሁሌ ሁሌ» እንዲሁ እንደተዘፈነ ለምን እንደሚኖር ይጠይቁ ነበር።

እኔ እንደ ጲላጦስ ከደሙ ንጹህ እያሉ እጅን እየታጠቡ መኖርን ዓለም እንዴት አድርጋ ሁሌ ትቀበላለች? ... ይሉ ነበር። ቃል በቃል እናምጣው «ዓለም ሁሌም ስለራሱ መልካምነት የሚናገርን ሰው አታምነውም፣» በማለት ይተቹና በራሳቸው ወገን ያለውንም ይተቻሉ። «የኮሚኒስቱን የለውጥና የመስዋዕትነት ዕወጃም (call for) በተልካሻ ሐሳቦች መፋለምም አይቻልም!» ነበር ያሉት።

በጣም የሚያስገርመው የቀዝቃዛው ጦርነት ኮሚኒስት ፕሮፖጋንዳ ዓላማ ያኛው ወገን አንገቱን ደፍቶ፣ አናቱን ተመትቶ፣ ዐርፎ እንዲቀመጥ ማድረጉ ነበር። ምዕራቡን ዓለም ማሳፈር፣ ተቃዋሚውን በተገቢዋ ቅጽበት በፕሮፓጋንዳው መምታት! ማንኳሰስ፣ኃጢአቱን መቁጠርና «ለመሆኑ አንተ ማነህ የኔን ዐይን ጉድፍ - ያውም ጉድፍ ሳይኖርብኝ ልታወጣብኝ የምትሞክር?» በማለት፣ «እንዲህና እንዲህ ያደረግህ አይደልህምን?» ... ብሎ መዘርፈጥ ዋነኛ የጦርነቱ መሳሪያ ሆኖ ነበር። ምን ያለበት ምን አይችልምና በዚሁ ያኛውም ወገን ዐርፎ ቁጭ እንዲል ማዕረግን የተካኑበት ነበር።

ይህንን የተመለከቱት ከዚያ ወገን ያሉት ታዲያ ሩስያን ራሷን እንደዛው ማሳፈር እንደሚቻል ሲገልጹ ነበር:: ግና «ምዕራቡ ከፈለገ» ነው የሚሉት ታዲያ:: «ከፈለገ» የኮምዩኒስቱ ወገን አባወራ ገና እንዲያ ያለ ሥርዓትና አመራር ይዞ ከተገኘበት ጊዜ ጀምሮ ሊሆኑ የማይገባቸው እንከኖችና ስህተቶች የሞሉበት ሆኖ እንደሚገኝ ይታወቃልና ስንትና ስንቱን አንገቱን ማስደፊያ አውጥቶ በቀዝቃዛው ጦርነት የምሥራቁን ወገን ይገዛ በነበረው ላይ ማድረግ ይቻል ነበር?

ያነን ለማድረግ ስላልቻሉ - ስላልፈለጉ ወይም ያነን ከማድረግ መቆጠብን የመረጡ ሆነው የመገኘታቸው ሐቅ ታዲያ የሶቭየት ሩስያን ቁንጮዎች ሁሌ በራሳቸው የሚተማመኑ ሁሌ ተራማጆች እንዲሁም ከሥነ ምግባራዊ (ሞራል) እና ፖለቲካዊ እንከኖች ፈጽመው ሆነው እንዲያስቡ ወይም እንዲታሰቡ አደረጋቸው:: እንዲህ ብለው ነበር ያስቀመጡት እንግዲህ:-

The fact that the west has refrained from doing so creates the impression that Soviet Russia is ever confident  ever progressive and free from MORAL or POLITICAL BLEMISHES.

እንግዲህ በኮንግረሱ ሪፖርት ላይ የመንግሥትን አቋም የሚገልጸው ቢንያም መሃመድን ጠቅሶ ለዜጎች ተቆርቋሪ የመሆኑ ታሪክ ይህን ያህል ሆኖ የ ሚታይ ነው::

አንባቢም ቢሆን ይበዛበታል በማለት እንጂ በሊን ዩታንግ መጽሐፍ፣ «አሁን የሚያስፈልገው ነገር ሁሉን በትክክለኛ ስሞቻቸው መጥራት ነው» ብለው «የፀረ ኮምዩኒስት ዓለም ዓቀፋዊ ፖሊሲ» ማድረግ የሚገባውን በመጨመር የቀረቡትን በመዳሰስ ይህን የበለጠ ማፋጠን በተቻለ ነበር:: ለመተንፈስ ያህል ግን ይበቃል:: ግና አንድ ጥያቄ ወይም «የምሥራች» ሳንጠቁም አንሰናበትም:: እና እጠይቃለን:- እኛም እንደዜጋ በየደረስንበት የሚደርሰብንን ማንኛ ውንም ዓይነት መከራና ስቃይ፣ድብደባና ግድያም ቢሆን የሚጠይቅልን አባት አገኘን ማለት ነው? ብፁዕ አቡነ ቀውስ ጦስ በሌላ ርዕስ ጉዳይ በጻፉት አንድ መጽሐፍ  በመካከለኛው ምስራቅ ይደርስባቸው የነበረውን መበደል ያዩ የሌሎች አገር ሰዎች ሁሉ የሚረዳቸውና የሚቆረቆርላቸው አባት (መንግሥት) ባይኖራቸው ነው::» ይሉን ነበር ብለዋል:: እንዲያ ያሉት ሁሉ መልስ አገኘልን? ከንግዲህ በየአገሩ ላሉት ኢትዮጵያውያን ጥብቅና የሚቆም አገኘን ማለት ከሆነ እሰየው! ይሁን - ይሁን እንጂ ሌላ ምን ይባላል?

የምሥራች! በያላችሁበት

# ዳግማዊ የእስር ቤት ማስታወሻ - ለ13 ቀናት

**በወሰንሰገድ ገ/ኪዳን (ጋዜጠኛ)**

«ተራራ እገፋለሁ

መከራ እግፋለሁ

ዕጣዬ ነው ብዬ ለምን እከፋለሁ ?

አልከፋም እኔ

በዝቷል ብዬ በደል

አልቆጭም እኔ

ጠንቷል ብዬ በደል

የተስፋ ዕንቁላሌን

አድራለሁ ታቅፌ

ቅርፊት መከራዬን

ለመውጣት ሰብሬ ... »

ይህቺ ግጥም፣ወዳጄ ገጣሚ እንዳለጌታ ከበደ በ 2001 ዓ.ም «ልብ ሲበርደው» በሚል ርዕሥ ካሣተመው የግጥም መድብል የተወሰደች ናት:: ርዕሷ «ለምን?» ይሠኛል:: በ13 ቀናት የእስር ቤት ቆይታዬ «ለምን?» የሚያሠኙ በርካታ ሁኔታዎች ስለገጠሙኝ ለዚህ ፅሁፍ እንደመንደርደሪያ ልጠቀምባት ወደድኩ::

የእስር ቤት ሕይወት ለእኔ አዲስ አይደለም:: በምርጫ 97 ሰበብ ለ 1 ዓመት ከ 9 ወር እስር ቤት ለመቆየት ተገድጃለሁ:: የእስር ቤት ሕይወት አስቸጋሪ፣አስከፊ፣አሳዛኝ መሆኑን ጠንቅቄ አውቃለሁ:: ከእስር ቤት ከወጣሁ በኃላ ባደረግኩት መራር ትግል «ሐራምቤ» ጋዜጣን ለሕትመት ሳበቃ አንድ ቀን እንደምከሰስና ልታሰርም እንደምችል አውቃለሁ:: ይህ ደግሞ የደሀ አገር ጋዜጠኝነት ሙያ የሚጠይቀው መስዋዕትነት ስለሆነ አይደንቅም:: አይገርምም:: ይህ የ13 ቀን እስር ግን እጅግ የከፋ ነውና ክፋቱን ላወጋችሁ ብእሬን አነሳሁ::

እናም የካቲት 12 ቀን 2001 ዓ.ም ከቀኑ 5 ሰዓት አካባቢ ፍ/ቤት የተከሳሽ ሣጥን ውስጥ ልቆም ግድ ሆነ:: ዳኛዋ ጠና ያሉ ሴት ናቸው ስሜንና አድራሻዬን ጠየቁኝ:: ነገርኳቸው:: ከዚህ በኋላ ያቀረቡልኝ ጥይቄዎች ግን ግር የሚያሰኙም፣የሚያስገርሙም ዓይነት ነበሩ::

- የአባትህ ስም ማነው?
- ገ/ኪዳን
- ገ/ኪዳን ማ?
- ተገኝ
- የእናትህ ስም?
- የሺ ለማ

- የአባትህ ሥራ? የት ነበር የሚሠሩት?

ከዚህ በፊት ተከሰህም ሆነ፣ሌሎች ተከሳሾች ሲቀርቡ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ሲቀርብላቸው ሰምቼ ስለማላውቅ ግርም፣ግርምም እያለኝ መልስ ሰጠሁ።
ይቅርታ እንዲህ ዓይነት ጥያቄዎች ከተከሰስክበት ጉዳዮች ጋር የሚያያዛቸው ነገር የለም። ነገር ግን አንድ ዳኛ ቅርበት ወይም ዝምድና ያለውን ተከሳሽ ጉዳይ ማየት ስለሌለበት የማውቅህ ከሆነ ክስህን ላለማየት ነው የጠየቅኩህ ገባህ አይደል? አሉኝ።
«ገብቶኛል። ግን አያውቁኝም» በዚሁ ተስማማንና ዳኛዋ ክሱን አነበቡልኝ። እናም ጥያቄ አስከተሉ፣

«ክሱን ተረድተኸዋል? »

«አልተረዳሁትም!»

«አልተረዳሁትም?»

«አዎ! ግልጽ፣የተብራራና መልስ ለመስጠት የሚያስችለኝ አይደለም። ስለዚህ መቃወሚያ አለኝ» አልኩኝ ቀደም ሲል በጽሑፍ ያዘጋጀሁትን የክስ መቃወሚያ እያዘረጋሁ፣ እናም አንድ ኮፒ ለከሳሼ ዐ/ሕግ፣ሁለት ኮፒ ለፍ/ቤቱ አቀረብኩና ዋስትና እንዲሰጠኝ ጠየቅኩ።

ዳኛዋ ለጥቂት ደቂቃ የክስ ፋይሌ ላይ ሲፅፉ ቆዩና «የ3ሺህ ብር ዋስትና ታቀርባለህ። ዋስትና ማቅረብ የማትችል ከሆነ ማረሚያ ቤት ሆነህ ጉዳይህን ትከታተላለህ» የሚል ትዕዛዝ ሰጡ። ወዲያውኑ የችሎቱ ፖሊስ ክንዴን ያዝ አድርጎ ወደ እስረኛ ማቆያ ስፍራ ወሰደኝ።
ይህቺ የፍ/ቤት የእስረኛ ማቆያ ስፍራ አራት ሜትር በአራት ሜትር የምትሆን በብረት ፍርግርግ ብቻ የተሠራች ናት። ጊዜያዊ እስረኞች በብረት አጥር ውስጥ ተከርችሞባቸው ስለሚታዩ «አንበሳ ማሠሪያ» ብለው ይጠሯታል። አምስት ሰዓት ከሩብ የእስረኝነት ሕይወት ተጀመረ። ወደ አንበሳ ማሠሪያ ከገባሁ በኋላ አብሮኝ ወደ ፍ/ቤት የሄደውን የእህቴን ልጅ ቱታ፣የሌሊት ልብስ፣ነጠላ ጫማ፣ምሣ፣ትንሽ ገንዘብ እንዲያመጣልኝ ወደ ቤት ላክሁት። የ16 ዓመቱ ዮናታን ማልቀስ እየቃጣው ወደተላከበት ሄደ። እስከዚያው መታሰሬን ማወቅ አለባቸው ላልኳቸው ሰዎች መደወል ቀጠልኩ። 6:30 ሲል ዮናታን የላክሁትን ነገር ሁሉ በሻንጣ ውስጥ አጭቆ መጣ እስከ 4:30 የባጥ የቆጡን ስናወራ ቆይተን ሞባይሌን ሰጠሁትና ተለያየን። ማልቀስ እየቃጣው።

ደቂቃዎች እያለፉ፣ሰዓት እየነጎደ ነው። አንበሳ ማሠሪያ ውስጥ ያሉ ዋስትና እየተከፈለላቸው የሚወጡ በደስታ ይፍነከነካሉ። ዋስትና የሚጠብቁ ይቁነጠነጣሉ። አንዳንዶች ያለቅሳሉ። እኔና ሌሎች ሁለት ሰዎች ቁርጣችንን ስላወቅን ነው መሰል ተረጋግተን ተቀምጠናል። 8:30 ሲል በእስር ማቆያ ክፍል ውስጥ ያሉ ሰዎችን ስም ፖሊሶች መጥራት ጀመሩ። ተጠራሁ።

«አቤት»

«ዋስ አለህ?»

«የለኝም»

ፖሊሶች የእኔ እስር ትዕዛዝ እንደመጣ ተሯሯጡ:: የችሎቱ አስተናባሪ ተፈለገ:: አልተገኘም:: 9:30 መኪና መጣና ወደ ቃሊቲ የሚሄዱ አስረኞች ተጠርተው ወጡ:: እኔና አንድ ሰው ብቻ ቀረን:: ከኔ ጋር የቀረው ልጅ ቤተሰቦቹ እንመጣለን ብለውት ነበር:: አልመጡም:: ወደ ቃሊቲ የሚሄዱትን መኪና ውስጥ ካስገቡ በኋላ አንድ ፖሊስ ወደ እኛ መጣና «እናንተ ፖሊስ ጣቢያ ነው የምታድሩት» አለን::

«ለምን?»

«ማዘዣችሁ አልመጣም»

«እኔ ፖሊስ ጣቢያ አልሄድም» አልኩ ኮስተር ብዬ:: ይህን ስናገር የሰማች ፈንጠር ብላ የቆመች ፖሊስ እንደመደንገጥ ብላ ሮጥ አለችና ለሌላ ፖሊስ ያልኩትን ተናገረች:: ሲፈለግ የጠፋው እኔ የቀረብኩበት ፖሊስ እየተቆናጠረ መጣ:: «አንተ ነህ ፖሊስ ጣቢያ አልሄድም ያልከው?» አለኝ ቆጣ ብሎ:: «አዎ! ዋስትና ያልከፈለ ወደ ማረሚያ ቤት እንጂ ወደ ፖሊስ ጣቢያ አይላክም»

«ትሄዳለህ! ትሄዳለህ!»

ዝም አልኩት

«የዳኛ ትዕዛዝ ነው ትሄዳለህ» አለ እንደማስፈራራት እየቃጣው:: ከኔ ጋር የቀረው እስረኛ «አረ ሌላ ነገር ታመጣብኛለህ» በሚል ዓይነት በክርኑ ይጎሻሽመኛል:: ከዚህ በኋላ አተካራ መፍጠር አስፈላጊ ስላልመሰለኝ የሚለው ሁሉ እንደማልሰማ ሆኜ ፊቴን አዞርኩ:: እናም የፖሊስ ጣቢያ እስር ቤት ሞን እንደሚመስል በህሊናዬ ውስጥ ለመሳል ሞከርኩ:: «ተከሳሽ በችሎት እያለ እና ከችሎት ሲወጣ ሁለት የተለያየ ትዕዛዝ የሚሠጥ (ትዕዛዝ ተሰጥቶ ከሆነ) ምን ዓይነት ዳኛ ነው? እንዲህ ለማድረግ ሕጉስ ይፈቅድለታል?» ስል ከሕሊናዬ ጋር ሞገትኩ:: አወጣሁ አወረድኩ:: «ስለዚህ ዳኛዋ እንዲህ ዓይነት ትዕዛዝ አልሰጡም፣ አይሰጡምም» ስል ሐሳቤን ደመደምኩ:: «እና ማነው ፖሊስ ጣቢያ እንዳድር ያዘዘው?» ስል ራሴን መልስ የሌለው ጥያቄ ጠየቅኩ::

«ስማ! ዕለታዊ ተግባሩንና ሚጢጢዬ ኃላፊነቱን በአግባቡ መወጣት ያልቻለ ሰው በሙሉ የሌላውን ሰው መብትና ክብር ለመገሠሥ እጅግ ደፋር የሚሆንበት ሀገር ውስጥ መሆንህን አትርሣ» ሲል ሞገተኝ አንደኛው እኔነቴ::

«እስከ መቼ ድረስ»

«ምን እስከመቼ አለው! ሁሉም ሰው ራሱን እስኪያውቅ ነዋ»

«እና እዚህ አገር ውስጥ ሰው ሁሉ ራሱን አያውቅም ማለት ነው»

«ትክክል!»

በዚህ መልኩ ከራሴ ጋር እየተሟገትኩ ሳለ ከቀኑ 10 ሰዓት ሆነ ሁለት ፖሊሶች አንበሳ ማሰሪያ ውስጥ የቆየነውን ሁለት እስረኞች አስወጥተው አንድ አንድ እጃችንን በካቴና ጠፈነጉት:: «ሻንጣህን ያዝ» አለኝ አንዱ ፖሊስ:: ሻንጣዬን እንጠለጠልኩና በዓይኔ ማማተር ጀመርኩ:: እኛን ሊወስድ የመጣ መኪና ግን ማየት አልቻልኩም::

«የት አለ መኪናው?» ስል ጠየቅኩ::

«የምን መኪና በእግርህ ነው የምትሄደው» አለ ፖሊሱ «የማነው ጅል» በሚል ዓይነት ስሜት፡፡
«የት ነው ፖሊስ ጣቢያው?»
«አታውቀውም» አለኝ በስላቅ፡፡ ይኸኔ በተራ ሌብነት የተያዝኩ ተመላላሽ እስረኛ አድርጎኛል አልኩ ለራሴ፡፡ በዚህ መልኩ በሁለት ፖሊሶች ታጅበን ከፍ/ቤት ግቢ ወጣን፡፡ ይገርማል መንገዱ በሙሉ በሰውና በመኪና ተወሯል፡፡ ከወትሮው በተለየ መልኩ ሰው ሁሉ መንገድ ላይ ወጥቶ ተኮልኩሏል ወይም የተኮለኮለ መሰለኝ፡፡ ሰው ሁሉ እኛን ብቻ የሚያይ መሰለኝ፡፡ እጃችን በካቴና ታሥሯል፡፡ ሻንጣ ተሸክሜያለሁ፡፡ፖሊሶች ከኋላ «በዚህ ሂዱ! በዚህ» ይሉናል፡፡ በዚህ መልኩ ያየን ሰው ሁሉ በትከሻዬ ያንጠለጠልኩትን ሻንጣ አይቶ እጅ ከፍንጅ የተያዙ ሌቦች ናቸው ይለናል ስል አሰብኩ፡፡ የእፍረት ስሜት ወረረኝ፡፡ ከፍ/ቤት ቅጥር ግቢ ጀምሮ ልደታ ቤተክርስቲያን አለፍ ብሎ እስከሚገኘ ው ቀድሞው ወረዳ 20 ፖሊስ ጣቢያ ድረስ ያለው መንገድ 42 ኪ.ሜትር ያህል ራቀኝ፡፡ ብቻ ንዴትና እፍረት እየናጠኝ ወደፊት እንዛለሁ፡፡

ካጀቡን ፖሊሶች አንዱ አብሮኝ ወደታሰረው እስረኛ ጆሮ ጠጋ ብሎ አንዳች ነገር ያንሾካሽካል፡፡ ትንሽ ወደ ኋላ ቀረት ይልና ከሌላኛው አጃቢ ጋር ያሾክሹክና እነደገና ወደ እስረኛው ጠጋ ብሎ የሆነ ነገር ይለዋል፡፡ የእኔ ፊት በንዴት ስለተከሰከሰ ነው መሰል ፖሊሱ ሊቀርበኝ አልደፈረም፡፡

«ምን እያለህ ነው?» አልኩት የካቴና ቁራኛዬን፡፡

«እዚሁ ፖሊስ ጣቢያ አድራችሁ ከዚሁ ነው ወደ ቃሊቲ ማረሚያ ቤት የምትወሰዱት ነው የሚለኝ» አለኝ፡፡

«እና ?» አልኩት ገርሞኝ፡፡

«ነገ በጠዋት ፍ/ቤት መልሰናችሁ እዛው እንድትውሉ የሆነ ነገር ሽጉጡልን ነው የሚሉት»

«ጉቦ መሆኑ ነው!?» አልኩት፡፡

ጥያቄዬ ቁራኛዬን አስፈገገው፡፡ እናም «አንድ 20 ብር ብንሰጣቸው ይሻላል ፍ/ቤት ከዋልን ከቤተሰብ፣ከጓደኛ ጋር በስልክ መገናኘት እንችላለን፡፡ አስር ብር ካለህ እኔ አስር ብር አለኝ ...» አለኝ ብር መስጠት የተሻለ እንደሆነ ሲያሳምነኝ በሚጥር ስሜት፡፡

«እኔ ቤሳ ቤስቲን አልሰጥም ከፈለክ አንተ ስጥ» አልኩት በንዴት እንዲሁ እየተማገትን እሱ ከፖሊሱ ጋር እየተንሾካሾኩ የቀድሞው ወረዳ 20 ፖሊስ ጣቢያ ደረስን፡፡ ንዴት፣እፍረትና ተስፋ ቢስነት ተፈራረቁብኝ፡፡ እነዚያ ከእስረኛ ጉቦ የሚጠብቁ ፖሊሶች ደም መጣጭ ቁንጫዎች መስለው ታዩኝ፡፡ እንዲህ ዓይነት የዘቀጠ ሕሊና ያላቸው አንዳንድ ፖሊሶች ተስፋ ቢስ አደረጉኝ አሳዘኑኝ፣አሳፈሩኝ፡፡

የሆነ ሆኖ የቀድሞው ወረዳ 22 ፖሊስ ጣቢያ ቅጥር ግቢ ደረሰን፡፡ ግቢ በራፍ ላይ አነስተኛ የጥበቃ ቤት አለ፡፡ ከጥበቃው ቤት ጋር ተያይዞ የተሠራ ትንሽዬ የቆርቆሮ ቤት ይታያል፡፡ ከዚህች ቆርቆሮ ቤት ውስጥ የተከረቸመበት አንድ ሰው ፊቱን እስከአንገቱ ድረስ አውጥቶ ሲያቁለጨልጭ አየሁ፡፡ «ይኼ ነው እስር ቤቱ » አልኩ ለራሴ፡፡ ያጀቡን ፖሊሶች በዚህ በኩል እያሉን ከአንድ ቤት ጆርባ ወሰዱንና አንድ ቢሮ ውስጥ ለተቀመጠ ፖሊስ የያዙትን ወረቀት ሰጡ፡፡

ፖሊሱ ወረቀቱን አየና የሆነ ነገር ጫርጫር ካደረገ በኋላ ገብተን እንድንቀመጥ አደረጉ፡፡ የዕለት ሁኔታ መዝገብ አውጥቶ መዘገበን ከዛ በኋላ ቀበቶ፣ጫማ ክር፣ቦርሣ … የመሳሰሉትን እንድናስረክብ አዘዘና «ሻንጣ ይዞ ለምን አመጣችሁት? ለማንኛውም ሻንጣው እዚህ ቢሮ ይቀመጥልሀ፣ነገ ጠዋት ስትመጣ ትወስደዋለህ፣ልብስ መቀየር ከፈለክ ቀይር … » አለኝ፡፡

እዛው ቢሮ ቁታዬን፡፡ ሌሊት የምለብሰውን ስመርጥ አየና «ምን ያደርግልሀል፣የአንገት ፎጣው ብቻ ይበቃሃል፣የምትድበት ቦታ ጥሩ አይደለም» አለኝ፡፡

«ብር ይዣለሁ!» አልኩት፡፡ አምጣው አለኝና ስለመረከቡ ደረሰኝ መፃፍ ጀመረ፡፡ ፖሊስ ጣቢያ ያሉ እስረኞች የሻማ ብለው ከአዲስ እስረኛ ገንዘብ እንደሚቀበሉ በወሬ ደረጃ ስለማውቅ አስራ ሁለት ብር ያዝኩና 80 ብር አስረከብኩ፡፡

«ጨርሰናል ውሰዷቸው» አለ የዕለት ሁኔታ መዝጋቢው ፖሊስ፡፡ የፍ/ቤቱ ፖሊሶች በር ስር ወዳለችው ትንሽዬ የቆርቆሮ ቤት ወሰዱንና «ነገ በጠዋት እንመጣለን» ብለው ለጥበቃው ካስረከቡን በኋላ የካቴና ቁራኛዬን አንዱ ፖሊስ በጆሮው ጠጋ ብሎ የሆነ ነገር አለው፡፡

«እኔ ምን አውቃለሁ» አለ የካቴና ቁራኛዬ፡ እናም ካቴናው ተፈታ ወደ ቆርቆሮዋ ቤት ዘለቅን፡፡ «ፖሊሱ ምን ብሎህ ነው ምንአውቃለሁ» ያልከው ብዬ የእስር ጓደኛዬን ጠየቅሁት፡፡ «ብር ይዛችሁ ነው እንዴ የለንም የምትሉት» ነው ያለኝ አለኝ፡፡ እየገረመኝና እየደነቀኝ ጠባቧን የቆርቆሮ እስር ቤት ቃኘኋት፡፡ በቆሻሻ የተትረከረከች ባለ ሲሚንቶ ንጣፍ ናት፡፡ በአንዱ ጥጋት በኩል አንድ የማዳበሪያ ከረጢት በቁመት ተሰርቶ ተነጥፎበታል፡፡ እውስጥ የነበረው ብቸኛ እስረኛ እኛ ስንገባ «እፎይ የማወራው ሰው አገኘሁ» አለ፡፡ ብቻውን መሆኑ ጨንቆት እንደነበር ያስታውቃል፡፡ «ተቀመጡ» አለን ወደ አንድ ጎን እየተጠጋ፡፡ ሶስታችንም ተጣጥፈን ኩርምት ብለን ቁጭ አልን፡፡

«ሻይ ልጋብዛችሁ» አለን የቀደመው እስረኛ፡፡ «አለ እንዴ! ካለማ ውሃም እዘዝልን፡፡ ስለራበን ምሳ እንብላ» አልኩት በትንሽዬ ፌስታል ያንጠለጠልኩትን ምሣ ዕቃ እያወጣሁ፡፡ ቀኑን ሙሉ ምሳ አልበላንም ነበር፡፡ አስር ሰዓት ተኩል ሆኗል፡፡ ምሳና እራት በልተን እፎይ እንዳልን የቀደመው እስረኛ በምን እንደታሰርን ጠየቀን፡፡ ነገርነው፡፡

«እኔ ደግሞ ሻንጣ ተሸክማችሁ ስትገቡ እንደኔ የተያዛችሁ መስሎኝ ነበር» አለን፡፡ «ከፋ» እጅ ከፍንጅ ማለት ነው፡፡ እኔ በስጭት አለብኝ፡፡ ከፍ/ቤት ወደ ፖሊስ ጣቢያ እንደሄድ መደረጉ ሕሊናዊ እና ስነልቦናዊ ጥቃት አሳደረብኝ፡፡ ካኑ 11፤30 ሲሆን የተረከቡን ጥበቃ ፖሊሶች በስም እየጠሩ ለተተኪዎቹ አስረከቡን፡፡ ወዲያው አንዱን ተተኪ ፖሊስ ጠራነውና በትህትና «ሚስኮል» እንዲያደርግልን ጠየቅነው፡፡ «ሚስኮል የሚደረግለት ሰው ይደውልልሃል» አለኝ፡፡ «አዎ» አልኩት፡፡ «ሲደውል ምን ልበለው» አለኝ፡፡ አሁን ወረዳ 22 (ቀድሞው ፖሊስ ጣቢያ መሆኔን ወደ ወረዳ 5 ፖሊስ ጣቢያ ልንወሰድ እንደምንችል እንዲነግርልኝ ጠየቅኩት፡፡ «አንተ እስረኛ ስለሆንቀስ ስልክ ማነጋጋር ስለማትችል ነው» አለኝ፡፡ ይኼን ትብብር ማግኘቴም ተመስገን ነው አልኩና ተቀመጥኩኝ፡፡

እየመሸ ነው፡፡ ቆርቆሮዋ እስር ቤት ሕይወት የሚኖርባት አትመስልም፡፡ መብራት የለም፡፡ ትንሽዬ የተቆረጠች ሻማ አንድ ማገር ላይ ተጋድማለች፡፡ እዚህ መቆየት ካለብን ሻማ መግዛት

አለብን ማለት ነው እያልን፡፡ የቀደመው እስረኛ ሲጋራ፣ክብሪት፣ማስቲካ፣ሻማ ፖሊሱ እንዲገዛልን ጠየቀውና 10 ብር አውጥቶ ሰጠው፡፡ ግቢው ፀጥ ረጭ ብሏዋል፡፡ ፖሊሶች አልፎ አልፎ ሲጠራሩ ከመሰማቱ በቀር እኛ በየራሳችን ሐሳብ ሰጥመናል፡፡ ከምሽቱ 2 ሰዓት አካባቢ ድንገት በር ተከፈተና አንድ ሌላ እስረኛ ገባ፡፡ ፊቱ የበላለዘ፣በመጠጥ የደነዘዘ የሚመስል እስረኛ ነው፡፡ እንደገባ የሚያደርገው ጠፍቶበት ቆመ፡፡ ቁጭ በል አልነው፡፡ ነገር ግን የሚቀመጥበት ነገር አልነበረም፡፡ የሲሚንቶ አቧራ ላይ ዝርፍጥ ብሎ ተቀመጠ፡፡ «እዚህ አይሻልም አለው» የማይነተተውን የማዳበሪያ ከረጢት ንጣፍ ለመነተት እየሞከረ፡፡ «ተወው ባክህ! ለበረንዳ አዳሪ ደግሞ ይኼም ሲበዛበት ነው» አለ በተስፋ መቁረጥ፡፡ ይኼኛው እስረኛ በድብድብ የተያዘ ነው፡፡ «አሁን አራት ሆነናል፡፡ ከዚህ በላይ ሌላ እስረኛ አይመጣም፣ቤቱም አይበቃም» ስል ግምቴና ተናገርኩ፡፡

«አይምሰልህ! እዚህ ሰፈር ሌሊቱን ሙሉ እስረኛ ይመጣል» አለኝ፡፡ አላመንኩም፡፡ ምሽቱ እየገፋ ነው፡፡ ማዳበሪያው ምንጣፍ ላይ ተቀምጠን በአንድ በኩል ያለው ሲሚንቶ ግድግዳ ደገፍ ብለን፣ የእኔን የአንገት ፎጣ እግሮቻችን ላይ ጣል አድርገን ለማንቀላፋት ሞከርን፡፡ 3:30 ሲሆን፣ ሌላ እስረኛ መጣ፡፡ በጣም ልጅ ነው ዕድሜው ከ 16 - 18 ቢሆን ነው፡፡ በእጁ በላስቲክ የተጠቀለለ አምባሻ ይዟል፡፡ እንደገባ የያዘውን አምባሻ እንበላ እንደሆነ ጠየቀንና ሲጋራ እንዳለን ጠየቀን፡፡ ሲጋራ ሰጠነው፡፡ ለራሱ በረዥሙ ይለመጥጠው ገባ፡፡

«እናታቸውን! ወደ ቤት እናታቸውን ወደ ቤት ልገባ ስል ነው ፍግሮች የያዙኝ» አለ፡፡ «ፍግር» ማለት ሲቪል ለባሽ ፖሊስ መሆኑን ያወቅሁት ያኔ ነው፡፡ ይኼ በጣም ልጅ እግር እስረኛ በተጠረጠረበት ወንጀል ሲፈለግ ቆይቶ ደንገት የተያዘ ነው፡፡ እረፍት የለሽ ቅብጥብጥ፡፡ አንዴ ይቆማል፣አንዴ ይቀመጣል፡፡ «ሲጋራው ፓኬት ብልጭልጭ ወረቀት አለው» ሲል አንዱን እስረኛ ጠየቀው፡፡ ከውስጥ ሱሪው ውስጥ በጋዜጣ የተጠቀለለች ትንሽዬ ነገር እያወጣ፡፡

«ጋንጃ ነው?» ሌላው እስረኛ ጠየቀው፡፡

«ቀለባችን ነው» አለ በኩራት፣ ሀሺሽን መሰል አደንዛዥ እጽ እንደተፈቀደ ነገር «ቀለብ» ሲለው ገረመኝ፡፡ ልጁ እንዲሁ እንደተንቆራጠጠ ከምሽቱ አራት ሰዓት ሆነ፡፡ ከዛ አንድ ወፍራም እስረኛ ወደ እስር ክፍላችን ሁለት ኩርቱ ፌስታል ሙሉ ዕቃ ይዥ ገባ፡፡

«ምን አርገህ ነው?»

«ሲያቀብጠኝ ከሰው ዕቃ ገዝቼ፤ የሸጠልኝ ሰው አስያዘኝ» አለ፡፡ ይኼኛው እስረኛ ብርድልብስ፣አንሶላ፣ረዥም ፎጣ እና በሃይላንድ የውሃ ፕላስቲክ ሙሉ አረቂ ይዞ ገብቷል፡፡ እንደምንም ተጠጋግተን በአንድ መደዳ በአንድ ጎናችን ከወገብ በላይ ማዳበሪያው ላይ ከወገብ በታች በሲሚንቶ ላይ ተጋድመን ብርልብስ እና ፎጣውን ለብሰን ተኛን፡፡ በትንሹም ቢሆን ሙቀት ማግኘት ቻልን፡፡ ወዲያው በሃይላንዷ ውስጥ ያለችውን አረቂ አፍ ለአፍ ተቀባብለው ጨለጧት፡፡ ያቺ 2 ሜትር 2 ሜትር የምትሆን የእስር ክፍል በአረቂ ሽታ ታወደች፡፡

ይህ ሁሉ ነገር ለእኔ አዲስና እንደብርቅ የሚታይ ነው፡፡ ሽንት ቢመጣ ከዚያች ክፍል መውጣት የለም፡፡ ደግነቱ ያቺ የሃይላንድ ውሃ መያዣ ፕላስቲክ ለሁለት ሰው ሽንት መክፈያ ጠቀመች፡፡ ከምሽቱ አራት ሰዓት ተኩል ሌሎች አራት እስረኞች መጡ፡፡ ሞባይል ሊሠረቅብን ሲል ተደባድበን

ነው የተያዝነው አሉ፡፡ እንደመጡ እግራችን ስር ጥቅልል ጥቅልል ብለው ተኙ፡፡ መጠጥ ስለጠጡ የሲሚንቶው ቅዝቃዜ ምንም አልመሰላቸውም፡፡ እዚያች ጠባብ ክፍል ውስጥ የእስረኛው ብዛት ዘጠኝ ደረሰ፡፡

ከምሽቱ 5:30 ሲሆን «መኪና መጥቷል ሁለት ሁለት ሆናችሁ ውጡ» ተባልን፡፡ እኛም ከኛው ጫማ በተፈቱ ረዣዥም የጫማ ክሮች አንድ አንድ እጆቻችን ጥፍንግ ተደርገው ታሰሩ፡፡ ሁለት ሰው እዚያው ሲቀር ሰባተችን በጫማ ክር ተሳስረን የፖሊስ ፒክ አፕ መኪና ላይ ተሰቅለን ወደ ወረዳ 5 ፖሊስ ጣቢያ መረሽን፡፡

ያኔ «ተራራ እገፋለሁ
መከራ እገፋለሁ
እጣዬ ነው ብዬ ለምን እከፋለሁ» የሚለው የጓደኛዬ ግጥም ወደ ሕሊናዬ መጣ፡፡

(ይቀጥላል)

/ወሰንሰገድ ገብረኪዳን፣የሐራምቤ ጋዜጣ አሳታሚና ቃና አዘጋጅ ነበር/

# በኢትዮጵያ አረንጓዴ ርሃብ፤አፈ ታሪክ ወይንስ እውነታ?

*በተጋ ሌንዳዶ (ዶ/ር)*
*(ከአትላንታ)*

ይህ ጽሑፍ የቅርብ ጊዜው ድርቅ፣በሽታ፣ምግብ አለመመጣጠን፣ርሃብ እንዲሁም በደቡባዊ ኢትዮጵያ ያለጊዜያቸው ለሚሞቱ ዜጎች መታሰቢያ ነው፡፡ ዓላማውም በአምባቢዎች ዘንድ ምክንያታዊ፣ሃይማታዊና ሰብዓዊ ምላሽ ለማመንጨት ነው፡፡ ከመነሻውም እንደ ወገንተኝነት ወይም እንደ ፖለቲካ ቅስቀሳ ተደርጎ መተርጎም እንደሌለበት አምናለሁ፡፡ ፍላጎቴም አንባዎች በብልሃት እንዲጸልዩ፣ለጋሾች በኃላፊነት ስሜት እንዲለግሱና መንግሥት የተነሳሽነት ስሜት እንዲኖረው ለመናገር ነው፡፡ በአጭሩ፣ይህ የአካባቢያዊ ፍትሕ (Environmental Justice) ጥሪ ነው፡፡

አስከፊ ግን አስፈላጊ ጉዳዮችን ሳነሳ ኃላፊነት እንደሚሰማው የሞራል ወኪል፣ቀላል አስተሳሰብ እንዳለው አዋቂ ሰውና እንደ የዓለም አቀፍ ልማት ፕሮፌሽናል፣ብሎም እንደ የአካባቢ ጥበቃ አቀንቃኝ መሆኑ ግልጽ ይሁን፡፡ ይህ ጽሑፍ እጅግ ከማመሰግናቸው ግለሰቦች ጋር በተደረጉ ዝርዝር ግምገማዎችና ውይይቶች ላይ መሠረት ያደረገ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ደቡብ ምዕራብ ክፍል በአረንጓዴ ተክሎቹ ይኩራራ ነበር። ከአንድ ክፍለ ዘመን በፊት የመሬቱ 40 በመቶ በደን የተሸፈነ ነበር። ንጉሰ ነገስት ኃይለ ሥላሴ በ1930 በመጡ ሰዓት የደኑ መጠን ወደ 10 በመቶ ተመናምኗል። በ1974 ከሥልጣን ሲወርዱ ወደ 4 በመቶ ቀነሰ። በገጠራማ መሬት ላይ የደርግ የሕዝብ ባለቤትነት ፖሊሲ መምጣትን ተከትሎ የሐገሪቱን ደን አርሶ አደሮች ያለ ሐሳብ ጨፈጨፉት። በ1978 በደን የተሸፈነው መሬት ግምት 3 በመቶ ብቻ ነበር። በአሁን ሰዓት 2 በመቶ ብቻ ይገመታል።

በተለምዶ ሳህል ከሚባለው ከሳሃራ በረሃ የበረሃነት መስፋፋት (Desertification)ተጽዕኖና ከሌሎች ወሳኝ ምክንያቶች ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ አየር ጠባይ ወደባሰ ሀሩርና ሞቃታማ ተለውጧል። በሚያቃጥለው የፀሐይ ብርሃን የሚከሰተው ሞቃት አየር የእርጥበት በእድሜ የገፋ ሰው በከፍተኛ ቦታዎች አካባቢ በአየር እጥረት ምክንያት የመተንፈስ እንከን ሊገጥመው ይችላል። የሙቀት ማዕበሉ በዝቅተኛ ቦታዎችም ጭምር ለመቋቋም የሚያዳግት ሊሆን ይችላል። የእጽዋት እና የእንስሳት የተፈጥሮ መስተጋብር (eco-system) በደን ጥበቃ፣ልማትና አስተዳደር ተከታታይ ቸልተኛነትና ብዝበዛ ምክንያት የእፀዋትና የእንስሳት ተፈጥሯዊ መስተጋብር (eco-system) እጅጉን ተጎድቷል። በቅርቡ ከተደረገው ከሚሊንየሙ የዛፍ ተከላ ጥረት በዘለለ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ውስጥ በክልሉ ጎልተው የሚጠቀሱ የደን ልማት ፕሮጀክቶች አልነበሩም። በተቃራኒው በጋሞ እና ከፋ በመቶ ሄክታሮች የሚለካ መሬት ለእርሻ ሲባል ተጨፍጭፏል። በቅርብ ዓመታትም በባሌ እና በአርሲ ዞኖች በእሳት ምክንያት ከፍተኛ መጠን ያለው የተፈጥሮ ደን የማይተካ ጉዳት ደርሶበታል።

የእርሻ መሬቱ ምርታማ ላለመሆኑ ሌሎች ተፅዕኖ አድራጊ ምክንያቶችም አሉ። ከነዚህም መካከል የሕዝብ ቁጥር መጨመር፣ከመጠን ያለፈ የከብቶች ግጦሽ፣በመሸርሸርና ማዳበሪያን በአግባቡ ባለመጠቀም የአፈር ለምነት መቀነስ፣ከዘመናዊ ሜካናይዝድ እርሻ እንዲሁም ከከተማና ከኢንዱስትሪ መስፋፋት ይልቅ ለገጠሩ ነዋሪ ባሕላዊ እርሻ የኑሮ መሠረቱ ስለመኖሩ የሚያስረግጡ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲዎች መኖራቸው ይገኙበታል። እርሻ እንደ የእጅ መሣሪያዎች እና የተጠመዱ እንስሳዎች ባሉ ኋላ ቀር የማምረቻ ዘዴዎች ደካማውን አርሶ አደር እርሱና ቤተሰቦቹ ከሚበሉት ያለፈ እንዲያመርት አይፈቀድለትም። ከጋሞ አካባቢ በስተቀር እርከን እና መስኖ እምብዛም በክልሉ አይታወቁም። ለዓመታት ያህል ሕዝቡ ወቅቱን ጠብቆ በሚመታ ዝናብ ላይ ጥገኛ ሆኖ ቆይቷል። እነዚህ ሁሉ እንቅፋቶች እያሉ ከደሀው አርሶ አደር የተትረፈረፈ (Surplus) ምርት መጠበቅ እንዲሁም አግባብ የሌለው እና ሥነ - ምግባር የጎደለው ነው።

ጠንካራ በሬዎች እንደልብ እና መሬት በገፍ በነበረበት ባለፉት ጊዜያት እንደ ዳቦ ሥርዓት ያለ የተደራጀ ጉልበት ጥቅም ላይ የሚውልበት የጋርዮሽ ልማት በጣም ውጤታማ ነበር። ሆኖም አሁን የቤተሰብ የንብረት ይዞታ እጅጉን ቀንሷል፣እንዲሁም በወላይታ፣ሲዳማ እና ከምባታ አካባቢዎች ከጥቂት ወራት በፊት ባደረኩን አነስተኛና የአጭር ጊዜ ጥናት በእያንዳንዱ ቤተሰብ የሚገኘው የበሬ መጠን 0.45 እንደሆኑ ይገመታል።

ስለዚህም ተከታታይ ድርቅ እና ርሃብ እንደ የደን ጭፍጨፋ፣የላይኛው የአፈር ክፍል መሳሳት፣ለከት ያለፈ ግጦሽና የመሳሰሉት ክስተቶች ውጤቶች ናቸው:: መጠነ ትንሽ (scanty) እና ወቅቱን ያልጠበቀ (erratic) ዝናብም ሌላው  መንስኤ ነው:: ፈጥኖ አዳጊ እፅዋቶች ቱሪስቶችን ሊያሳስቱ ቢችሉም በነባር ነዋሪዎች ላይ አይሰሩም:: ለአጭር ጊዜ የደረቁ ተክሎች ለምልመውና ሳር በቅሎ በአርሶ አደሩ ጓሮ አካባቢ የሚገኝ ነገር ሁሉ አረንጓዴ ሊለብስ ይችላል:: አርሶ አደሩ ያልደረሰ እና ጥቅም ላይ የማይውል ምርት ለመሰብሰብ ብቻ ባህላዊ ሰብሎችን ሊዘራ ይችላል:: በ1992 ወላይታን እና ከምባታን በጎበኘሁ ጊዜ በደቡብ ኢትዮጵያ የተመለከትኩት ይህንን ነበር:: መሬቱ አረንጓዴማ እና ተክሎቹ ደግሞ በሚያስደምም መልኩ አረንጓዴ ነበሩ:: አፈሩ እርጥበት እና ጭቃማ ነበር:: ነገር ግን አርሶ አደሮቹ ቀጫጫ እና ደካማ ነበሩ:: ሕፃናቱ የምግብ አለመመጣጠን ምልክቶች የሚሳይ የተወጠረ ሆድ የደፈረሱ ዓይኖች ነበራቸው:: ከዚህ በመነሳት እነዚያ አርሶ አደሮች ሰነፍ እና ማምረት የማይችሉ እንደሆኑ የተሳሳተ ድምዳሜ ሊሰጥ ይችላል::

በ1970 ዎቹ  በተማሪዎች የተመራው አብዮት «መሬት ለአራሹ» የሚል መፈክር ነበረው:: በዚያን ጊዜም አልደገፈፍኩትም፣አሁንም አልደግፈውም:: ከሁሉም በላይ፣አራሹ ደሃው አርሶ አደር ነበር:: በቦታው በማይገኙ ባለቤቶች የተያዘ መሬት ባለቤትነቱ መሬት ላልነበራቸው አርሶ አደሮች በማደሉ ረገድ ልስማማ እች ይሆናል:: ምንም እንኳን በድብልቅ አልያም ነፃ ገበያ ኢኮኖሚ በሚባለው ዘመን ከሙኒዝም ውጤታማ እንዳልሆነ መረጋገጡ ቢሰነብትም መንግሥት በኮሙኒስታዊ «መሬት - ለአራሹ - አብዮት» ላይ የሙጥኝ ያለ ይመስላል::

በፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ሁሉም አርሶ አደሮች ባለቤት ሳይሆን ባለይዞታ ይሆኑ ዘንድ ሁሉም መሬት የሕዝብ ንብረት ነው:: አርሶ አደሮቹ ኃላ ቀር እና ያልሰለጠነ የአመራረት ዘዴዎች አናሳ ይዞታ አቅም አዳም ሊደርሱ ልጆቻቸው በመከፋፈሉ የምርት መጠኑ እጅጉን ተመናምኗል:: የጉዳት መጠን የተሰገሰገ የሕዝብ ብዛት (densely populated) ባለባቸው እንደ ጉራጌ፣ከምባታ፣ወላይታ፣ጠምባሮ እና የመሳሰሉት አካባቢዎች በግልጽ ይታያል:: አስገራሚ የተራራ አስተራረስ ቴክኒኮች በከምባታ ብቻ ይታያሉ:: የሚደነቅ እና የሚደገፍ የእርሻ ሥራ ! ነገር ግን ሕዝብ ለደረሰ የርሃብ እና የበሽታ አደጋ የተጋለጠ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል:: እነዚህ ሕዝቦች መንስኤ ብዙ እና ተደጋጋሚ በሆኑ ችግሮች ሁሉ ለሙሉ ከመውደማቸው በፊት «ሊታደጋቸው» የሚችል ሰው አለን?

ርሃብ ወደ ዘገምተኛ ሞት የሚያመራ አስከፊው የስቃይ ዓይነት ነው:: አንዳንድ ጫማ ጠራጊዎች «እዚህ ዘገምተኛውም ሞት ከመሞት ይልቅ ወደ ጦርሜዳ መሄድን እንመርጣለን» ሲሉ አጫውተውኛል:: ከጥንት ጀምሮ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች የተትረፈረፈ ምግብ ያመርታሉ:: በኑሮዋቸው ደስተኞች በመሆናቸው የአርብቶ አደርን ወይም የስደተኛ ሕይወትን አልመረጡም:: ሌሎች ሕዝቦች ከተለያዩ ቦታዎች መጥተው እነርሱ ጋር በመስፈር እንግዳ ተቀባይነታቸውን ያጣጥማሉ:: መጤዎቹ መነቃቃትን እና ጉልበትን በማምጣት ነባሮቹን

ያገዝፏቸዋል፣ ነገር ግን የነበራቸውን ጥቂት የተፈጥሮ ሐብት ይጋሯቸዋል:: እንዲህ ዓይነቱ ማህበራዊ መስተጋብር በሌላ የሀገሪቱ ክፍል ርሃብ ሲከሰት የየወቅቱ መንግሥት በርሃቡ የተጠቁትን ሕዝቦች እንደ ጋሞ፣ከፋ፣ወላይታ፣ባሌ፣ አርሲ እና ጎፋ በመሳሰሉት ቦታዎች በማስፈር ሲበረታታ ቆይቷል:: ይህ መጤ የሆኑት ሕዝቦች የአላቂ የተፈጥሮ ሐብቶች ተቋዳሽ እንደመሆናቸው በአርሶ አደሮቹ ላይ የተወሰነ ግፊት አሳድሮባቸዋል:: ተከትሎም ርሃብም ሕዝቦቹ የሚጋሩት ሌላው ሰቆቃ ሆነ:: እውነታው እንዳሳየው የሶሻሊስት ኢትጵያ (1974 - 1991) ውጤት ድህነት እና አብረውት የሚመጡትን እርግማች ሁሉ የመጋራት ሕይወት ነበር::

በሻሸመኔ - ሶዶ መንገድ ትይዩ በአላባ እና ሰሜን ሀዲያ አካባቢዎች የሚታየው የመሬት መንሸራተት ያስደነግጣል:: የላይኛው የአፋር ክልል ከመሸርሸሩ ባሻገር ከ 2 እስከ 3 ሜትር ስፋት፣4 ሜትር ጥልቀት እና በመቶዎች የሚቆጠር ሜትር ርዝማኔ ያላቸው ክፍተቶች በመሬት መሰነጣጠቅ ምክንያት ተፈጥረዋል:: ተመሳሳይ ክስተት በአባያ ሀይቅ አካባቢ እና በሌሎች የስምጥ ሸለቆ ቦታዎች ይታያል:: ሁኔታዎቹን ለመቀነስ ጥንቃቄ የተሞላበትና የተጠናቀረ ጥናት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል:: በዚህ አረንጓዴው ርሃብ ትንተናችን ቻልተኝነት እና አላዋቂነትን መውቀሳችንን አንዘንጋ:: እንደ እንሰት፣በይና፣ቦዬ፣ስኳር ድንች፣ካሳቫ እና የመሳሰሉት ድርቅ ተቋቋሚ ተክሎች በአንዳንድ የደቡብ ክፍል ውስጥ አይታወቁም:: በቅርቡ በሀዋሳ ጥቁር ውሃ አካባቢ አንድ እርሻ ጎብኝቼ ነበር:: ሦስት ዓይት የስኳር ድንች ዝርያዎችን አይቻለሁ:: አንዲት የጉራጌ ተወላጅ ሴት ገበሬ ከየት እንዳገኘቻቸው ጠየኳት:: ባለቤቷ ከወላይታ ዞን እንዳመጣቸው ነገረችኝ:: ለጎረቤቶቿ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲያውቋቸው አድርጋለች:: ተከትሎም በሲዳማ ዞን የሚገኙ አርሶ አደሮች እነዚህን የስኳር ድንች ዝርያዎች መትከል ጀመሩ::

በአጠቃላይ ከእንሰት ተጠቃሚ ሕዝቦች በስተቀር ኢትዮጵያን ድርቅ ተቋቋሚ እህሎችን፣ፍራፍሬዎችንና አትክልቶችን እምብዛም አይመገቡም:: አንዳንድ አትክልቶች ለማደግ አጭር ጊዜና ለመለምለም ጥቂት ጥረት የሚጠይቁ ናቸው፣ ሆኖም አያሌ አርሶ አደሮች ይህንን የሚያውቁ አይመስሉም:: ስለዚህም ሕዝቡ የተለያየ የአመጋገብ ባህልን እንዲያዳብር ጠንካራ ትምህርት ሊሰጠው ያስፈልገዋል::

እርሻ እና ግብርና የገጠሩ ኑሮ ሁለት ተመሳሳይ የሥራ መስኮች ናቸው:: አርሶ አደር በትንሽ ይዞታ ለእርሱና ለቤተሰቡ ቀለብ ብቻ የሚያመርት ነው:: ገበሬ በከፍተኛ መጠን እና በተሻለ ጥራት ለንግድ የሚውል ምግብን የሚያመርት ነው:: በእርግጥ በዚህ በአሜሪካ አርሶ አደሮች የሉንም:: እዚህ ከአጠቃላይ ሕዝብ 4 በመቶ የሚያህለው ብቻ በንግድ ኢንስትሪያዊ ግብርና ላይ ይንቀሳቀሳል:: ለሀገር ውስጥ እና ለዓለም አቀፍ ገበያ የተትረፈረፈ ምርት የሚያመርቱት እነዚህ ገበሬዎች ናቸው:: ማሽነሪዎችን ይጠቀማሉ፣ብቁ የሰው ኃይል፣ የተሻሻሉ ምርጥ ዘሮችን፣በሳይንስ እና በቴክኖሎጂ የረቀቁ ዘዴዎችን፣ቴክኒኮችን እና የግብዓት እና የውጤት ሥርዓቶችን በሥራ ላይ ይውላሉ:: ገበሬዎቹ ለንግድ እና ኢንዱስትሪያዊ ግብርና እጅግ ሰፋፊ መሬቶችን በባለቤትነት በመያዝ ወይም ሊዝ በመውሰድ ውስብስብ ማሽኖችን እና

መሣሪያዎችን ይጠቀማሉ:: የኢትጵያ አርሶ አደሮች «ገበሬዎች» ለሚለው ስያሜ ብቁ አይደሉም፣ ምክንያቱም ከስያሜው ጋር የተያያዙ ብቃቶች ሁሉ የሏቸውም:: ሆኖም በገጠራማው ክፍል «ገበሬ» ተብሎ ሲጠራ ቆይቷል:: ላላፉት አራት አስርት ዓመታት የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች አይደለም ለከተማው ሕዝብ የተትረፈረፈ ምርት ለማቅረብ ይቅርና እራሳቸውን እንኳን ለመመገብ ተስኗቸው ቆይተዋል::

## ተጠቃሽ ቸግሮች እና አስፈላጊ መፍትሔዎች

1. **አካባቢያዊ ፍትሕ (Environmental Justice):-** ከዓለም ሙቀት መጨመር (በኢንዱስትሪያዊ ብክለት ሳቢያ) እና ከድህነት (በተለይም የተፈጥሮ ሀብትን በአግባቡ ባለመተቀም፣ፍትሃዊ ባልሆነ ብዝበዛ፣ በተጓደለ አስተዳደር ወይም በሙስና ምክንያት) ጋር በተያያዘ የአየር ንብረት ለውጥ ዓለም አቀፋዊ ትኩረትን የሚጠይቅ ዋና የዓለም ችግር ሆኗል፣የመዕድን መመናመን፣የደን መጨፍጨፍ፣የዱር ሕይወት ብዝበዛ፣የአፋር እና የውሃ ሀብት እያለቀ መምጣት እና የመሳሰሉት ክልላዊ እርምጃዎችን ይጠይቃሉ:: በዓለም አቀፍ ብክለት ተጠቂ የሆኑ ሀገራት ለደረሰባቸው ጉዳት ሊካሱ ይገባል:: በተቃራኒው "ግሎባላይዜሽን" እውን እና ፍትሀዊ ነው ከተባለ አካባቢን የማይበክሉ ሀገራት ማበረታቻ ሽልማት ሊሰጣቸው ይገባል::የምዕራቡ ኢንዱስትሪያዊ ሀገራት እና ቻይና፣ሕንድ፣ብራዚል፣ሩሲያ፣ደቡብ አፍሪካ፣አውስትራሊያ፣ኒውዚላንድ እና የመሳሰሉትን ጨምሮ ሌሎች እየፈለቁ ያሉ የኢኮኖሚ ኃይሎች ለ "ዓለም አቀፍ መንደር" ደህንነት ሲባል በካይ ቴክኖሎጂዎችን ሊያስወግዱ ወይ በአፋጣኝ ሊቀንሱ ይገባል::
2. **ያልተገባ የሕዝብ ቁጥር መጨመር:-** ኃላፊነት የጎደለው እና ኢ-ሞራል ውልደትን እና አስተዳደግን ለማረም ባሕላዊ እና ሞራላዊ ትምህርቶች ሕች፣የጤና አጠባበቅ እና የኑሮ በዘዴ ትምህርቶች፣ተነሳሽነትን የሚፈጥሩ ትምህርቶች እና የመሳሰሉት:: ለምሳሌ ኃላፊነቱን ለማደጎ ቤተሰቦች፣ድርጅቶች እና ለሕዝባዊ ተቋማት ለማስተላለፍ ብቻ ሕፃናትን መውለድ ኢ-ሞራል ነው::
3. **የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ :-** አርሶ አደሩ ትንሽ እና ምርታማ ባልሆነ መሬት ላይ ታጋች ሊሆን አይገባም:: የሀብት ዝውውር እና ልውውጥ እንዲኖር አቅም ያለው አርሶ አደር ንብረቶችን እንዲገዛ፣ይዞታቸውን እንዲያጎለብት፣መሬቱን እንዲሸጥ እና ገዝቶም እንዲሸጥ ሊፈቀድለት ይገባል:: አብዛኞቹ እንደ ኢንሹራንስ እና ባንክ ዓይት የገንዘብ ተቋማት መሬትን እንደ ግዑዝ ንብረት ይቆጥሩታል:: ትክክለኛ የመሬት አጠቃቀም ተሞክሮ ተፈጻሚ እንዲሆን እርሻ በኢንዱስትሪያዊ ሥርዓት መቀየር አለበት:: መሬት ለምግብ ማምረቻ፣ለከብቶች ግጦሽ፣ለኢንዱስትሪ ቦታዎች፣ለደን እና ለዱር እስሳት ጥበቃና ልማት ተብሎ ለፍቃደኛ አራሾች መከፋፈል አለበት::

4. **የአመራረት ዓይት እና ዘዴ፡-** በሚደጎም የጋርዮሽ ግብርና፣በኢንዱስትሪያዊ ልማት፣በጎጆ ኢንድስትሪ ልማት ላይ እና ውጭ ንግድ ሰብሎች እና በሀገር ውስጥ የሚውሉ ምግቦችን ለማምረት በተዋቀረ መልኩ ለሚሰማሩ የገጠሩ ማህበረሰቦች አስፈላጊው ትኩረት እንዲሰጣቸው የአርሶ አደር እና የገበሬ ልዩነት በግልጽ መታወቅ አለበት፡፡
5. **የአስተሳሰብ ለውጥ፡-** እንደኔ እምነት ኢትዮጵያን «ከዚህ በኋላ እንዳሃራቡ» ግብርና መር ኢንዱስትሪ ሳይሆን ግብርና እራሱ ኢንዱስትሪ መር ሊሆን ይገባል፡፡ መጠነ ሰፊ ምርት እና እንደ አቀዝግዞ ማየትና ቴክኖሎጂ፣ ምግብና በኢንዱስትሪ ሂደት የማሳለፍ፣አግባብ ያለው የምግብ አያያዝ እና የማከፋፈያ ሥርዓት ያሉ ምግብን የማቆያ ዘዴዎች ርሃብን ሊቀንሱና እርዛትን ከኢትዮጵያ ሊያሰወግዱ ይችሉ ይሆናል፡፡ ይህ እንዲሆንም በብሔራዊ እና ክልላዊ የፖለቲካ አመራሮች አይምሮ የአስተሳሰብ ለውጥ አስፈላጊ ነው፡፡
6. **የምርት ዓይነት**፡- እንደ የቃጫ ተክል፣የሸንኮራ አጋ፣ጥጥ፣ቡና፣ኣ፣ሻ ቅጠል፣ኦቾሎኒ፣ባህር ዛፍ እና የመሳሰሉት ለውጭ ንግድ የሚውሉ ሰብሎች ለምግብነት የሚውሉ ሰብሎችን ምርት ተጋፍተዋል፡፡ እንደ ጤፍ እና በቆሎ ዓይነት አንዳንድ ለምግብነት የሚውሉ ሰብሎችም የንግድ ሰብል እየሆኑ መጥተው አርሶ አደሩ እራሱ ለቤተሰቡ ቀለብ እንኳን ሊያውላቸው ያዳግተዋል፡፡ በጃንሆይ ዘመን በሻሸመኔ - ሀዋሳ መንገድ ያለው ሰፊ መሬት ለቃጫ ተክል ማምረቻነት ይውል ነበር፡፡ ወንጂ እና መተሃራ የስኳር እርሻዎች ሰፋፊ ቦታዎችን ይዘው ቆይተዋል፡፡ ደርግ ለቡና እና ሻይ ቅጠል እርሻ በከፋ ቤቤካ የነበረውን የተፈጥሮ ደን መንጥሯል፡፡ የአሁኑ መንግሥትም እጅግ አስፈላጊ የሆነውን የውጭ ምንዛሬ ለማመንጨት የአበባ ምርትን በስፋት ጀምሯል፡፡ ነገር ግን ሦስቱም መንግሥታት ለአካባቢው ተጠቂነት ተገቢውን ጥንቃቄ ባለመውሰድ በዚህ ዓይነት የአጭር ጊዜ ግቦች የተገፈፉ ይመስላሉ፡፡ የአበባ ምርቱ ምንም እንኳን በሚሊዮኖች የሚቆጠር የውጭ ምንዛሬ ሊያስገኝ ቢችልም ከሰብል ምርት ጋር ፉክክር ይዟል፡፡ አናሳ የምርት መጠንን የሚስከትለው አፈር ለምነት መቀነስ በእንዲህ ያሉ የውጭ ንግድ ሰብሎች ምክንያት ሊሆን እንደሚችልም ልብ ሊባል ይገባል፡፡ በሀገሪቱ የምግብ ዋስትና ለማምጣት ከውጭ ንግድ ሰብሎች ይልቅ ለምግብ ምርት ውድሚያ ሊሰጠው ይገባል እላለሁ፡፡ እንዲሁም በዚህ ወላዋይ የዓለም ኢኮኖሚ ወደ አበባ ምርት ከመጥለቁ በፊት ለኢትዮጵያ በምግብ እራሷን መቻል አይሻላትምን?
7. ደቡብ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያ የዳቦ ቅርጫት ነው የሚባለው አፈ-ታሪክ ተወግዶ በማያስተማምነው ዝናብ ምክንያት በክልሉ ለሚከሰተው የምግበ እጥረት ችግር ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ተገቢ የሆነው ክልላዊ እርምጃ እንደ ኦሞ፣ቢላቴ፣አባያ እና የመሳሰሉትና ወሳኝ ወንዞች እና ሃይቆች ጥቅም ላይ ማዋልን ከግምት ሊያስገ ይገባል፡፡
8. **የኢንዱስትሪ ቦታዎችን ማዕከላዊነት :-** ባለፉት አስርተ ዓመታት በአዲስ አበባ እና አካባቢዋ አያሌ ኢንዱስትሪዎች ተገንበተዋል፡፡ እንደ አርባ ምንጭ፣ዲላ እና ሶዶ ያሉ ከተሞች የሥራ እድልን በሚፈልጉ አቅም ባላቸውና የተማሩ ወጣቶች የተጨናነቁ ናቸው፡፡ ኢኮኖሚውን

ለማሰባጠር እና ያልተገባ የከተማ ምስረታን ለማስተካከል ቀላል እና ከባድ ኢንዱስትሪዎች ወደነዚህ ከተሞች ሊዛዋወሩ እና /ወይም አዲስ ሊመሰረቱ ይገባል፡፡

## መደምደሚያ

ይህንን ጽሑፍ ለማሳጠር ያህል ወደ መደምደሚያ ሐሳቦቼ በአፋጣኝ ልለፍ፡፡ አስተባባሪዎቹን፣መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እና ጠጠቂዎቹን እስኪበቃን ድረስ ልንወቅሳቸው እንችላለን፡፡ በትክክልም ለረጅም እና ለብዙ ጊዜያት ይህንን ስናደርግ ቆይተናል፡፡ ዝምታን የመረጠው ምሁር፣እራሱን ያገለለው ዲያስፖራ እና የተሰደደው ፕሮፌሽናል ልቦናው እና ዓይምሮው በሚያዘው መንገድ የኃላፊነት እርምጃዎችን የሚወስድበት እና ተጨባጭ ሚናዎችን የሚጫወትበት ጊዜው አሁን ነው፡፡ ሌሎችን በመውቀስ ወይም እራስን ለዘላለሙ በማግለል የችግሩ አንድ አካል መሆን ቀላል ነው፡፡

የኢትዮጵያ ዲያስፖራ እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላቶች በደቡብ ኢትዮጵያ እየተንቀሳቀሱ ከሚገኙነት የመንግሥት አካላት ወይም መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች (በቅርቡ ከወጣው ሕግ አንፃር በሀገር ውስጥ የሚገኙ ካሉ) ጋር በሚከተሉት ደረጃዎች ላይ አብረው ሊሠሩ ይችላሉ፡፡

**ነፍስ አድን፡-** የመንግሥት አካላት፣መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣በጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ሃይማኖታዊ ወይም ሃይማታዊ ያልሆኑ፣ ሀገር በቀል ወይም ምንጫቸው ውጭ የሆኑ አካላት በነፍስ አድን ጥረቱ ላይ ተባብረው ሊሰሩ ይገባል፡፡ ግለሰብ ለጋሾች ርሃብን ለመከላከል በገንዘብም ሆነ በምግብ፣በትራንስፖርት፣በመድኃኒት፣በአልባሳት እና በመሳሰሉት መንገድ መሳተፍ ይገባቸዋል፡፡ በጥረቱ ላይ የሚሳተፉ አስተባባሪ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የጊዜውን አስፈላጊነት ሊያሳውቁ ይችላሉ፡፡

**መልሶ ማቋቋም** ፡-_የነፍስ አድኑ ሥራ አንዴ ከተጠናቀቀ መልሶ ማቋቋም ይከተላል፡፡ የነፍስ አድኑን ጥረት ሳያስተጓጉል የተጎጂውን የአጭር ጊዜ የሰው እርዳታ በማራዘሙ ረገድ መልሶ ማቋቋም ሊከተል ይችላል፡፡ ይህም ተጎጂው እራሱን መቻል እስኪችል ድረስ ያጣቸውን ንብረቶች መልሶ እንዲያገኝ ማድረግን ይጨምራል፣ በተጠቃሽም ቤት፣የጤና አጠባበቅ፣ሬሽን ምግብ እና ሌሎች አስፈላጊ ግብዓቶች፡፡

**ልማት** ፡- ግለሰቡ በመልካም ሁኔታ ከተቋቋመ የረጅም ጊዜ ግቡን ሊያስብ ይችላል፡፡ ከግለሰቡ ጋርም አብሮ በማሰብ የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶች፣ጥሬ ዕቃዎች፣ዘሮች እና ቴክኒኮች ማቅረብ ይቻላል፡፡ ለዚሁ ጉዳይ የተቋቋሙ ኤጀንሲዎች የተጎጂውን ኑሮ ለማሻሻል አነስተኛ ብድሮችን እና የመሳሰሉትን ሊያመቻቹ ይችላሉ፡፡ አንድ በጎ አድራጊ ግለሰብ ጉዳቱ በደረሰበት ቦታዎች በተቋቋሙ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በኩል አንድ ቤተሰብ ወይም አንድ ሕፃን ስፖንሰር ሊያደርግ ይችላል፡፡

**/ቴጋ ሌንዳዶ (ዶ/ር)፣ በአሜሪካ - አትላንታ የልማት አማካሪ ሲሆኑ ቀድም ሲል በማዕከላዊ ኢትዮጵያ የደን ልማት ዳይሬክተር እንዲሁም በደቡብ አፍሪካ የUNDP/ የደን ልማት ኢንጂነር ሆነው አገልግለዋል።/**

# የፕሬዚዳንት አል-በሽር ጉዳይ፤የአፍሪካ ሕብረት ራስ ምታት

**በፍጹም ማሞ**

የሱዳን መንግስት እና መንግስት ይደግፈዋል የሚባለው «ጃንጃዊድ» ሚሊሺያ በ2003 በአል-በሽር መንግስት ላይ ወታደራዊ ተቃውሞአቸውን ከገለፁ ቡድኖች ጋር በጀመሩት (የዳርፉር) ጦርነት ከ300ሺህ በላይ ሰዎች ህይወታቸውን አጥተዋል። (ምንም እንኳን መንግስት 10ሺህ ብቻ ናቸው ብሎ ቢከራከርም።) እንዲሁም 2.7 ሚሊዮን የሚደርሱ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል። ለዚህ ውድመትና ውድቀት ተጠያቂ የተደረጉት ፕሬዚዳንት አል-በሽር በጦር ወንጀሎችና በሰብአዊ ፍጡር ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ተጠርጥረው ዓለም ዓቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት ጉዳያቸው እንዲታይ ሆኖ በየካቲት 25/2001 ተወስኖባቸዋል - ውንጀላዎቹን ሙሉ በሙሉ ውድቅ ቢያደርጉትም።

በፕሬዚዳንት አል-በሽር ላይ የተቆረጠውን የእስር ማዘዣ ተከትሎ ብዛት ያላቸው አስተያየቶች ተደምጠዋል። አብዛኞቹም ከ«ፍትሕ» እና ከ«ሰላም» ጋር የዓለም ዓቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማየት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። ሁኔታዎች እየተባባሱ እንጂ እየላሉ ባልሄዱበት እውነታ ሱዳን እና አል-በሽር የፍርድ ቤቱን ውሳኔ በፍፁም ተቀባይነት እንደሌለው አበክረው እየገለፁ ይገኛሉ። ሱዳን ወሳኔውን እንድታከብር ከተለያዩ የዓለማችን ሀገሮች የሚሰነዝሩ ማስጠንቀቂያዎች ትርጉም ያላቸው አልመስል ብለዋል።

ምንም እንኳን ለአመታት የሱዳን መንግስት የዳፉርን ጉዳይ በተመለከተ ይህ ነው የሚባል ተጨባጭ እርምጃ ሳይወስድ ቢቆይም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት (ተ.መ.ድ) ሴክሬታሪ ጄኔራል ባን ኪ-ሙን አል-በሽር በዳፉር ወንጀሎችን ፈፅመዋል የተባሉ ተጠርጣሪዎችን በአገራቸው በፍርድ ቤቶች እንዲዳኙ ሊያዙ ይችላሉ የሚል ተስፋ ያላቸው መሆኑን ገልፀዋል። ዓለም ኣቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት በአል-በሽር ላይ እንደተከፈቱት ያሉ ወንጀሎችን የመዳኘት ስልጣን የሚኖረው አገሮች (አባል የሆኑም ያልሆኑም) በራሳቸው ጉዳዩን መፍታት ካልቻሉ ወይም የማይችሉ ከሆነ ነው።

ፕሬዚዳንት አል-በሽር ባለፈው ሳምንት ከግብፅ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አህመድ አቦል ጌይት እና ከስለላ መስሪያ ቤት ዋና ሃላፊ ኦማር ሱሌይማን ጋር ተገናኝተው የነበረ ሲሆን ታዛቢዎች ግብፅ ከፍተኛ የመንግስት መልዕክተኞቿን ወደ ሱዳን መስደዷ አል-በሽር የእስር ማዘዣ ከተቆረጠላቸው በኋላ የተከሰተውን ውጥረት ለማርገብ በድብቅ የታለመ ሲሆን

እንደሚችል እና ምን ያህል ለግንኙነቷ አስፈላጊ እንደሆነ የሚጠቁም ነው ብለዋል፡፡ የግብፅ መልዕክተኞች የዳርፉርን ክልል የደህንነትና የፖለቲካ ሁኔታዎች በተመለከተ የዓለም ቁልፍ አመራሮች የሚታደሙበት ኮንፍረንስ ይደረግ ሲሉ ያቀረቡትን ሃሳብ ሱዳን ያጣጣለችው ሲሆን ምክንያቷንም የአረብ ሊግ ዳርፉርን በተመለከተ ለሚደረግ ማንኛውም ውይይት መቀመጫ መሆኑን እና የዳፉርን ጉዳይ «ዓለም ዓቀፋዊ» ለማድረግ የሚፈልጉ ተቀባይነት እንደማይኖራቸው በግልፅ ለማሳየት ነው በማለት በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯ አሊ ካርቲ በኩል ገልፃለች፡፡

ጉብኝቱን አስመለክተው ከግብፅ ፕሬዚዳንት ሆስኒ ሙባለክ ጋር በስልክ እንደተወያዩ የተናገሩት የተ.መ.ድ. ሴክሬታሪ ጄኔራል ባን ኪ-ሙን የመልዕክተኞቹ አላማ ግቡን እንደሚመታ እምነታቸው መሆኑን ገልፀው ነበር፡፡ ከሁለት ሳምንት በፊት አልበሽር ከአስር የሚበልጡ በዳርፉር የሰብዓዊ እርዳታ የሚለግሱ ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶችን ለማባረር የወሰኑትን ውሳኔ እንዲያስቀሩ ጫና ያደርጉባቸው ዘንድ መልዕክተኞቹን በተማፅኖ ጠይቀዋቸው ነበር፡፡ ከግብፅ በተጨማሪ በተለይ ቻይና የሱዳን መንግስት ውሳኔውን እንዲለውጥ ጠንከር ያለ ጫና የማሳደር አቅም እንዳላት እምነታቸውን ይገልፃሉ፡፡ ሆኖም የአል-በሽር መንግስት የባን ኪ-ሙን እምነት እውን እንዳይሆን ከአቋሙ የሚመለሱ አይመስልም፡፡ የሱዳን መንግስት የዜና ወኪል መንግስታቸው «የውጭ ድርጅቶቹ በመባረራቸው የሚፈጠረውን ክፍተት ለመሸፈን ብቃት» እንዳለው ለግብፅ መልዕክተኞች መናገራቸውን ዘግቦ ነበር፡፡ ነገር ግን እንደ ባን ኪ-ሙን የሚወክሉት ድርጅትም ሆነ የሱዳን መንግስት ክፍተቱን ለመሸፈን እንደማይቻላቸው አስጠንቅቀዋል፡፡ ሱዳን ከግዛቷ ይውጡ ያለቻቸው ድርጅቶች ለዓለም ዓቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት መረጃዎችን አቀብለዋል የሚል ውንጀላ ትሰነዝራለች፡፡

ለፕሬዚዳንት አል-በሽር የተቆረጠው የእስር ማዘዣ የዳርፉር ክልልን የተመለከቱ የሰላም ጥረቶች እንዳይሳኩ እንቅፋት ይሆናል የሚል የሚገርም ምልከታ የአፍሪካ ሕብረት አለው፡፡ በዚህም ምክንያት በፕሬዚዳንቱ ላይ የቀረበውን ክስ ለማስቆም ወይም ለአንድ አመት እንዲራዘም ለማስደረግ በቅርቡ ወደ ተ.መ.ድ. የፀጥታ ምክር ቤት መልዕክተኞችን እንደሚልክ አስታውቋል፡፡ የአፍሪካ ሕብረት የክሱ ሂደት መዘግየት ለሱዳን «ሰላም» ታላቅ አስተዋፅኦ ይኖረዋል የሚል ዕምነት አለው፡፡ ሆኖም ከ54 የሕብረቱ አባል ሀገርት 30ዎቹ የዓለም ዓቀፉን የወንጀል ፍርድ ቤት ያቋቋመውን የ«ሮም አዋጅ» የፈረሙ ወይም ያፀደቁ መሆናቸው እንዴት አድርጎ በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ፍላጎቱን እንደሚያሟላ አልታወቀም፡፡ የ«ሮም አዋጅ» የተ.መ.ድ የፀጥታው ምክር ቤት የአል-በሽር ጉዳይ ላይ ምርመራም ሆነ የክስ ሂደት ለአንድ ዓመት እንዲዘገይ ወይም እንዲቀር የማስደረግ ስልጣን ይሰጠዋል፡፡

ዓለም ዓቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት ከፕሬዚዳንት አል-በሽር አስቀድሞ በዳርፉር የጦር ወንጀሎች ፈፅመዋል የተባሉ ሁለት ሰዎች ላይ የእስር ማዘዣ አውጥቶ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ሱዳን አንዱን ተከሳሽ በሚኒስትርነት ደረጃ እስከ መሾም በመሄድ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ ውድቅ ማድረጓ የሚታወስ ነው፡፡ በሱዳን ገዢ ፓርቲ «ናሽናል ኮንግረስ ፓርቲ» ውስጥ ያሉ የሲቪል

አመራሮችና ወታደራዊ አዛዦች ከበቂ በላይ ሽክም የሆኑባቸው ናቸው የተባሉትን አል-በሽር ሊያስወግዷቸው ይችላ የሚል አመለካከት እየተንፀባረቀ ይገኛል፡፡ በ2003 የላይቤሪያ መሪ የቻርለስ ቴይለር ፓርቲ - «ናሽናል ፓትርዩቲክ ፓርቲ» - አባላት እና የበታች አመራሮች ከመሪያቸው ጋር አብረው ሄግ ከመዝለቅ ቻርለስ ቴይለርን አሳልፈው መስጠትን መምረጣቸው ይታወሳል፡፡ አሁንም በተመሳሳይ አል-በሽር የቴይለር ዕጣ ሊገጥማቸው የሚችል ነው ተባሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሱዳን ከበርቴዎች ከዓለም ዓቀፉ ማህበረሰብ ጋር ከመጋጨት ይልቅ - ለዓመታት ያካበቱት ሃብት በዓለም ዓቀፍ የኢኮኖሚ ቀውስ እና በነዳጅ ዘይት ዋጋ መውረዱ ተጨምሮ - ፕሬዝደንቱን ምንአልባት አሳልፈው ሊሰጧቸው ይችላ ተባሎ ተገምቷል፡፡

የተቆረጠው የእስር ማዘዣ በጥሬው ሊተገበር የሚችል አይደለም፡፡ የአንዲትን ሉዓላዊት ሀገር መሪ በቁጥጥር ስር ለማዋል ሥልጣን ያለው ዓለም ዓቀፍ የፖሊስ ኃይል የለም፡፡ ሆኖም የፍድ ቤቱ አባል የሆኑ አብዛኞቹ የአፍሪካ ሀገራት አል-በሽር ሀገራቸው ከተገኙ በቁጥጥር ስር የማዋል ግዴታ አለባቸው፡፡ ይህም ፕሬዝደንቱ በሀገራቸው ድንበር ውስጥ ብቻ ተወስነው እንዲኖሩ የሚያስገድዳቸወ ነው፡፡ ከአሁኑ የፍርድ ቤቱ የእስር ትዕዛዛ ተፅዕኖው እየታየ ነው፡፡ በቅርቡ በኢትዮጵያ ስብሰባ የነበራቸው ፕሬዝደንት አል-በሽር «ባልታወቀ» ምክንያት አዲስ አበባ ሳይመጡ ቀርተዋል፡፡ የእስሩ ማዘዣ ላለመምጣታቸው ምክንያት መሆኑ አለመሆኑ ባይረጋገጥም ኢትዮጵያ ቢመጡ እንኳን ተላፈው እንደማይሰጡ የጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ አማካሪ አቶ በረከት ስምዖንን ጠቅሶ «አዲስ ፎርቹን» በባፈው እሁድ እትሙ ጠቅሶ ነበር፡፡

ያም ሆነ ይህ በዳርፉር ክልል ከሚገኙ የአል-በሽር መንግስት ታጣቂ ተቃዋሚዎች መካከል ጠንካራ የሚባለው የ«ጀስቲስ ኤንድ ኢኳሊቲ» መሪ፣«አል-በሽርን በቁጥጥር ስር እናውላቸዋልን» የሚል ጠንካራ መልዕክት አስተላልፏል፡-

« . . . (የአፍሪካ አመራሮች) አል-በሽርን ለመያዝ የሚያስችለው መንገድ ፍርድ ቤቱ የለውም ይላሉ፡፡ ሆኖም የእኛ «ጀስቲስ ኤንድ ኢኳሊቲ» የራሱ የሆነ ታላቅ እና ሃይለኛ መንግድ አለው እንላለን ... በሱዳን ህዝብ ዘንድ መንገድ አለ - የፍትህና የእኩልነት መንገድ፤ ከአለም አቀፍ ማህበረሰብ ጋር በመተባበር የሚተገበር መንገድ፡፡ ከተ.መ.ድ የፀጥታው ምክር ቤት እና ከፍርድ ቤቱ ጋር (ውሳኔውን ከፍፃሜ ለማድረስ) ሙሉ በሙሉ እንተባበራለን» ብለዋል፡፡

# ከአሜሪካ ጋር መላተሙ አዋጪ ነውን?

**በፍቅር አያልቅበት**

**ከ-ጨርቆስ**

የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ መ/ቤት የዓለም ሀገራትን የሰብዓዊ መብት አከባበር በተመለከተ በየዓመቱ ሪፖርት የሚያወጣ ሲሆን፣ሪፖርቱ፦ በተለይም በኢትዮጵያ ላይ የሰነዘረው ትችት የአገዛዙን ሆድ ያስባሰና ያበሳጨ ስለመሆኑ ሰሞኑን ከባለሥልጣናቱና ከመንግሥት ሚዲያዎች የሚሰማው የማጥላላትና የማጣጣል ዘመቻ ይጠቁማል። የስቴት ዲፓርትመንት ባለፈው የካቲት ወር ባወጣው ሪፖርት ላይ የኢህአዴግ መንግሥት በዜጎች፣በተቀናቃኝ ፓርቲ አመራር አባላትና ደጋፊዎች ላይ ተፈጸሙ ያላቸውን የሰብዓዊ መብት ረገጣዎች አሉኝ ያላቸውን መረጃዎች እያጣቀሰ በዝርዝር አቅርቧል።

በኢህአዴግ መንግሥት ላይ ከቀረቡት ውንጀላዎች መካከል ከብዙዎቹ ጥቂቱን ለመቃኘት እንሞክራለን።

... በሀገሪቱ ሕግና ሕገ መንግሥት መሠረት ዜጎች በሰላማዊ መንገድ መንግሥት የመለወጥ መብታቸው ተገድቧል፤የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች ላይ የፀጥታ ኃይሎች እስራት፣ አፈናና ግድያ ይፈጽማሉ፤የፖሊስና የደህንነት ኃይሎች የተቃዋሚ አባላትና ደጋፊዎች ናቸው ባሏቸውና በጠረጠሯቸው ዜጎች ላይ ወከባ፣አፈና፣እስራትና ግርፋት አካሂደዋል። ከሕግ አግባብ ውጪ በርካታ ዜጎች በተለያዩ እስር ቤቶች ታጉረው ይሰቃያሉ .. » ካለ በኃላ ... የኦነግ እና አብነግ ተዋጊዎች ናቸው በሚል በመንግሥት ፀጥታ ኃይሎችና ሚሊሺያዎች ተወሰዱ ያላቸውን የኃይል ርምጃዎች ለንፁህን ዜጎች መሞት፣መቁሰልና ቤት ንብረታቸው መውደም ምክንያት ሆኗል ሲል ያብራራል። በተለይም አዲስ አበባን ጨምሮ በኦሮሚያ በደቡብ፣ አማራ፣ በትግራይና በሱማሌ ክልሎች የመንግሥት ፀጥታ-ኃይሎች ከመጠን ያለፈ የኃይል እርምጃ መውሰዳቸውንና በንፁህን ዜጎች ላይ ግድያ፣ እስርና ወከባ የፈጸሙት ለሕግ አለመቅረባቸውን ሪፖርቱ ያትታል።

በኢህአዴግ መንግስት ላይ የቀረበው ውንጀላ በዚህ ብቻ አልቆመም፣ ... በመንግሥት ስርዓቱ ከታች እስከ ከፍተኛ የሥልጣን እርከን የሚገኙ ባለሥልጣናት አብዛኞቹ በሙስና መዘፈቃቸውን፣የሐገሪቱን ኃብትና ንብረት ባለ ሥልጣናቱ ለግል ጥቅማቸው እንደሚያውሉት፣ የሕግ የበላይነት አለመከበሩንና የዳኝነት አድልዎ በሰፊው እንደሚንጸባረቅ፣ በህገ መንግሥቱ የተደነገገው ... ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ... በተደጋጋሚ መጣሱንና በዚህም ሳቢያ የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞች በተደጋጋሚ እስርና ወከባ እንደሚፈጸምባቸው፣ጋዜጠኞች በተደጋጋሚ እስርና ወከባ ማሰርና ማዋከቡ አለመቆሙን የሚገልጸው ይኸው ሪፖርት በጥቅሉ በአገሪቱ ሰብዓዊ መብት ረገጣው ተጠናክሮ መቀጠሉን አብራርተዋል።

የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ መ/ቤት በአምስት ክፍሎች በከፋፈለው ሪፖርት ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብት ጥሰቶች መፈጸማቸውን አስመልክቶ ያቀረበው ውንጀላ፣የኢህአዴግን መንግሥት ክፉኛ ያበሳጨ ስለመሆኑ ሰሞኑን በመንግሥት ሚዲያዎች የሚደመጡ «ፀረ-አሜሪካን» ዘመቻዎች በቂ ማስረጃዎች ናቸው። ለመጣው ሁሉ የሚያጨበጭበው ዕድሜ

ዘልዛላው ጋዜጣም ኡኡታውን በየርዕስ አንቀጹ ሳይቀር ለማስተጋባት ሞክሯል። እዚህ ጋር ለውድ የጋዜጠዋ አንባቢዎች አንድ ጉዳይ አስታውሼ ልለፍ። ይኸውም የዩናትይትድ ስቴትስ መንግሥት ኢህአዴግ አገሪቱን ከተቆጣጠረበት ጊዜ አንስቶ የዲፕሎማሲና የገንዘብ ድጋፍ ሲያደርግ እንደነበረ፣ለፖለቲካውም ዋልታና ማገር ሆኖ መቆየቱ ይታወሳል። ከዚህም አልፎ «... ለምስራቅ አፍሪካ ጭምር የዲሞክራሲ ፋና ወጊ የሆነው የኢትዮጵያ መንግሥት ትክክለኛውን የእድገት ጎዳና በመከተል ላይ ይገኛል። የሰብአዊ ዲሞክራሲያዊ መርሆችን ይከተላል። የሕግ መሠረትን ጥሏል» በማለት ስርዓቱን አሞካሽቶት ነበር።

በወቅቱም ከቀድሞዎቹ የአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች ጂሚ ካርተር፣ክሊንተንና ቡሽ አንስቶ አምባሳደር ሺን፣ ኮህንና ኤርቪን ሂክስ ... ወዘተ ለአገዛዙ «ዲሞክራሲያዊነት» ሽንጣቸውን ገትረው ሲሟገቱ እንደነበረ አይዘነጋም። ነገር ግን ዛሬ «ያ ቀርቶ ሌላ ጨዋታ መጥቶ» እንዲሉ ዩናይትድ ስቴትስ የተጋረደውን መጋረጃ ስትገልጥ ከወትሮው ከረር ያለ ሪፖርት አውጥታለች። እንደውም አንዳንዶች ይህን ሪፖርቱ ከተመለከቱ በኋላ የሁለቱ አገራት የግንኙነት ድልድይ ወዴት እያመራ ነው? ብለው የስጋት ጥያቄ መጠየቅ ጀምረዋል። ያም ሆነ ይህ ይህ ጠጣር መልዕክት ያልተዋጠላቸው ባለስልጣኖቻችን ተራራውን ለመግፋት የ«መልስ ምት» ሰንዝረዋል።

በአገራችን «የማይመቱት ልጅ ሲቆጡት ያለቅሳል» እንደሚባለው በእኔ አመለካከት ገዢዎቻችን በእሳት ለመጫወት የሞከሩበትንና እንደ ጲላጦስ «ከደሙ ንፁህ ነን» ለማለት የደፈሩበትን አጸፋዊ ምላሽ እንባቢ የራሱን ፍርድ ይሰጥ ዘንድ የኢፌዴሪ ውጭ ጉዳይ መ/ቤት መጋትቢ 1 ቀን 2001 ዓ.ም ያወጣው መግለጫ ከሞላ ጎደል እንደሚከተለው ቀርቧል።

...ኢትዮጵያ ሉዓላዊ ሀገር እንደመሆኗ መጠን ማንም በውስጥ ጉዳያችን ጣልቃ መግባት አይችልም። ... አሜሪካ ውጭ ጉዳይ መ/ቤት ከሰሞኑ ያወጣው ሪፖርት የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያላስገባ መሠረተ-ቢስ ወሬ ነው። ሪፖርቱ ሂዩማን ራይትስ ዎች ተብዬው ያወጣው በአሉባልታ የታጀበ መሠረት የሌለው ወሬ ቀጣይ ክፍል ነው።

... በአገራችን ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች ሕገ መንግሥታዊ እውቅና እንዳገኙ፣ የዜጎች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ደረጃ በደረጃ እየተሻሻለ መምጣቱን ያላገናዘበ ሪፖርት ተቀባይነት የለውም። በመሠረቱ አሜሪካ ሌሎችን የመኮነን አቅም የላትም። በአሸባሪነት ተፈርጀው በጓንታናሞ ታስረውና በዘመናዊ መሣሪያ እየተሰቃዩ መሆናቸው እየታወቀ ሌላውን ወገን የመክሰስ አንድም አቅም የላትም።

... በአንድ አገር ሰብዓዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ዙሪያ የማንም ሀገር መንግሥት ጣልቃ በመግባት «እኛ እናውቅልሀለን» በሚል ያረጀና ያፈጀ አስተሳሰብ ጫና ለማሳረፍ መሞከሩ በምንም መልኩ ተቀባይነት የለውም።

... በአገራችን ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ለማስከበር የምንታገለው ለራሳችን ስንል እንጂ፣ይኼኛውን ወይንም ሌላውን «አለቃ ነኝ ባይ» ለማስደሰት አይደለም ... በመሆኑም

አሜሪካ ላቀረበችው ውንጀላ በየጊዜው አንድ በአንድ ምላሽ እንሰጣለን፡፡» ይላል፡፡ መግለጫው የዓለማችንን ተጨባጭ ሁናቴና የኃይል ሚዛንን ግንዛቤ ውስጥ ያላካተተ ዛቻ አዘል መግለጫ ይመስላል፡፡

አገዛዙ ያወጣውን የ«መልስ-ምት» መግለጫ የታዘቡ … የኢትዮጵያን ህዝብ «እናስተዳድራለን» የሚሉ ባለሥልጣናት ከአንዲት ልዕለ-ሃያል ሀገር ጋር የሚኖረውን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በምን መልኩ ሊቀጥል እንደሚችል፣ በአገር ደረጃ ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮች በየትኛው አቅጣጫ ሊፈቱና ሊሻሻሉ እንደሚችሉ ከግንዛቤ ውስጥ ማካተተት ያልቻሉ፣ የዲፕሎማሲ ግንኙነት አቅማቸውም ቢሆን ውስንና ብልጠት ያልታየበት ነው ሲሉ ተችተዋል፡፡ አሜሪካ በዓለማችን ውስጥ አንድም ተቀናቃኝና ተፎካካሪ መንግስት የሌለባትና የፈለገችውን ሁሉ የማድረግ ሙሉ አቅም እንዳላት በተጨባጭ የሚታወቅ ሆኖ ሳለ፣ ከአገር ሉዓላዊነት ጋር በማያያዝ እንካ ሰላንቲያ መግጠሙ ብዙ ርቀት ሊያጓጉዘን እንደማይችል ፀሃይ የሞቀው ሃቅ እንደሆነ መታወቅ አለበት ይላሉ፡፡

በእርግጥ በዝሆኖች እርግጫ የሚጎዳው ሳሩ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም ቢያንስ አገዛዞች ለራሳቸው ህልውና ሲሉ የተደቀነባቸውን አደጋ ለመቅረፍ ከመጣር ይልቅ ተቃራኒውን መንዝ «ሽኝትን» ከማፋጠን ውጪ ፋይዳ ቢስ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

ከወራት በፊት የአሜሪካ ከፍተኛ ባለሥልጣናት በተደጋጋሚ ወደ አ/አ መመላለሳቸው ለሽርሽር እንዳልሆነ ሰሞኑን የወጣው ሪፖርት አቢይ ምስክር ሲሆን፣ አገር ያወቀውንና ፀሐይ የሞቀውን እውነታ ለመደበቅ መጣሩ ብዙዎችን አስደምሟል፡፡ የግፍ ፅዋ ሞልቶ ከፈሰሰ ደግሞ አወዳደቅን አስከፊ እንደሚያደርግ የጎረቤት አገራት መሪዎች የደረሰባቸውን ሁናቴ በቅጡ መመልከት ይገባል፡፡ ሌላው ቀርቶ አሜሪካ በእልበሽር ላይ የተቆረጠውን የእስር ማዘዣ፣ከላይቤሪያው ቻርለስ ቴይስር በሰንሰለት ተጠፍሮ ዘብጥያ የማውረድ አቅም እንዳላት እየታወቀ የመላተሙ ትርፍ ውጤቱ ምን ይሆን?

«ፍቅር ያለቀ ለት ምነው ካርኒ የለው»፡፡ ከመላተም ይልቅ ሰላም የሚፈጠርበትን ሁናቴ ለማመቻቸት ካልጣርን ዩ.ኤስ.ኤ ቃሉን ከጠ/ሚኒስትራችን ተውሳ «መንገዱን ጨርቅ ያርግልህ» የማለት አቅሙ እንዳላት ማወቅ ይኖርብናል፡፡ ሽኝቱንም ለማፋጠን «ብሶት የወለደው» ዜጋ ይጠፋል ማለት ደግሞ ግብዝነት እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል፡፡

ቸር ያገናኘን !

## ቃለምልልስ

# «አንዳንዶች «ከእኛ ውጪ የመሪነት ቅባት የተቀባ ሰው የለም» ብለው ስለሚያምኑ እንደኔ ዓይነቱን በፖለቲካ መሪነት ማየት አይፈልጉም፡፡»

**አቶ ልደቱ አያሌው**
**የኢዴፓ ሊቀመንበር**

**የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ባለፈው አርብና ቅዳሜ በመላው አለም ከሚገኙ አድማጮቹ ያሰባሰባቸውን በርካታ ጥያቄዎች ለአቶ ልደቱ አያሌው አቅርቦ ነበር፡፡ እኛም ቃለምልልሱን ወደ ጽሁፍ ቀይረን ለውድ አንባቢያን እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡**

***<u>ጥያቄ</u> ፡- የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች በአብዛኛው ከፓርቲው ይልቅ ግለሰቦች ናቸው የሚታወቁት ለምሳሌ ኢዴፓ ከማለት ይልቅ የልደቱ ፓርቲ፣መኢአድ ከመባል ይልቅ የኃይሉ ሻውል ፓርቲ ሲባል እንሰማለን፡፡ ሌሎችም እንደዚሁ፡፡ ስለዚህ የፓርቲን ሥልጣን ለመልቀቅ እንዲህ ከባድ የሆነባችሁ ሰዎች የመንግሥትን ሥልጣን ብትረከቡ አሁን እንዳሉ መሪዎች ሙጭጭ ብላችሁ እንዳትቀሩ ምንድነው ማረጋገጫችን፡፡***

<u>አቶ ልደቱ</u>፡- ይህ ጥያቄ በጣም መሠረታዊና በኢትዮጵያ ፖለቲካ ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ ነው የሚመስለኝ፡፡ በአክብሮትም እመልሰዋለሁ፡፡ ገዢው ፓርቲም ተቃዋሚዎችም ልንወቀስበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ በእኛ በኩል ይህ ባህል መሰበር አለበት ብለን እንምናለን፡፡ በዚህ መሠረት እኔ ኢዴፓን እየመራሁ መቀጠል የምችለው ለሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ብቻ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ በአመራርነትም ልወዳደር አልችልም ይህንን የምናደርገው መሰበርና መለወጥ ያለበት ባህል ስለሆነ ነው፡፡

***<u>ጥያቄ</u>፡- አቶ ልደቱ በ1997 ምርጫ ወቅት ከፍተኛ የሕዝብ ተቀባይነት እንዳተረፉና ማንዴላም እስከመባል እንደደረሱ እናውቃለን፡፡ ያንን ሁሉ የሕዝብ አደራ ገደል የከተቱበት ምክንያት ምንድነው? እርስዎ ሸራተን ላይ ከእነ አቦይ ስብሐት ጋር ተደራድረው ያንን የሕዝብ ትግል እንደሸጡት ነው የሚነገረው፡፡ ምን ያህል እውነት ነው?***

<u>አቶ ልደቱ</u> ፡- ጥያቄው መረጃን መሠረት ያደረገ የፖለቲካ ጥያቄ አይመስለኝም ፡፡ ስለዚህ አድማጩንም፣የኢትዮጵያንም ሕዝብ፣ሬዲዮ ጣቢያውንም እኔንም የሚመጥን አልመሰለኝም ዞሮ ዞሮ ትግሉን ማደናቀፍ ሳይሆን ትግሉን የመቀጠል ሥራ ነው የሰራነው፡፡ እነኚህ ነገሮች ብዙ

ጊዜ ሲባሉ የከረሙና መረጃም ሊቀርብላቸው የማይችሉ ናቸው፡፡ ሕዝቡንም የሀሰት ወሬ እንደሆኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተረዳቸው የመጡ ናቸው፡፡

***ጥያቄ:- አቶ ልደቱ አያሌው ወደ ምክክር መድረኩ አልተጋበዙም፡፡ ምክንያቱም በሕዝብ ዘንድ የተጠላ አቋም ስላላቸው ነው ይባላል፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ በግላቸው ኢህአዴግን እንጥላለን በማለት የሚታገሉት ለምርጫው ምን ያህል ራሳቸውን ብቁ አድርገው ነው፡፡ በምን ዓይነትስ የሕዝብ ድጋፍ ነው?***

አቶ ልደቱ:- እንደሚመስለኝ የወንድሜ ጥያቄ መድረክ ከሚባለው ቡድን ጋር እንዴት በጋራ አትታገሉም የሚል ይመስለኛል፡፡ ከአነጋገርህ እንደምረዳው የ(ቀድሞ) ቅንጅት ደጋፊ ትመስለኛ ለህ ቅንጅት ከሦስት ዓመት በፊት በ1997 የወሰነውን ውሳኔ ታስታውስ እንደሆነ በአደረጃጀት፣በፖለቲካና በኢኮኖሚ ፕሮግራም ከማይመሳሰሉን የፖለቲካ ህብረቶች ጋር አብረን አንሰራም ተብሎ ነው ከነፕሮፌሰር በየነ ፓርቲ ጋር እንድንሰራ የተወሰነው፡፡ ዛሬ ምን አዲስ ነገር ተገኝቶ ከእነሱ ጋር እንድንሠራ ግፊት እንደሚደረግብን አይገባኝም፡፡ ዋናው ጥያቄ እና አብረን ልንሠራ የምንችለው በአደረጃጀት አንድ ከሆንን በፖለቲካና በኢኮኖሚ ፕሮግራም አንድ ከሆንን ብቻ ነው እኔ እስከማውቃቸው ድረስ ደግሞ እነርሱ ከኢህአዴግ የተለዩ የአደረጃጀት የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚ ፕሮግራም የላቸውም፡፡ ዋነው ችግር ይሄ ነው፡፡ ሌላው የተነሳው የሕዝብ ድጋፍን በተመለከተ ነው፡፡ የቅንጅት አመራሮች ይቅርታ ጠይቀው ከተፈቱ በኂላ ከዚያም ባሻገር ተፈትተው ለአምስት ለስድስት ሲከፋፈሉ ከታየ በኃላ ፓርላማ እንግባ ብለው ማመልከቻ ሲያስገቡ አንዳንዶች መኢአድን ወደ መሳሰሉ ድርጅቶቻቸው ከገቡ በኂላ በእውነት የኢትጵያ ሕዝብ ከማን ጋር እንዳለ ትክክልኛ አቋን መያዙን እየተገነዘበ መጥቷል፡፡ ምናልባት እርሶ የዛሬ 3 እና 2 ዓመት የሰሙት ወሬ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ እየጠፋ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ እና በዛ ነው የምንለካው ዞሮ ዞሮ ድጋፍ ኖረም አልኖረም ሀቁ ላይ በመቆም እውነቱን ይዘን የመታገሉ ጉዳይ ነው፡፡

***ጥያቄ :- በእውነት አሉ ከሚባሉ ተቋዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ አሁን ያለው መንግሥት አስፋልት ስለሠራ ወይም አንዳንድ መሠረተ ልማቶች ስለተገነቡ እነዛን በግልጽ የተቃወመ የፖለቲካ ድርጅት የትኛው ነው? ሌላው ትልቁ ተቃዋሚዎች ጋር ያለው ልዩበት ኢትዮጵያዊያኖች ስለሆንን ስለኢትዮጵያም ስለምናውቅ የሰውን መብት እና ዴሞክራሲን በተመለከተ የእርሳቸውን ፓርቲ ከሌሎች ተቃዋሚዎች አንድ ላያደርገው የቻለው ምንድን ነው? ሌላው እርስዎ በ97 ምርጫ ፓርላማ ገብተው መቀመጫ ይዘዋል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ከበፊቱ የሕዝብ መብት እየተሸረሸረ ያለበትና ሠላማዊ ሰልፍ እንኳን የተከለከለበት ሁኔታ አለ፡፡ በአጠቃላይ ሰብአዊ መብት እየተረገጠ ነው ይህን እንዴት ይመለከቱታል፡፡ አንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ መሪ ስለሆኑት ስለ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ መታሰር ምን አመለካከት አለዎት?***

አቶ ልደቱ፡- አስፋልት መሰራቱ የተቃወመ ፓርቲ ታውቃለህ ወይ? ነው ያለኝ ወንድሜ፡፡ ምናልባት አሁን እየተደነቀ ያለው እና በስፋት እየተሠራ ስላለው አስፋልት በመጥቀሴ ይመስለኛ ል፡፡ አስፋልት መሠራቱን የተቃወመ ሌላ ፓርቲ ሰምቼ አላውቅም ልዩነታችን ምንድን ነው አስፋልት ይሁን ሌላ ነገር የተሠራውን ያህል ማለቴ ነው ሌሎቹ አንዳንድ ተቃዋሚዎች ግን ተሠራውን መልካም ነገር እውቅና መስጠት አይፈልጉም፡፡ ይሄ ነው ሰፊ ልዩነታችን መቼም ጤነኛ አዕምሮ ያለው ሰው የተሠራውን አስፋልት የሚቃወም አይመስለኝም፡፡ ሁለተኛው ጉዳይ ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር በዴሞክራሲያዊ በሰብአዊ መብት ጉዳይ ምን ዓይነት ልዩነት አላችሁ ለሚባለው ሰብአዊ መብት መከበር አለበት፡፡ ዲሞክራሲ መከበር አለበት ሲባል በእኛ በተቃዋሚዎች ብቻ ሳይሆን በገዥውም ፓርቲ ፕሮግራም ውስጥም ይገኛል፡፡ ዋናው ቁም ነገር እሱ አይደለም፡፡ ጥያቄው በተግባር እናከብራቸዋለን ወይ? የሚለው ነው እናም በዚህ ረገድ ሁሉም ፓርቲ እምነት ያለው ይመስለኛል፡፡ ከዚህ ከወቅቱ ጋር ተያይዞ በአሁኑ ወቅት የህዝብ መብት እየታፈነ ነው ዴሞክራሲ መብት አይከበርም የሚል ጥያቄ ተነስቷል፡፡ ይህ ጥያቄ ኢትዮጵያ ውስጥ መነሳት የሌለበት ጥያቄ ቢሆን ኖሮ እና የሕዝብ መብትና ዴሞክራሲ የተከበረ ቢሆን ኖሮ የአሁኑ አድማጭ እዚህ ሬዲዮ ጣቢያ አያገኙኝም ነበር፡፡ ትግል ውስጥም ከመጀመሪያው አንገባም ነበር፡፡ ሰብአዊ መብት፣ዲሞክራሲና የመደራጀት መብት ሙሉ በሙሉ ስላልነበረ፣ሰዎች ስለሚታሰሩ እና ስለመሳሰሉት ጉዳዮች እኔ ውጭ ሆኜ በታዛቢነት አይደለም የምመለከተው ወይም የማውቀው በዚህ ስርዓት ውስጥ 6 ጊዜ ታስሬ አይቸዋለሁ፡፡ ብዙ ጓደኞቼም ሲሞቱና ሲሰደዱ አይቻለሁ፡፡ ስለዚህ ይሄ ሁሉ ችግር ባይኖር ኖሮ ዛሬ የትግሉ አካል ሆነን ደፋ ቀና ለማለት አንገደድም ነበር፡፡ እና ሁሉም አዲስ ነገር አይደለም፡፡ የወ/ሪት ብርቱካንን መታሰር በሚመለከት ምን ይሰማሃል? በጣም ከልቤ አዝናሁ፡፡ ምናልባት ሌሎች ሰዎች ወ/ሪት ብርቱካንን የሚያውቋት በሚዲያ ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡ እኔ ግን በአካልም አውቃታለሁ፡፡ ከእስር ከተፈታችም በኃላ በጎ ሠላምታ እንለዋወጥ ነበር፡፡ ስለዚህ እንደማንኛ ውም ህሊና ያለው ሰው በመታሰሯ በጣም አዝናለሁ በጉዳዩ ላይ ግን አቋምን ከሆነ የምጠየቀው የህግ ጉዳይ ነው፡፡ በቂ የሆነ መረጃ ማግኘትን ይጠይቃል፡፡ ያኔ አቋማችንን ልንሰጥ እንችላለን ዞሮ ዞሮ በመታሰሯ የሚሰማኝ ልባዊ ሀዘን ነው፡፡

***ጥያቄ፡- እንደሰው በታሰሩበት ጉዳይ አዝነዋል ጉዳዩን ሲያዩ ግን ፓርቲዎ አቋሙ ምንድን ነው?***

አቶ ልደቱ፡- በፓርቲ ደረጃ አቋም አልወሰድንም ምክንያቱም በቂ መረጃ አላገኘንም ሁላችሁም እንደምታውቁት እነ ወ/ሪት ብርቱካን «መንግሥትን ይቅርታ ጠይቀው ተፈተዋል» ተብሎ ነው ለአንድ ዓመት ከ 6 ወር ያህል የሰማነው፡፡ ለአንድ ዓመት ከ 6 ወር «አይ ይቅርታ ጠይቀን አልተፈታንም» የሚል ማስተባበያም አልሰማንም፡፡ አሁን ወ/ሪት ብርቱካን «አልፈረምኩም አለች» ከተባለ በኋላ እውነት ነው ይቅርታ አልጠየቀችም አሁን መንግሥት ያሠራት በሀሰት

ነው ብለው ከነገሩን እና በዚህ በኩል በቂ መረጃ ካገኘን አቋም መያዝ እንችላለን፡፡ በቂ መረጃ ባልተገኘበት ሁኔታ የፖለቲካ አቋም መያዝ ተገቢ አይደለም፡፡

***<u>ቪኦኤ</u> አቶ ልደቱ እንደ ሚዲያ ነገሩን ግልጽ ለማድረግ የወ/ሪ ብርቱካንን ፓርቲ የአመራር አባላት አነጋግረናል፡፡ ወ/ሪት ብርቱካን ሽማግሌዎቹ ያመጡትን ሰነድ መፈረማቸውን አልካዱም፡፡ ነገር ግን ከይቅርታ ኮሚሽን የመጣውን ሰነድ አልፈረምኩም የሚል አቋም ያላቸው ይመስላል፡፡***

***ጥያቄ ፦ የእርስዎ ፓርቲ ታማኝ መሆኑ ይነገራል፡፡ ታማኝ ልጅ ደግሞ እናቷ የምትሠራውን ታውቃለች፡፡ ስለሆነም በሶማሊያ ስንት ወታደሮች ሞቱብን? ምክንያቱም እርስዎ ደግፈው እንደነበር ይታወቃል ለመሆኑ የሟቾቹ አስክሬንስ የት ነው ያረፈው? ሌላው ኢህአዴግ መንግሥት ሶማሊያ ሲገባ በፓርላማ ያሉ አብዛኛዎቹ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ሲቃወሙ እርስዎ ደግፈውት ነበር፡፡ በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ ወታደር ከሶማሊያ ለቅቆ ወጥቷል፡፡ ሶማሊያ አክራሪዎችም ከመቼውም በላይ ተጠናክረው ጠ/ሚኒስትር የነበሩት ሼክ ሸሪፍም ፕሬዚዳንት ሆነዋል፡፡ በዚህ ጦርነት ውሉ የማይታወቅ የኢትዮጵያ ሠራዊት ተሰውቷል፡፡ ታዲያ የኢህአዴግ መንግሥት ዓላማውን አሳክቶ ወጥቷል ብለው ያምናሉ? እርስዎ ጦርነቱን በመደገፍዎስ የሚወስዱት ኃላፊነት አለ?***

አቶ ልደቱ ፦ …ታማኝ ተቃዋሚ ማለት በዓለም አቀፍ ደረጃ ስናየው መጥፎ ስም አይደለም፡፡ እንደውም ጥሩና የሚፈለግ ስም ነው፡፡ ታማኝ ተቃዋሚ ማለት ሌላ ማለት ሳይሆን ገንቢ ተቃዋሚ ማለት ነው፡፡ በጭፍን የማይቃወም በጭፍን የማይደግፍ፣ለሕግና ለሥርዓት ተገዢ የሆነ እንዲሁም በራሱ መርህ የሚመራና ኃላፊነት የሚሠማው ማለት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ከሆነ ታማኝ ብንባል አይከፋንም፡፡ ምናልባት ከዚህ ውጭ ከሆነና «ለኢህአዴግ ያደላሉ፤ የኢህአዴግ ተለጣፊ ናቸው» ለማለት ከሆነ እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ ከእኛ ፓርቲ የተሻለ ከኢህአዴግ ግልጽ የሆነ ልዩነት ያለው ፓርቲ ያለ አይመስለኝም፡፡ የሶማሊያን ጉዳይ ስናይ እርግጥ ነው ደግፈናል፡፡ እኛ የሶማሊያን ጉዳይ የምናየው እንደ አገር ጉዳይ እንጂ የኢህአዴግ ጉዳይ ነው ብለን አይደለም፡፡ ምክንያቱም ኢህአዴግ ኢትዮጵያ ውስጥ ሥልጣን የያዘው ከ17 ዓመት በፊት ነው፡፡ በሶማሊያ ላይ፤ ያለንን ጥቅም በማስጠበቅ ጉዳይ ተቃውመን መቆም አልፈለግንም፡፡ ፓርቲያችን ኃላፊነት የሚሰማው ፓርቲ ስለሆነ በፓርቲና በሕዝብ መካከል እንዲሁም በሀገር መካከል ያለውን ጥቅም ስለምናውቅ ከዚህ ቀደም ህውሀትና ኢህአፓ የተሳሳቱት ስህተት ደግመን ለመሳሳት አልፈለግንም፡፡ በደርግ ጊዜ የዚያድ ባሬ መንግሥት ኢትዮጵያን ሲወጋ ደርግን የተቃወመ መስሏቸው የአሁኖቹ ገዢዎች ወይም ሕወሐቶች ከዚያድ ባሬ መንግሥት ጋር የቆሙበት ሁኔታ ነበር እንደዛ ዓይነቱን ታሪካዊ ስህተት የእኛ ፓርቲ ሊደግመው አይችልም፡፡ በወቅቱም ደግሞ የእስላማዊ ሀይሉ በኢትዮጵያ ላይ ግልጽ የሆነ ጀሀድ

አውጆ ስለነበረ አጋዴንንም ጥያቄ ውስጥ አስገብቶ ለእኔ የሚገባ ግዛት ነው ብሎ ስለነበረ በተባበሩት መንግሥታት መረጃ መሠረት ደግሞ ከ 9 እና ከ 10 የማያንሱ የአረብ አገሮች ከፍተኛ የሆነ ወታደራዊ እንቅስቃሴ እዚያ አካባቢ እያደጉ መሆኑ ስለተረጋገጠ ነው:: የደገፍነው እንጂ ምናልባት በዚህ ጉዳይ ኢህአዴግን ለመደገፍ ፈልገን አይደለም::

***<u>ጥያቄ-</u> አቶ ልደቱ ለሀገር ደህንነት ለመቆርቆር በሶማሊያ በተደረገው ጣልቃ ገብነት መደገፍ የፖለቲካ መብት ነው::ነገር ግን እንደሚያሳታውሱት በኢትዮ ኤርትራ ጦርነትም ጊዜ በርካታ ኢትዮጵያን ወታደሮች ወደ ጦርነት ተልከውና ስንት እንደሞቱና የት እንደሞቱ እንደተቀበሩ ለቤተሰቦቻቸው መርዶ እንኳን በትክክል አልተነገረም:: በሶማሊያ ጉዳይ ጠያቂው ያሉት ስንት ወታደሮች እንደሞቱና የት እንደተቀበሩ ያውቃሉ? ይህንንስ ለማረጋገጥ ሙከራ አድርገዋል ወይ? ጣልቃ ገብነቱንም እንደደገፋችሁ ማለቴ ነው?***

<u>አቶ ልደቱ</u>- ጣልቃ ገብነት ነው የሚባል አይደለም ይሄ ጣልቃ ገብነት ሳይሆን እራስን የመከላከል እርምጃ ነው:: ይህ ጉዳይ በተለይ በጦርነቱ አጠቃላይ ሂደት ላይ ያለው አሰራር ግልፅነትን የተከተለ መሆን አለበት:: ከፓርላማው ወይም ከኢትዮጵያ ህዝብ ተደበቀ መሆን የለበትም:: ኤህአዴግ ግን ይህን የግል ጉዳይ እያደረገው ነው::ግን ተገቢ አይደለም እያልን ፓርላማ ላይ አጀንዳ አስይዘን የጠየቅንበት ጊዜ አለ:: እኛ እኛ የምንፈልገው ያህል በጦርነቱ ሂደት ግልፅነት አልታየም እኛም ከፍተኛ የሆነ ተቃውሞና ቅሬታ አለን:: አሁንም ይፋ ሆኖ የሞቱ ሰዎች ቁጥር መታወቅና ለቤተሰቦቻቸው ይገለፃል እየተባለ ሲወራ እንሰማለን:: ግን እስካሁን መንግስት ይፋ በሆነ መልኩ ሲናገር አልሰማንም ይህም ተገቢ አይደለም:: እና በአጠቃላይ ሂደቱ ምን ያህል የኢኮኖሚና የሰው ሀይል ከፍለናል የሚለውን ነገር በግልጽ መታወቅ አለበት::

***<u>ጥያቄ</u>- አቶ ልደቱ ቀድሞውኑ የኢህአዴግ ሚስጥራዊ አባል እንደሆኑ ይታወቃል:: ኢህአዴግ ከምንም በላይ የመኢአድን መሪ ኢንጅነር ሀይሉን ስለሚጠላ ቅንጅት ውስጥ የተከለዎት ነዎት:: ድርጅቱን የማፍረስ ሥራዎን ካከናወኑ በኋላ አሁን በግልፅ የኢህአዴግ አባል የማይሆኑት ለምንድን ነው? ምንስ ቀረዎት? በተጨማሪ በመላ አማራ ድርጅት ውስጥ በነበሩበት ወቅት እጅግ ጠቃሚ ነው የተባለ ሰነድ ወስደው ለህወሐት ሰጥተዋል መባሉን አውቃለሁ:: በዚህ ሳቢያ ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ እስር ቤት ገብተው ለህልፈት በቁ ለእርሳቸው ህይወት መጥፋት አስተዋፅኦ ማድረግዎም ይሰማል:: በሌላ በኩል እጅዎ ከሙስና ያልፀዳ ለመሆኑ ማስረጃ ተይዞብዎታል ህወሓትም ለራሱ ፖለቲካ ይጠቀምበታል ይባላል ምን ይህል እውነት ነው? የሙስናው ጉዳይ ከላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት ቅርፃቅርፆች መሰረቅ ጋር የተያያዘ ነው:: ምላሽዎ ምንድ ነው?***

አቶ ልደቱ- (ሣቅ... ) ማስታወሻዬን ሳገላብጥ ከ80 በላይ አሉባልታዎች ውስጥ እነዚህ አሁን የተጠቀሱት ጥቂቶቹ ናቸው:: ብዙ ጊዜ ስንሰማቸው የኖርን ስለሆኑ ለእኔ አዲስ ነገር አይደሉም::ግን ችግሩ ምንድን ነው በፖለቲካ አጀንዳ እና በኢኮኖሚ አጀንዳ ተከራክሮ ሰውን ማሸነፍ ሲያቅታቸው ታርጋ እየፈጠሩ ሠው ላይ መለጠፍ ልማዳቸው ነው:: ዞሮ ዞሮ የህውሐት ሚስጥራዊ አባል ነበሩ ለተባለው ሚስጥራዊ አባል መሆኔን የሚያውቅ ሰው መቼም ኢህአዴግ መሆን አለበት:: ስለዚህ እርስዎ ኢህአዴግ ሆነው ነው ማለት ነው የእኔን ኢህአዴግነት ያወቁት:: ሁለተኛው ቅንጅት ከፈረሰ በኂላ ለምን ኢህአዴግ አይሆኑም ነው የተባለው:: እንግዲህ ቅንጅትን ያፈረሰው እሱ ነው የሚለውን ጥያቄ ሠፊ ፕሮፓጋንዳ ተሰርቶበታል ግን ሁለት ጥያቄ መመለስ አለብን:: አንደኛ በምን መልኩ ነው እኛ ያፈረስነው? እንዲህ ብዙ ሠዎች ልደቱ ቅንጅትን አፈረሰው ሲሉ ይደመጣሉ አንድ ልደቱ የሚባለው ተራ ግለሰብ ቅንጅትን ያህል ትልቅ የተባለ ድርጅት ማፍረስ የሚችል ከሆነ ቅንጅት መጀመሪያ ደካማ ወይም መፍረስ የሚገባው ድርጅት ነበር ማለት ነው:: አንዳንዶች ደግሞ የለም በቀጥታ ባታፈርሱትም እናንተ ስትወጡ ቅንጅት ፈረሰ ይላሉ:: ቅንጅትን እኛ ያላፈረስነው ሥለመሆኑ የቅንጅት መሪዎች ከእስር ቤት ከወጡ በኂላ ለ5 እና ለ6 ሲበታተኑ እርስ በእርሳቸው አንዳቸው ሌላቸውን ወያኔ እያሉ ሲከሱ እያየናቸው ነው:: ያፈረስነው እኛ ብንሆን ኖሮ እኛ ከእነሱ ስንለይ ችግሩ ይቆምና ቢያንስ ያሉት ድርጅቶች ተስማምተው ይቀጥሉ ነበር::

***ጥያቄ- አሁን በያዙት የትግል ስልት ለኢትዮጵያ ህዝብ ምን ያህል ሰላምና ዲሞክራሲ አመጣለሁ ብለው ያስባሉ:: ሠላማዊ ትግሉስ አዋጭ ነው? መጀመሪያ ከላሊበላ ከመጡ በኂላ በመዐህድ ውስጥ ሲሳተፉ መዐህድን ለሁለት ለመክፈል የወጣት ማህበራት ሲያደራጁ ቆይተው ያ ሲታወቅብዎ የራስዎን ኢዴፓን አቋቋሙ:: ካቋቋሙም በኂላ በቅንጅት አባልነት ሲሰሩ ቆይተው በመጨረሻ የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ከግቡ ላይ ሲደርስ በትክክል የመለመለዎ ኢህአዴግ እንደሆነና ሁሉንም ትተው ፓርላማ እንደገቡ ይታወቃል:: መጀመሪያውኑ ከላሊበላ ሲመጡ በኢህአዴግ ተመልምለው መሆኑ የኢትዬጵያ ህዝብ አያውቅም ብለው ነው? እባክ እውነቱን ይመልሱልን?***

አቶ ልደቱ- በአጠቃላይ እንደው ከውጪ የምሰማቸውን ጥያቄዎች በተመለከተ በአጠቃላይ የአሉባታ ኔትወርክ አለ ያን ኔትወርክ ተፈለፈለ እየተመካከረ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ማዝነብ ነው እያየን ያለነው:: ኢትዮጵያ ውስጥ ይሄ ቢባል ብዙ ላያስደንቅ ይችላል:: ግን አሜሪካ፣ስዊድን ወይም ሌላ ቦታ ተሁኖ ፓርላማ መግባት ወንጀል ነው ወይም በሌላ መልኩ ከሌሎች ጋር ተባብሮ ለመሥራት መጣር የምክኒያት ፖለቲካ ይዳብር ማለት እንዲህ ዓይነቱ ወንጀል ሆኖ ሲታይ በጣም በጣም ነው የሚገርመኝ ኢትዮጵያ ውስጥ የዛ ዓይነቱን የፖለቲካ ባህል ለማምጣትና ለመከተል የሚታገሉ ኃይሎች ለምን እንደሚጠሉና ከሀዲ፣ወንጀለኛ፣ባንዳና ተለጣፊ እንደሚባሉ አይገባኝም:: ሌላው ወንድሜ ከላሊበላ ጀምሮ የኢህአዴግ አባል ሆነህ

ተመልምለህ ነው የመጣኸው አሁን ለምን ኢህአዴግነትህን አትነግረኝም:: ሲጀመር ኢህአዴግ ሆኜ ቢሆን ሌላ ፓርቲ መመስረት ምንም አያስፈልገኝም ነበር ለእናንተም ለመናገር የሚያስፈራ አይመስለኝም ወይም ደግሞ ኢህአዴግ መሆን አንድ የፖለቲካ አመለካከት ነው መቼም ሁላችንም በየአካባቢው ዘመዶች ጓደኞች አሉን የኢህአዴግ አባላት የሆኑ ማለት ነው ታዲያ አብረን ከእነሱው ጋር እየኖርን ነው:: ይህንን እንደ ሀጢያት አይቼ ከሆንኩ እንደሀጢያት የማፍርበት ጉዳይ የለም::

***ጥያቄ:- እስካሁን ከሰማናቸው አብዛኛው አድማጭ ከውጭ ብቻም ሳይሆን ከተለያዩ አካባቢዎች የመጡልን በእርስዎ ድርጅትና የፖለቲካ ሚና ላይ ጥርጣሬ ያላቸው ናቸው እና ለዚህ ጥርጣሬ መንስኤው ምንድን ነው የሚሉት እንደሚባለውም በአንድ ወቅት ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ የነበረዎት የፖለቲካ መሪ ነዎት ለዚህ ጥርጣሬ ምንጩ ምን ይሆን? ከዚህ በፊት ከካፒታል ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ መጠይቅ ኢህአዴግ ከ 2005 ምርጫ በኃላ የሕዝቡን ጥያቄ መመለስ ጀምሯል ብለዋል አቶ ልደቱ ኢህአዴግ እየመለሳቸው ያለው የሕዝቡ ጥያቄዎች ምንድን ናቸው? በእነዚህ ላይ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ቢሰጡኝ?***

**አቶ ልደቱ**:- የጥርጣሬው ምንጭ ሁለት ነገር ነው አንደኛው የጄነሬሽን ጋፕ ጉዳይ ነው ብዙ ሰዎች አሁን በገዢነትም በተቃዋሚነትም የፖለቲካ ድርጅቶችን እየመሩ ያሉት በ 1960ዎቹ ፖለቲካ የአንድና የሌላ ፓርቲ አባል ሆነው እርስ በእርስ ሲጠላለፍና ሲገዳደሉ የነበሩ ናቸው:: አሁንም የፖለቲካ መሪነቱን ይዘው የቀጠሉት እነርሱ ናቸው:: የአዲሱ ጀነሬሽን አካል የሆነ ሰው በፖለቲካ መጥቆ ተቀባይነትና ተሰሚነት እንዲያገኝ ፍላጎት የሌላቸው አሉ እስኪሞቱ ድረስ የኢትዮጵያ የፖለቲካ አመራርነት ከእኛ እጅ መውጣት የለብንም ብለው የሚምኑ ሰዎች አሉ እነዚህ ሰዎች በተለያየ የፖለቲካ ቡድን ተቧድነው ዘመቻ የሚያደርጉ ናቸው በአንድ በኩል ተቃዋሚ ፓርቲዎች በተለይ በምርጫው ሰሞን ሥልጣን ልንይዝ ተቃርበናል ይህን ሥልጣን ስንይዝ እዛ ውስጥ ሊያስቸግረን የሚችል የመብት ጥያቄ የሚያነሳ የፈለግነውን እንደልባችን እንድናደርግ የሚያደርገን ማነው ከተባለ በኋላ ኤዲፓንና ልደቱን መምታት አለብን ተብሎ የተቀነባበረ ዘመቻ ነው የተካሄደው በአንድ በኩል ተቃዋሚዎች ይህን ሲያደርጉ ገዢው ደግሞ እነሱ የሚያወሩትን አሉባልታ ለእነሱና ለራሱ ጥቅም በሚመቸው መልኩ በመጠቀም ልደቱ ኢህአዴግ ነው የእኛ ሰው ነው እያለ በካድሬዎቹ አማካኝነት በሕዝብ ውስጥ ማስወራት ነው የጀመረው መጨረሻ ላይም ከሌሎቹ ነጥሎ እኔን ባለማሰር ይህን ፕሮፓንጋዳና አሉባልታ እውነት ለማስመሰል የሚፈልገውን ነገር አድርጓል:: ዋናው የጥርጣሬ ምንጭ እንዲፈጠር የተደገፈው በዚህ መልኩ በተቀነባበረ ፕሮፓጋንዳ ነው:: ይህ ፕሮፓጋንዳ በሰው አፍ ብቻ አይደለም በሬዲዮ ጣቢያም በጋዜጣም በኢንተርኔትም በከፍተኛ ቅንብርና ዘመቻ የሚካሄድ ነው:: ሁለተኛው ዘረኝነት ነው አንዳንድ ሰዎች ከእኛ ውጪ የኢትዮጵያ መሪ የመሆን ቅባት የተቀባ ሰው የለም ብለው ስለሚያምኑ እንደኔ ዓይነቱን በፖለቲካ መሪነት ማየት አይፈልጉም::

ሌላው ጥያቄ ኢህአዴግ የህዝቡን ጥያቄ መልሷል የተባለው በገሀድ እያየን ነው፡፡ በምርጫው ተደናቅፏል፡፡ በዛ ምርጫ የተወሰነ ሥራ ካልሠራ በስተቀር ተመሣሣይ እጣፋንታ ወደፊት እንደሚገጥመው ያውቃል ከምርጫ 97 በኃላ ልን እንደ አዲስ ፓርቲ ሌት ተቀን የሚሠራበት ሁኔታ ነው እያየን ያለነው ለምሳሌ አዲስ አበባን መውሰድ ይቻላል፡፡ በአሁኑ ሰዓት እየተሠሩ የሕዝብ እየታደሉ ያሉት የኮንደሚኒየም ቤቶች ሌት ከቀን እየተሠራ ያለው መንገድ በየሰፈሩ እንዲደራጁና ብድር እንዲያገኙ እየተደረጉ ያሉ ወጣቶች እና የመሳሰለው ከሌላ ጉዳይ ጋር ተያይዞ አይደለም እንደዚህ ዓይነት ጥቅም በኅብረተሰቡ ውስጥ ማሳየት ካልቻልን በሥልጣን ላይ መቆየት አንችልም የሚል ስሜት ኢህአዴግ ውስጥ ስለተፈጠረ ነው፡፡